# የክርስቶስ የደሙ

# ኃይል

አንድሪው ሙሬይ እንደጻፈው

አሸብር ገብሬ እንደተረጎመው

2002 ዓ.ም

የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved
ያለ ተርጓሚው ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሣተም በህግ ያስጠይቃል።
የመጀመሪያው ሕትመት 2002 ዓ.ም
ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው
"The power of the Blood of Jesus"
By Andrew Murray
Copy right 1993
Whitaker House
580 Pittsburgh Street
Springdale, PA 15144
ከሚለው መጽሐፍ ነው

አንድሪው ሙሬይ በዚህች መጽሐፍ አማካይነት አንባቢዎች ክቡር ስለሆነው የክርስቶስ የደሙ ኃይል የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይመክራሉ።

ማንኛውም ሰው በሕይወት ዘመኑ በድል አድራጊነት ሕይወት ሊመላለስ የሚችለው ስለክርስቶስ የደሙ ኃይል ትክክለኛ መረዳት ካገኘና ይህንንም መረዳት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በሕይወቱ የተለማመደው እንደሆነ ብቻ ነው። ይህች መጽሐፍ መንፈሳዊ ውጊያ በማካሄድ ወደ ድል ሕይወት የምናመራበትን ቁልፍ የጦር ዕቃ ይዛለች።

## ምሥጋና

- ከሁሉ አስቀድሞ ይህችን መጽሐፍ እንድተረጉም የረዳኝን ልዑል እግዚአብሔርን አመሠግናለሁ።
- ይህን መጽሐፍ በማሳተም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማገልገል ከፍተኛ ተግባር ላከናወኑት ለደቡብ አጥቢያ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።
- ይህን መጽሐፍ በማረምና በማበረታታት ለረዳኝ ለመጋቢ ተኩ ክበደ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።
- በብዙ ለረዳኝ ላበረታታኝ በሕይወቱም በሥራውም በፍቅሩም በቅንነቱም መልካም ምሣሌ ለሆነኝ ወንድሜ ለምወደው ለመጋቢ ዳንኤል ገ/ሥላሴ ታላቅ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።
- በፍቅሩ፣ በወንድምነቱና በቅንነቱ ለምወደውና ለማከብረው ለዚህች መጽሐፍ ሕትመት ከደቡብ መሠረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር አብሮ ለደከመ ለወንድም ምናሴ በየነ ታላቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።
- በወንድማዊ ቅንነት እና አርቆ አሳቢነት ብስለት ያለው ሐሳብ በመለገስ ለትርጉሙ እርምትና መሻሻል በጽሑፍ ገንቢ ሐሳብ በመስጠት ለተሳተፈው ለመጋቢ ዮናታን ተኪኤ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።
- መጽሐፏን በዝርዝር በማየት ለትርጉሙ መሻሻል መታረም የሚገባውን በግልጽ በመጠቆም በልባዊ ቅንነት አስተያየቱን በጽሑፍ ለገለጸልኝና ላበረታታኝ ወንድሜ ንጉሤ ቡልቻ ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

በክርስቶስ አካል ተሳታፊ የምትሆኑና የሆናችሁ ከአገርውጪና በአገር ውስጥም ያላችሁ ወገኖች ሁሉ ይህችን መጽሐፍ አንብባችሁና አስነብባችሁ ራሣችሁንና ሌሎችን በማገልገል ፈጣሪአችንን እግዚአብሔርን ለምታከብሩ ሁሉ እውነትና የእውነት ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ማንነታችሁንና ቤተሰባችሁን ይባርክ !!

ተርጓሚው



# (የመጽሐፍ ማውጫ)

መቅድም .................................................. 6
ምዕራፍ አንድ .................................................. 8
ስለ ደም የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ምንድን ነው?
- ስለ ደም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አስተምህሮ
  ብሉይ ኪዳን ስለደም ምን ያስተምረናል?
- ጌታችን ኢየሱስ ስለ ደም ምን አስተማረ?
- በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የሐዋርያት ትምህርት
- ደምን በተመለከተ የራዕይ መጽሐፍ ምን ይላል?
- ከቅዱሳት መጻሕፍት የምንማራቸው ትምህርቶች
- ኃጢአትን የማሸነፊያ ብቸኛው መንገድ
- ስለደሙ ትክክለኛ አመለካከት
- የደሙ በረከትና ኃይል
- የደሙ ኃይል መገለጥ

ምዕራፍ ሁለት .................................................. 19
በደም መዋጀት
- የደም ኃይል ያለው ምን ውስጥ ነው ?
- ሕይወት ያለው በደም ውስጥ ነው
- ለእግዚአብሔር በመሰዊያ ላይ ይቀርባል
- የደሙ ኃይል የፈጸመው ነገር ምንድን ነው?
- ደሙ መቃብርን ከፈተ
- የክርስቶስ ደም ለማያትን ከፈተ
- በሰው ልብ ውስጥ ባሉ ኃያል ነገሮች ሁሉ ላይ
- ይህ ኃይል እንዴት ይሰራል?
- ኃይሉ በእምነት ውስጥ ይሰራል
- መንፈሱና ደሙ
- ዕውቀት አስፈላጊ ነው
- ፍላጎትና ከፍተኛ ምኞት
- በጉጉት መጠበቅ

ምዕራፍ ሶስት ............................................ 29

በደም አማካይነት መታረቅ

- ኃጢአት እርቅን አስፈላጊ አደረገው
- እርቅ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ቅድስና ተወስኗል
- እርቅ የተገኘው በክርስቶስ ደም ነው
- ይቅርታ እርቅን ይከተላል

ምዕራፍ አራት ............................................ 39

በደም አማካይነት መንፃት

- መንፃት በብሉይ ኪዳን ጊዜ
- በአዲስ ኪዳን መንፃት እንደ በረከት ነው
- የዚህን በረከት ሙሉ እርካታ መለማመድ

ምዕራፍ አምስት ............................................ 48

በደም አማካይነት መቀደስ

- ቅድስና ምንድን ነው?
- ቅድስና የክርስቶስ መከራ ዓላማ ነው
- ቅድስና እንዴት በደም እናገኛለን?

ምዕራፍ ስድስት ............................................ 56

ሕያው እግዚአብሔርን ለማገልገል በደም መንፃት

- በእግዚአብሔር መገኛ ውስጥ በትክክል መኖር
- መንፈሳዊ መስዋዕት ለእግዚአብሔር የማቅረብ አገልግሎት
- የደሙ ኃይል ለሌሎች በረከት ለማምጣት
- በምልጃ
- እንደ ንዋየ ሕልየት /የሙዚቃ መሣሪያ

ምዕራፍ ሰባት ............................................ 68

በደሙ አማካይነት በቅድስት ውስጥ መኖር

- እግዚአብሔር ለእኛ ምን አዘጋጀ?
  ሀ. ቅድስትን
  ለ. በደሙ አማካይነት መንፃትን
- አዲስና ሕያው መንገድ
- ታላቁ ሊቀካህን
- እንዴት እንዘጋጅ?
  - በቅን ልብ እንቅረብ
- ሙሉ የእምነት መረዳት
- ልባችንን ተረጭተን እንቅረብ
- ሰውነታችንንም ታጥበን
- እንቅረብ

ምዕራፍ ስምንት ............................................ 83

ሕይወት በደም ውስጥ

- ደሙን የመጠጣት በረከት
- ይህ በረከት በእኛ ውስጥ እንዴት ይሰራል?
- ለሚጠጣው ደሙ የእኛ አመለካከት

ምዕራፍ ዘጠኝ ............................................ 90

ድል በደሙ አማካይነት

- አንድ ጊዜ ለሁሉም የተገኘው ድል
- ድሉ ለዘለዓለም ይቀጥላል
- በዚህ ድል ውስጥ የእኛ ድርሻ ምንድን ነው?
- መንፈሳዊ ውጊያ ማካሄድ
  - ያለ ውጊያ ድል የለም
- ድል የምናደርግበትን እምነት መያዝ
- በበጉ ደም ኅብረት ውስጥ ድል አድራጊነት እንዳለ መረዳት

ምዕራፍ አስር ............................................ 100

በደሙ አማካይነት ሰማያዊ ሐሴት

- ደሙ በመንግሥት ሰማይ ትክክለኛ ስፍራ ይሰጣል
- ደሙ ለመንግሥት ሰማይ ብቃትን ይሰጣል
- የፈቃድና የአእምሮ ውስጣዊ ስምምነት
- ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ከእርሱም ጋር ህብረት በማድረግ መደሰት
- ደሙ ለመንግሥት ሰማይ ዝማሬ ርዕስ ይሰጣል

# መቅድም

ይህች መጽሐፍ በጌታ ያንቀላፉት አባቴ ሬቨረንድ አንድሪው ሙሬይ “ የክርስቶስ የደሙ ኃይል “ በሚል ርዕስ ከፃፉት ተከታታይ ጽሑፎች በከፊል የተተረጎመ ነው። ሬቨረንድ አንድሪው ሙሬይ የማስተርስ ዲግሪ እና በሥነ- መለኮት የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ያገኙት ይህችን መጽሐፍ ከፃፉ በኋላ ነው።

ይህን መጽሐፍ ከዳች ቋንቋ ወደ እንግሊዘኛ የተረጎመው ዊልያም ዳግላስ የሚባል ሰው ሲሆን ለረጅም ዓመታት የአባቴ የቅርብ ጓደኛ ነበር። አባቴ ከዚህ ሰው ጋር የተዋወቁት በደቡብ አፍሪካ በኬስዊክ ኮንቬንሽን ሙቭመንት ውስጥ ነው። አባቴ በሕይወት ሳሉ ለሚስተር ዳግላስ ይህን መጽሐፍ እንዲተረጉም ፈቃቸውን ሰጡት። የጸሎት ሕይወት የሚባለውንም መጽሐፋቸውን ተርጉሟል። ከአባቴ ሕልፈተ ሞት በኋላም የሕይወት ታሪካቸውን ለመፃፍ በቅቷል።

የአባቴን የእጅ ጽሑፍ ከእንግሊዘኛው ትርጉም ጋር በማስተያየት በድንቅ ሁኔታ እንደተተረጎመ ማረጋገጥ ችያለሁ። ሚስተር ዳግላስ የአባቴን ሐሳብ በትክክል እንደተረጎመው እመሰክርለታለሁ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ምዕራፎች በጸሎትና በጥሞና ላነበባቸው ብዙ በረከት እንደሚያተርፍለት እርግጠኝነት ይሰማኛል።

በአዳኛችን እና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ የደም ኃይል በመጠቀምና በመለማመድ ለመኖር እንደምታነቡት ባለሙሉ ተስፋ ነኝ።

በተባረከው የጌታ አገልግሎት ላይ በሕይወት ያለሁት ልጃቸው ኤም.ኢ. ሙሬይ



# የተርጓሚው ማስታወሻ

በምእራፎቹ ውስጥ ሁሉ ዶ/ር ሙሬይ “የመስዋዕቱ ደም” የሚለውን ቃል ተጠቅመዋል ይህን አገላለጽ መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚጠቀምበት መገንዘብ ያስፈልጋል።

ምዕራፍ ሶስትን ስታነብቡ እንድታስታውሉ ዶ/ር ሙሬይ የተጠቀሙት የዳች መጽሐፍ ቅዱስ “ቤዛ” ለሚለው ቃል “Verzoening” የሚል ቃል ይጠቀማል “Verzoening” ማለት መታረቅ ማለት ነው። በዚህ ትርጉም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው ይህ ቃል ነው።

ዊልያም ኤም ዳግላስ

# ምዕራፍ አንድ

## ስለ ደም የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ ምንድን ነው

" … የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ…

ዕብ. 9፡7

እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮችና ሁኔታዎች ተናግሮናል፡፡ ቃሉ የማይለወጠው የህያው የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ያስረዳናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በአጠቃላይ ማንበብና በተለያዩ ክፍሎች ላይ የሰጠውን ግልጽ እውነታዎች በእምነት መቀበል አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ እውነታዎች ደግሞ በመገለጥ ወይም በእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ እንዳሉ ልብ ልንል ይገባል፡፡ ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ እውነቶች ትኩረታችንን ከሚስቡ ከሌሎች ነገሮች ልቀው መገኘታቸውና በእያንዳንዱ አዳዲስ የእግዚአብሔር መገለጥ ውስጥ ፀንተው መቆም የሚችሉ በመሆናቸው የሃይማኖት ሥርዓቶች ቢለወጡ እንኳ እነርሱ ግን ሳይፋለሱ መለኮታዊ ጠቀሜታቸውን እንደያዙ የሚዘልቁ መሆናቸውን ያስገነዝቡናል፡፡

ዓላማዬ ይህን መግቢያ የከተለው በሚመጡት ምዕራፎች ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ ክቡር የደም ኃይል የሚያስተምረውንና በደሙም አማካይነት የተገኙልንን በረከቶች ለማሣየት ነው፡፡ ውድ አንባቢዎቼ አንድ ነገር ግልጽ ላደርግላችሁ እወዳለሁ፣ ይኸውም በገለጻዬ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ የተሻለ መሠረት መጣልም ሆነ ስለ ደሙም የመዋጀት ኃይል የበለጠ ማስረጃ ላቀርብ አልችልም፡፡ ነገር ግን በትህትና ልጠይቃችሁ የምወደው በትዕግስት ከእኔ ጋር በመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ውስጥ በማለፍ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በወሰነው ልዩ መገለጥ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለደሙ የሰጠውን ልዩ ቦታ አብረን ከቃሉ እንድንመለከት ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ደም አንድ ቁንጽል ሐሳብ ሳይሆን በስፋት መጠቀሱ ግልጽ ነው፡፡ ከዘፍጥረት  እስከ ራዕይ ብንመለከት በተደጋጋሚና በግልጽ ተጽፎ እናነባለን፡፡ ደም የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ተደጋግሟል፡፡ ስለዚህ መሠረታዊው ጥያቄያችን ቅዱሳት መጽሐፍት ስለ ደም ምን ያስተምራሉ? የሚለው ነው፡፡



- *በመጀመሪያ፡     በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት*
- *ሁለተኛ፡  በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ውስጥ*
- *ሶስተኛ፡   ሐዋርያት ባስተማሩት ትምህርት ውስጥ*
- *አራተኛ፡  ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በራዕይ መጽሐፍ ስለ ደም ምን ነገረን ?*
- *በመጨረሻም፡በአጠቃላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ልንማር የምንችለው ትምህርት ምንድን ነው ?*

## ስለደም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አስተምህሮ

### ብሉይ ኪዳን ስለ ደም ምን ያስተምረናል

ስለ ደም መጻፍ የተጀመረው በኤድን ገነት መግቢያ በሮች ላይ ነው፡፡ ወዳልተገለጠው የኤድን ገነት ምስጢር አልገባም ነገር ግን ከአቤል መስዋዕት ጋር የተያያዘው ነገር ሁሉ ግልጽ ነውና፡፡  ከመንጋው የተመረጠውን በኩር ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጐ በመቅረቡ የደም መስዋዕት አምልኮ የመጀመሪያውን የመሠረት ድንጋይ አኖረ (ዕብ 11፡4)፡፡ አቤል በእምነት ለእግዚአብሔር መስዋዕትን አቀረበ ስለዚህ አማኞች ከሚባሉት የስም ተርታ ውስጥ ስሙ መጻፉን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ በዚህ የእምነት እርምጃው "እግዚአብሔርን ደስ አሰኘ" የሚል ምስክርነትን አትርፏል፡፡ የአቤል እምነት፣ የእግዚአብሔር ልዩ ደስታና የመስዋዕቱ ደም በአንድነት የተያየዙ ነበሩ፡፡ በሰው ልጆች ታሪክ ጅማሬ ላይ የተሰጠው ይህ የመገለጥ ፋና ምስክርነት ጥልቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ያለ ደም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፣ በእምነት ከእርሱ ጋር ሕብረት ማድረግ እና በእርሱም ውስታ መደሰት ፈጽሞ የማይቻል እንደሆነ ያሳያል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስላለፉት አሥራ ስድስት ክፍለ ዘመናት አጭር ማሳሰቢያ ይሰጠናል፡፡ ይኸውም በሰው ኃጢአት ምክንያት የሰው ዓለም በእግዚአብሔር የፍርድ ውኃ ጥፋት መደምሰሱን ይገልጣል ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ከዚህ የጥፋት ውሃ ጥምቀት ውስጥ አዲስ ምድርን ብቅ ሲያደርግ ይታያል፡፡ መገንዘብ የሚገባን ይህችም አዲስ ምድር በደም መጠመቅ ነበረባት፡፡ ኖኅ ከመርከቡ ከወጣ በኋላ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መስዋዕት ማቅረቡ ከጥፋት ውሃ በኋላ ስለ ኖኅ የተጻፈው የመጀመሪያ ጽሑፍ ያስረዳል፡፡ ከአቤል ጋር የተደረገ ከኖኅም ጋር የተደረገው አዲስ ጅማሬ የተከፈተው "ያለ ደም" አልነበረም፡፡ ኃጢአት እንደገና በምድር መስፋፋቱን ሲቀጥል እግዚአብሔር ደግሞ በምድር ላይ የመንግሥቱን ጅማሬ አዲስ መሠረት ሲጥል እናያለን፡፡ በአብርሃም መለኮታዊ ጥሪ እና በይስሐቅ ተአምራዊ ልደት ወይም መወሰድ መሠረትነት እግዚአብሔር እርሱን

የሚያገለግለውን ሕዝብ ሲያዘጋጅ እናያለን፡፡ ይሁን እንጂ ይህም ተግባር ፍጻሜ ያገኘው ያለ ደም አልነበረም፡፡ ስለሆነም በአብርሃም የአምልኮ ሕይወት ዘመን በግልጽ ተንጸባርቆ ታይቷል፡፡ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ወደ ቃል ኪዳን ኅብረት ውስጥ ሲገባ የአብርሃም እምነት በጭንቅ ተፈትሿል፣ ተፈትኗልም፡፡ ስለዚህ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት፡፡ ዘግየት ብሎ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠው የተስፋው ልጅ ይስሐቅ ለእግዚአብሔር ምርኮኛ የሚሆነው በሞት እንደሆነ መማር ስለነበረበት ይስሐቅ መሞት ተገባው፡፡ ለአብርሃምም ሆነ ለይስሐቅ ከግለኝነት ሕይወት መላቀቂያው ብቸኛ መንገድ ሞት ብቻ ነበር፡፡ አብርሃም በመሰዊያው ላይ ይስሐቅን ማቅረብ አለበት ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ግብታዊ ትእዛዝ ሳይሆን ሕይወት ለእግዚአብሔር መስጠት የሚችለው በሞት በኩል ብቻ እንደሆነ የሚያብራራ መስኮታዊ መገለጥ ነበረ፡፡ የኃጢአት ዋጋ የሆነው ሞትን ስናስብ ይስሐቅ ሞቶ የመነሣቱ ጉዳይ የማይታሰብ ነበር ምክንያቱም ሞት ወዲያውኑ ይዞት ጥርግ ይል ስለነበር በዚህ ምክንያት በእርሱ ምትክ በግ ተሰውቶ የእርሱ ሕይወት ሊተርፍ ቻለ፡፡ በሞርያ ተራራ ላይ ደም ፈሰሰና የይስሐቅ ሕይወት ከሞት ተረፈ፡፡ ከእርሱ ወገብ የወጡት ትውልዶች በእግዚአብሔር ፊት በሕይወት መኖር የቻሉት "ያለ ደም" አልነበረም፡፡ በዚያ ደም አማካይነት ይስሐቅ ከሞት እንደተነሣ እንቆጥራለን በዚህ ድርጊታዊ ምሣሌ የምትክነት ትምህርት ተብራርቶ እንመለከታለን፡፡

አራት መቶ አመታት ካለፉ በኋላ ይስሐቅ ሕዝበ እስራኤል ሆኖ ግብጽ ውስጥ ኖሯል፡፡ ከግብጽ ባርነት ነፃ በመውጣት እስራኤል ከሕዝቦች መካከል ለእግዚአብሔር "በኩር" ሆና ተመረጠች፡፡ ይህም እንኳ ሲሆን "ያለ ደም" አልነበረም፡፡ የበኩርነት ምርጫ ምስጢሩ በእግዚአብሔር የመምረጥ ፀጋ ወይም ከአብርሃም ጋር በነበረው የቃልኪዳን ሕብረት አለበለዚያ ጠላቶቻቸውን በቀላሉ መደምሰስ በሚችለው በእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል ሣይሆን የሆነው በደሙ አማካይነት ነበር፡፡

የአህዛብ አባት ለሆነው ለአብርሃም በሞሪያ ተራራ ላይ ደሙ ያደረገው ምን ነበር? ያ ድርጊት በህዝበ እስራኤል ውስጥ መደገም ነበረበት እስራኤላውያን የበራቸውን ጉበንና መቃን በፋሲካው በግ ደም በመርጨት "ደሙን ባየሁ ግዜ ከእናንተ አልፋለሁ" በሚል ጽኑ ቃል የፋሲካ በዓል ሥርዓት ተጀመረ፡፡ ስለዚህ ህዝቡ ሕይወት በምትክ ሞት እንደሚገኝ ታላቅ ትምህርት ተማሩ፡፡ የእነርሱ ሕይወት ሕልውና የሚረጋገጠው በምትካቸው በተሰዋው ሕይወት አማካይነት እንደሆነና ይህም በደም መረጨት ሥርዓት እንደሚከናወን አረጋገጡ፡፡



ከሃምሣ ቀናት በኋላ ትምህርቱ በግልጽ ሲብራራ እናያለን፡፡ እስራኤላውያን አሁን ሲና ተራራ አጠገብ ደርሰዋል፡፡ እግዚአብሔር ህጉን የቃል ኪዳን መሠረት አድርጎ ሰጥቷቸዋል፡፡ ቃል ኪዳኑ መመሥረት ነበረበት፡፡ በዕብራውያን 9:7 ላይ "የሚያቀርበውን ደም ሣይዝ … " በማለት ተብራርቶ ተገልጿል፡፡ የመስዋዕቱ ደም በመጀመሪያ መረጨት ያለበት በመሠዊያው ላይ ቀጥሎ በቃል ኪዳኑ መጽሐፍ ላይ ይረጫል በመጨረሻም "የቃል ኪዳኑ ደም ይኸው" በሚለው በዘፀአት 24:8 መሠረት በህዝቡ ላይ ይረጫል፡፡ የቃል ኪዳኑ ቃል በእግዚአብሔር በኩል ያለውን ሁኔታ ይወክላል፡፡

የቃል ኪዳኑ መሠረትና ኃይል ያለው በዚያ ደም ውስጥ ነው፡፡ ሰውና እግዚአብሔር ወደ ቃል ኪዳን ህብረት መምጣት የሚችሉት በዚያ ደም አማካይነት ብቻ ነው፡፡ ይህም በኤድን ገነት መግቢያ ላይ፣ በአራራት ተራራ ላይ፣ በሞሪያ ተራራ ላይ እና በግብጽ የነገር ጥላ ሲሆኑ በሲና ተራራ ሥር በመደገሙ የነዚህ ሁሉ ማጽኛ ሲሆን እናያለን ያለ ደም ኃጢአተኛ ሰው ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር መቅረቢያ ምንም መንገድ የለውም፡፡

ደሙን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በቀድሞውና በኋለኛው ሁኔታ መካከል ግልጽ ልዩነት አለ፡፡ በሞሪያ ተራራ ላይ በደም መፍሰስ አማካይነት ሕይወት መቤዠትን ሲያገኝ እናያለን፡፡ በግብጽ ደግሞ በበር መቃንና ጉበን ላይ ሲረጭ በሲና ተራራ ላይ ግን በሰዎች ላይ ሲረጭ እናስተውላለን፡፡ ከደሙ ጋር ያለው ግንኙነት እየቀረበ በሄደ ቁጥር በሕይወት ላይ ያለው ኃይል እያየለ ሲሄድ ይታያል፡፡ ቃል ኪዳኑ ከተመሠረተ በኋላ ወዲያውኑ ትእዛዝ ተሰጠ ትዕዛዙም "በመካከላቸው አድር ዘንድ መቅደስ ይስሩልኝ" የሚል ነበር፡፡ (ዘፀ.25:8) የቃል ኪዳኑ እግዚአብሔር በመካከላቸው የመሆኑ ዓላማው ህዝቡ በበረከቱ ሙላት እንዲደሰቱ ነበር፡፡ ከእርሱ ፀጋ የተነሳ እግዚአብሔርን ያገኙታል በቤቱም ያገለግሉታል፡፡

እግዚአብሔር ራሱ ስለሚሰራው መቅደስ አዘገጃጀትና አገልግሎት በጥንቃቄ መመሪያ ሲሰጥ እናያለን፡፡ ልንገነዘበው የሚገባን ዋና ነጥብ ደሙ የዚህ ሁሉ ነገር ምክንያትና ማዕከል መሆኑን ነው፡፡ ወደ ሰማያዊው ንጉሥ በምድራዊው መቅደስ መግቢያ በኩል ስንቀርብ መጀመሪያ የምናገኘው የሚቃጠለው መስዋዕት የሚቀርብበትን የሚታየውን መሠዊያ ነው፡፡ በዚህ የመሠዊያ ላይ ከማለዳ ጀምሮ እስከ ቀትር ድረስ ያለማቋረጥ የመሥዋዕቱ ደም ይረጭበታል፡፡ ወደ ቅድስት ስንገባ ደግሞከወርቅ የተሰራውን ማራኪ የእጣን መሠዊያ እናገኛለን፡፡ እንዲሁም ከዚህ መሠዊያ ጋር ያለ ማለሰለስ የመርጨቱን ደም የሚጋራውን መጋረጃ እዚሁ ሥፍራ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ ቅድስት ስፍራ ወዲያ ምን አለ? ብለን እንጠይቅ

ይሆናል የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነው ቅድስተ ቅዱሳን እዚያ ይገኛል። እግዚአብሔር እንዴት በዚያ ያድራል? እንዴትስ ወደ እርሱ መቅረብ ይቻላል? ብለን እንጠይቅ ለዚህም መልሱ "ያለ ደም" አይቻልም ነው። የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ የሆነው የወርቁ ታቦት እንኳ ሊቀካህኑ የመስዋዕቱን ደም ይዞ እግዚአብሔርን ሊያመልክ በዓመት አንድ ጊዜ ሲገባ ከመርጨት ደም ተካፋይ ይሆናል። እንግዲህ በዚህ አምልኮ ውስጥ ትልቁን ስፍራ ይዞ የምናገኘው "የመርጨት ደም" ነው።

በዚያን ዘመን ኖራችሁ የመጠየቅ እድል ብታገኙ በየትኛውም ጊዜና በማንኛውም ሁኔታ ዋናው ተፈላጊ ነገር ደሙ እንደሆነ ይነገራችኋል። ቤት ለእግዚአብሔር ሲቀደስ፣ ካህናት ለአገልግሎት ሲለዩ፣ ሕፃናት ለእግዚአብሔር ሲሰጡ ፣ ታላላቅ ክብረ በዓላት ሲዘጋጁ፣ በሃጢአት ምክኒያት ልባዊ ዐዐት ሲደረግ ከሃጢአት ለመንጻትና ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ለማድረግ ብቸኛው መንገድ በደሙ በኩል ብቻ ነበር።

ይህ ሥርዓት ለ1500 ዓመታት ያህል ሲከናወን ቆይቷል። ይኸውም በሲና ፣በምድረበዳ ፣በሴሎ ፣ በመቅደስ ውስጥ፣ በሞሪያ ተራራ ላይ እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን ደም በማቅረብ ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር በመንፈስና በእውነት ህብረትን በመመሥረት ጠላትነትን እስካስወገደበት እና እውነተኛውን አካል አዲስ ኪዳንን እስከ መሠረተበት ጊዜ ድረስ ቀጥሎ ኖሯል።

## ጌታችን ኢየሱስ ስለ ደም ምን አስተማረ?

በእርሱ መምጣት አሮጌው ነገር አልፎ ሁሉም አዲስ ሆነ። በሰማይ ከሚኖረው ከአብ ዘንድ ተልኮ መጣና ወደ አብ ስለሚወስደው መንገድ በመለኮታዊ ቃል ነገረን በሕይወቱም ተምሣሌት ሆኖ አሣየን።

በብሉይ ኪዳን ለመኖር "ያለ ደም" እንዳልተቻለ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነግሩናል። ጌታ ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ተናገረ ? መጥምቁ ዮሐንስ ስለክርስቶስ መምጣት ሲናገር ሁለት አገልግሎቶችን እንደሚፈጽም መግለጡን ማስታወስ ተገቢ ነው። መጀመሪያ "የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" አለ። ቀጥሎ " በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ" ሲል ተናገረ። መንፈስ ቅዱስ ከመውረዱ ወይም ከመፍሰሱ በፊት የእግዚአብሔር በግ ደም በቅድሚያ መፍሰስ ነበረበት። ብሉይ ኪዳን ስለ ደም ያስተማረው ይህ ነገር ፍፃሜ ካገኘ በኋላ እርሱን ተከትሎ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ፍፃሜ አግኝቷል።



ጌታ ኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞቱ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዋናው ዓላማ መሆኑን በመግለጽ ተናግሯል። ይኸውም ሕይወት የመዋጀት ጉዳይ ዋና ነገር እንደሆነ አመልክቷል። ከመስቀል ሞቱ ጋር አያይዞ የእርሱ ደም መፍሰስ አስፈላጊነቱን በግልጽ ተናግሯል።

በቅፍርናሆም ምኩራብ ውስጥ ስለራሱ ሲናገር "የሕይወት እንጀራ" ብሎ ነበር። ስለ ሥጋው ሲገልጽ ደግሞ "ስለ ዓለም ሕይወት የሚሰጠው እንጀራ ሥጋው" እንደሆነ ተናግሯል። ከአራት ጊዜ በላይ በአጽንኦት "ደሜን ካልጠጣችሁ በራሣችሁ ሕይወት የላችሁም ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ በማለት ገልጿል። ዮሐ 6፡53-56። ጌታችን ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና የእኛን የጠፋ ሕይወት ወደ ስፍራው ለመመለስ የመምጣቱን መሠረታዊ ዓላማ ተናግሯል። ይህም የሆነው ለእኛ በመሞት ደሙን በማፍሰስ እንዲሁም እኛን የደሙ ኃይል ተካፋዮች በማድረግ እንጂ በሌላ መንገድ አይደለም።

የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ሰው በምትክ ሞት መኖር እንደሚችል በትንሣኤው ደግሞ የዘለዓለምን ሕይወት እንደሚያገኝ ያስተማሩትን ትምህርት ጌታችን ኢየሱስ አጽንቶልናል።

ጌታ ኢየሱስ በምድራዊ ሕይወቱ ማብቂያ ምሽት ላይ ታላቅ መስህብ ያለውን እውነት ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ በመስጠት የመጣበትን ትልቁን ሥራ ከመፈጸሙ በፊት "ስለ ብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ" በማለት የጌታን እራት ሥርዓት መሠረተ። (ማቴ፡ 26፡28) ያለ ደም መፍሰስ የኃጢአት ሥርየት ሊኖር አይችልም። (ዕብ.9፡22) ያለ ኃጢአት ሥርየት ደግሞ የዘለዓለም ሕይወት የለም። ስለዚህ ደሙን በማፍሰስ ለእኛ አዲስ ሕይወትን አመጣልን በሚጠጣው ደሙ የራሱን ሕይወት ለእኛ አካፈለን ስለ ኃጢአት ይቅርታ የፈሰሰው ደሙ እኛን ከኃጢአት እዳ እና ከዘለዓለም ሞት ነፃ አደረገን። ለበደላችን ሥርየት የፈሰሰውን ደሙን በእምነት ስንጠጣ የእርሱ ሕይወት በእኛ ላይ ይቀጠራል እርሱ ስለ እኛ ያፈሰሰው ደሙ ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ የገባና የተሰጠ ነው።

## በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የሐዋርያት ትምህርት

ጌታ ኢየሱስ ከትንሣኤውና ከእርገቱ በኂላ ለሐዋርያት በሥጋው ብዙም አልተገለጠም። ቀደም ሲል በምሣሌነት ተገልጠው የነበሩት ሁሉ አለፉ። ተሸፍነው በምሣሌነት ተጠቅሰው

የነበሩት ጥልቅ መንፈሳዊ እውነቶች ደግሞ ተገለጡ ደሙን የሚጋርደው ነገር አሁን ምንም አናይም። ምክንያቱም ከፍ ያለውን ስፍራ ይዞ የሚገኘው እርሱ ነውና።

ጌታ ኢየሱስ ሲመጣ የሚሻረውን የመቅደስ አገልግሎት የሚገልጸውን የዕብራዊያንን መልዕክት በቅድሚያ እንመልከት። ይህ መልእክት በአጋጣሚ ሳይሆን ሆን ብሎ በዓላማ የተጻፈ ነው።

በየትኛውም ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ ዓላማ በጥልቀት እንዲገለጥ ከተፈለገ የክርስቶስ ደም በቅድሚያ ስለዚህ እውነት አዲስ ነገር እንዲያስተምር መጠበቅ አለብት።

የጌታችን የኢየሱስን ደም በሚመለከት ከዕብራዊያን መልዕክት የሚከተሉትን እናነባለን። "ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ"፣ "የክርስቶስ ደም ህሊናችሁን ያነፃል" (ዕብ. 9:14) "ወንድሞች ሆይ በክርስቶስ ደም ወደ ቅድስት ለመግባት ..." (ዕብ. 10:9) የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሚሆን ወደ ኢየሱስ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል።" (ዕብ.12:24) "ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጪ መከራን ተቀበለ" (ዕብ.13:12-13) "በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነው ጌታችን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው ..." (ዕብ. 13:20)።

በእነዚህ ጥቅሶች አማካይነት የክርስቶስ ደም የመዋጀት ማዕከላዊ ኃይል እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል። "ያለ ደም አልሆነም" የሚለው የዕብራዊያን መልዕክት አባባል በአዲስ ኪዳን የያዘውን ዋጋ ያህል በብሉይ ኪዳንም ይዟል።

ክርስቶስ ሞቶ ስለኃጢአት ያፈሰሰው ደም በእግዚአብሔር በኩል ኃጢአትን ሲከድን በእኛ በኩል ደግሞ አስወግዶልናል።

በሐዋርያው መልዕክቶች ውስጥ ተመሣሣይ ትምህርት ሰፍሮ እናገኛለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ላይ "በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነትም በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተሰሪያ አድርጐ አቆመው" (ሮሜ 3:24-25) "አሁን በደሙ ከፀደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን" (ሮሜ 5:9)። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተክርስትያን በፃፈው መልእክቱ ሲገልጽ "የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ህብረት ያለው አይደለምን?" ብሏል።



በገላትያ መልዕክቱ ላይ "መስቀል" የሚለውን ቃል በመጠቀም ተመሣሣይ ሐሳብን ለማስተላለፍ ሲሞክር ይታያል። በቆላስያስ መልእክቱ ደግሞ ሁለቱንም ቃላት በማዋሃድ "የመስቀሉ ደም" ይላል (ገላ. 6:14) እና (ቆላ. 1:20) ተመልከቱ።

የኤፌሶንን ቤተክርስትያን እንዲህ ሲል ያሳስባቸዋል። "በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን" የሚለውንና "በክርስቶስ ደም ቀረብን" የሚለውን በቅደም ተከተል እናነባለን (ኤፌ. 1:7፣2:13)።

ጴጥሮስም በበኩሉ ለመልዕክቱ ተቀባዮች "በክርስቶስ ደም መረጨት ለመታዘዝ መመረጣቸውን" ያሳስባቸዋል (1ጴጥ.1:2) ይኸውም "በክርስቶስ ክቡር ደም" መዋጀታቸውን ያረጋግጥላቸዋል (1ጴጥ.1:19)

ሐዋርያው ዮሐንስ በመንፈስ ሕፃናት ለሆኑት ልጆቹ "የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል" (1ዮሐ.1:7) የሚለውን ሃሳብ ይገልጽላቸዋል። በተጨማሪም "ልጁ በውሃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ክርስቶስ ነው (1ዮሐ. 5:6) በማለት ሲያጸናላቸው እናያለን።

እነዚህ ሁሉ ፀሐፊዎች ደሙን በመግለጽ እና በውስጡም ያለውን ክብር በማሣየት ረገድ ይስማማሉ። በክርስቶስ የደሙ ኃይል የሚገኘው ውስጣዊ መዋጀት የሚረጋገጠው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። ይህ ምናልባት የምድራዊው ቋንቋ አገላለጽ በሰማያዊው ቋንቋ ሲገለጽ እንዴት ይሆን?

## ደምን በተመለከተ የራዕይ መጽሐፍ ምን ይላል

የዙፋኑ ክብር እና በዙሪያው ያሉትን መባረክ የተገለጠበትን ይህን የራዕይ መጽሐፍ ስንመለከት ደሙ አሁንም ከፍ ያለውን ስፍራ ይዞ መቀጠሉን እናስተውላለን።

ዮሐንስ ኢየሱስን "በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየው" (ራዕይ 5:6)። ሽማግሌዎቹ በበጉ ፊት ተደፍተው እየሰገዱ "ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው (ራዕ. 5:8-9)" የሚለውን አዲስ ዝማሬ ይዘምራሉ።

እኛም "ደሙ ደሙ የክርስቶስ ደሙ፣ሕይወት ያለበት ነው ደሙ የሰይጣንን ምሽግ የሚያፈራርስ ነው ደሙ" እያልን እንዘምራለን።

ቀጥሎ ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል ታላቅ ሠራዊት ባየ ጊዜ እነዚህ እነማን ናቸው? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ "እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ልብሳቸውን በበጉ ደም አጥበው አነጹ" የሚል መልስ ተሰጠው። ከዚያም በሰይጣን መሸነፍ ምክንያት የሚዘመረውን የድል ዝማሬ ሰማ ዝማሬውም "እነርሱም ከበጉ ደም የተነሳ ከምስክርነታቸውም ቃል የተነሳ ድል ነሱት" (ራእይ 12፡11) የሚል ነው። ዮሐንስ በራዕይ እንዳየው የመንግሥተ ሰማይን ክብር የእግዚአብሔርን ታላቅ ዓላማ ፍፃሜ፣ የእግዚአብሔርን ልጅ አስደናቂ ፍቅር፣የትንሣኤውን ኃይል፣ "የበጉ ደም" እያሉ ሐሴትና ምስጋናቸውን በዝማሬ የሚያቀርቡትን የተዋጁትን ታላቅ ሠራዊት ደስታ መግለጫ ቃላት አላገኘለትም።

## ከቅዱሳት መጻሕፍት የምንማራቸው ትምህርቶች

ከመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ እስከ መጨረሻው ከኤድን መግቢያ መዘጋት እስከ ሰማያዊቱ ጽዮን መግቢያ መከፈት በመጻሕፍት ሁሉ የዘለቀ አንድ ወርቃማ ገመድ አለ። እርሱም መጀመሪያውንና መጨረሻውን ያያያዘ እና አንድ ያደረገ ደም ነው። ይኸውም ኃጢአት አውድሞት የነበረውን የሰው ክብር እንደገና ወደ ስፍራው የመለሰ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደሙ ከፍ ያለ ስፍራ እንዳለው ስንመለከት እግዚአብሔር ምን ዓይነት ትምህርት መማር እንዳሰብን እንደፈለገ መገንዘብ ከባድ አይሆንም።

## ኃጢአትን የማሸነፊያ ብቸኛው መንገድ

እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚያስወግድበትና ኃጢአተኛውን የሚያድንበት መንገድ ከደሙ ሌላ የለውም። በኃጢአት ላይ ድል ለመቀዳጀትም ሆነ ኃጢአተኛውን ለማዳን ከክርስቶስ ደም በቀር እግዚአብሔር ሌላ መንገድም ሆነ ሐሳብ የለውም። አዎን ይህ በእርግጥ ከመረዳት በላይ የሚያልፍ ነገር ነው።

ትኩረት የሚያስፈልጋቸው አስደናቂ ጸጋዎች ብዙ ናቸው። ቃል ሥጋ ሆኖ ፍቅሩን ለእኛ የገለጠው እንዲሁ ሳይሆን ራሱን በፈቃዱ ለሞት ምርኮኛ አድርጎ በመስጠት ነው። የኢየሱስ ጽድቅ የኃጢአት ቅጣት እስካልተከፈለ ድረስ ለኃጢአተኛው የኃጢአት ይቅርታ ሊያስገኝለት አይችልም። ጻድቁ ምትካችን ሆኖ ኃጢአታችንን በማስተሰረይ ለኃጢአተኞች የኃጢአትን ሥርየት እና የኃጢአተኛውን ጽድቅ አመጣ በቅድስናና በመንጻት ከእግዚአብሔር



ጋር የታደሰ ኅብረት ማድረግ ስንችል ይህ ኅብረት እንድንደሰት ያደርገናል። ደሙን በመጠጣት ከክርስቶስ ጋር የሚኖረን የሕይወት አንድነት ዘለዓለማዊ ደስታችንን "በደምህ ለእግዚአብሔር ዋጀኸን" በሚል የምስጋና ዝማሬ እንድንገልጽ ያስችለናል እነዚህ ድንቆች ሁሉ ከክቡር የክርስቶስ ደም በእኛ ላይ የበሩ የአስደናቂ ፍቅሩ ነጸብራቅ ውጤቶች ናቸው።

## ስለ ደሙ ትክክለኛ አመለካከት

ደሙ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ያህል በእኛም ልብ ውስጥ ስፍራ ሊኖረው ይገባል። እግዚአብሔር ከሰው ጋር መጀመሪያ ግንኙነት ማድረግ ከጀመረበት ጊዜ እና ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት በዚያ ደም እጅግ ተደስቷል ልቡም ረክቷል። እኛም በዚያ ደም ክብርና ኃይል መራመድ ባንማር የልብ እረፍት አናገኝም ድነትም የለንም።

ኃጢአተኛን በኃጢአቱ አዝኖ መጸጸቱ ብቻ የኃጢአትን ይቅርታ አያመጣለትም። እግዚአብሔር እንኳን በፀጋው ዙፋን ላይ ተቀምጦ የምስክሩ ደም ሁልግዜ በፊቱ እንደሆነ ሁሉ የተዋጀውም ሰው እንዲሁ ልምምድ ሊኖረው ያስፈልጋል። ከክርስቶስ ደም በቀር ወደ እግዚአብሔር እኛን በማቅረብ የእርሱን ፍቅር፣ሃሴትና ክብር እንድንለማመድ በዚያም ጸንተን መኖር የምንችልበትን ትክክለኛ አመለካከት ሊፈጥርልን የሚችል ምንም ነገር የለም።

## የደሙ በረከትና ኃይል

የደሙን ሙሉ በረከትና ኃይል መማር እንድንችል እሰኪ ጊዜና ትኩረት ሰጥተን እንመልከተው። የክርስቶስ ደም የዘላለማዊነት ታላቅ ኃይና የመለኮት ጥበብ ጥልቅ ምስጢርም ነው። ትርጉሙን በቀላሉ እንደምንረዳው አድርገን ማሰብ የለብንም እግዚአብሔር ራሱ የደሙን በረከትና ኃይል ለመግለጽ ለ 4000 ዓመታት ያህል ሰዎችን ሲያዘጋጅ ኖሯል። እኛም ጊዜ ወስደን በጥንቃቄ ልንመረምረው ይገባናል።

ትርጉም ያለው እና ውጤታማ የሆነ ጊዜ ካልወሰድን እንዲሁ በእግዚአብሔር ፊት መቀመጥ ብቻውን ዋጋ የለውም። የመስዋዕቱ ደም ማለት መሠረታዊ ትርጉሙ ሕይወት ማቅረብ ማለት ነው። እስራኤላዊ የሆነ ማንኛውም ሰው በምትኩ መስዋዕት የሚሆንለትን ሕይወት እስካላቀረበ ድረስ ደም ከየትም ሊያመጣ አይችልም። ጌታ ኢየሱስ እኛን ዋጋ ከመክፈል ነፃ አድርጎ ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ አልሰጠም ደሙንም አላፈሰሰልንም በፍፁም ይህን አላደረገም በአንጻሩ ግን የእኛን ሕይወት መስዋዕት መሆን የሚችልና ዋጋ ያለው አደረገው እንጂ።

በደሙ ውስጥ ያለው ስውር ዋጋ ግላዊ የመስዋእትነት መንፈስ ነው። በተጨማሪም ያ ደም ሐሳብን ወይም አእምሮን በሚነካበት ጊዜ ግላዊ መስዋዕት የመሆንን መንፈስ ያመጣል። ደሙ ባስገኘልን በአዲሱ ሕይወት ሙሉ ኃይል ውስጥ ማለፍ ከፈለግን ማንነታችንንና የገዛ ሕይወታችንን ሳይቀር መተውን መማር አለብን።

እነዚህን ነገሮች ከእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ለመረዳት እንዲያስችለን ጊዜአችንን መስጠት ይኖርብናል። ራሣችንን ከኃጢአት፣ከዓለማዊ አስተሳሰብ፣ከፈቃዳችን ነፃ ብናደርግ የደሙ ኀይል እንዳይሰራ እንቅፋት የሚሆንበት ነገር አይኖርም። ደሙም በዋነኝነት እነዚህን እንቅፋቶች ማስወገድ ይፈልጋል።

የደሙን በረከትና ኃይል ስናስብ በራሣችን ሃሳብ መያዝ የለብንም። ሕይወታችንንም እንደ ሽልማት ልንቆጥር አይገባንም። ይልቁንም በእርሱ መስዋዕትነት ከመጠቅለል የበለጠ ሊያድነን የሚችል እንደሌለ አውቀን ራሣችንን በጸሎትና በእምነት ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ምርኮኛ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህን ስናደርግ በደሙ ያዘጋጀልንን የከበረና የተባረከ ሕይወት ይገልጥልናል።

## የደሙ ኃይል መገለጥ

ጌታ ኢየሱስ የደሙን ኃይል እንዲገልጥልን በእርሱ ልንታመን ያስፈልጋል። በእርሱ ላይ ባለን ሙሉ መታመን በደሙ የተገኘው በረከት የእኛ ይሆናል። ደሙን ካፈሰሰልን እና ስለ እኛ ደሙን በማቅረብ ሊያማልድ ዘለዓለም ከሚኖረው ከታላቁ ሊቀ ካህን በሃሳባችን ደሙን ከእርሱ ልንለይ አይገባንም።

አንድ ጊዜ ደሙን ለእኛ ያፈሰሰልን ጌታ ያለ ጥርጥር በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ውጤቱንም በመግለጥ ሊያስተምረን ይችላል። ይህም ሲሆን የጠለቀ መንፈሳዊ መረዳትን በመስጠት ዓይኖቻችንን ሊከፍትልን እንደሚችል ልንታመንበት ይገባል። እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ደም እንደሚያስብ እኛም ማሰብ እንድንችል ሊረዳንና የደሙን ኃይል ሊገልጽልን በሕይወታችንም እውን ሊያደርገው ውጤቱንም እንድናየው ሊረዳን እንደሚችል እንታመንበት።



# ምዕራፍ ሁለት

## በደም መዋጀት

"ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ" 1ጴጥ. 1:18-19።

የክርስቶስ ደም መፍሰስ በመስቀል ላይ የመስቃየቱ ትልቁ ምልክት ነው። የኃጢአት ስርየት ፍሬ ደግሞ ያለው በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደም ውስጥ ነው። አማኝ የተዋጀበትን የደሙን ክብር እና በረከት ሳይረዳ መቀበሉ የተሟላ እርካታና እፎይታ አይሰጠውም። ነገር ግን ምርኮኛ ለሆነች ነፍስ ደሙ ወደ አስገኘላት ሙሉ መረዳትና ኃይል መምጣቷ የሚሰጣት በረከት የሚነገር አይደለም።

ከቅዱስ ቃሉ እንደምንረዳው ደሙ ያስገኘልን በረከቶች ብዙ እና የተለያዩ ናቸው።

- *በደሙ በኩል መታረቅን አገኘን*
- *በደሙ በኩል መንፃትን አገኘን*
- *በደሙ በኩል መቀደስን አገኘን*
- *በደሙ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትን አገኘን*
- *በደሙ በኩል በሰይጣን ላይ ድልን ተቀዳጀን*
- *በደሙ በኩል ሕይወትን አገኘን*

በደሙ የተገኙ የተለያዩ ዓይነት በረከቶች እሉ ሁሉንም የሚያጠቃልላቸው ሃሳብ "በደም መዋጀት" የሚለው ነው"። አንድ አማኝ እነዚህ በረከቶች ምን እንደሆኑ ሲረዳና በምን መንገድ የራሱ እንደሚሆኑ ግንዛቤ ሲያገኝ የዚያን ጊዜ የመዋጀትን ሙሉ ኃይል መለማመድ ይጀምራል።

እነዚህን የተለየዩ በረከቶች ጠለቅ ብለን ለመገንዘብ ከማለፋችን በፊት የጌታ የኢየሱስን የደሙን ኃይል በተመለከተ አጠቃላይ የሆኑትን ነገሮች በቅድሚያ እንመልከት።

በመጀመሪያ የደሙ ኃይል ያለው ምን ውስጥ ነው? ሁለተኛ የደሙ ኃይል ያከናወነው ነገር ምንድን ነው? እኛስ በረከቱን መለማመድ የምንችለው እንዴት ነው?

## የደም ኃይል ያለው ምን ውስጥ ነው?

ለክርስቶስ ደም ታላቅ ኃይል የሰጠው ነገር ምንድን ነው? በተጨማሪም በሌላ ነገር ውስጥ የሌለ በደም ውስጥ ብቻ ይህን የመሰለ ኃይል እንዴት ሊሆን ቻለ?

ለእነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ማግኘት የምንችለው ዘሌዋውያን 17 ቁጥር 11 እና 14ን ያነበብን እንደሆነ ነው። ቃሉም "የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነው።" "በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተሠሪያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት" ይላል። ምክንያቱም ይህ ነው ነፍስ ወይም ሕይወት ያለው በደም ውስጥ ነው። ደሙ ደግሞ ለእግዚአብሔር በመሰዊያ ላይ ይቀርባል ስለዚህ የመዋጀት ወይም ነፃ የማውጣት ኃይል ይኖረዋል ማለት ነው።

## ሕይወት ያለው በደም ውስጥ ነው

የደም ዋጋ የሚተመነው ደሙ ላለበት ሕይወት በሚሰጠው ዋጋ ነው። ለምሣሌ የበግ ወይም የፍየል ሕይወት ዋጋ ከበሬ ዋጋ ያንሣል። የፍየል ወይም የበግ ደም ለመስዋዕት ከቀረበ ከበሬ ደም ዋጋ ያነሰ ደም ለመስዋዕት ቀርቧል ማለት ነው። (ዘሌ. 4፡3፣14፡27) ይመልከቱ ከብዙ በጎች፣ ፍየሎችና በሬዎች ሕይወት ይልቅ የሰው ሕይወት ትልቅ ዋጋ አለው።

ይህ እንዲህ ከሆነ የክርስቶስን የደሙን ዋጋ እና ኃይል ምን ያህል እንደሆነ ማን መናገር ይችላል? በዚያ ደም ውስጥ ደግሞ የቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነፍስ ይኖርበታል። የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ሕይወት በዚያ ደም ውስጥ አለበት። የደሙ ኃይል ከብዙ ዋጋዎቹ ጋር ከእግዚአብሔር ዘለአለማዊ ኃይል የሚተናነስ አይደለም። የደሙን ሙሉ ኃይል ለመለማመድ ለወሰኑ ሁሉ ይህ እንዴት የከበረ ሐሳብ ነው!

## ለእግዚአብሔር በመሰዊያ ላይ ይቀርባል

የደሙ ኃይል ከሁሉም ነገር በላይ ሆኖ ለኃጢአት ማስተሰሪያ በመሰዊያ ላይ ለእግዚአብሔር ይቀርባል። ስለ ደም መፍሰስ ስናስብ ሞትን ደግሞ እናስባለን ደም ወይም ነፍስ ሲፈስ የሚከተለው ሞት ነውና። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የኃጢአት ማስተሰሪያ አድርጐ በመሰዊያ ላይ ደምን ሰጣቸው። ይህም ማለት የኃጢአተኛው ኃጢአት የሚሰዋው



እንስሳ ላይ እንደተላለፈ ይታሰብና እንስሳው በኃጢአተኛው ምትክ ይሞታል። ለሕጉ መንፃትና ለእግዚአብሔር ትእዛዝ መፈጸም ሲባል ደም ሕይወት

እስኪያልፍ ድረስ ይፈስሳል። ኃጢአት በውስጥ ታዋቂ ስለሚከደንና ስለሚሰረይ በኃጢአተኛው ላይ ከዚያን በኂላ አይቆጠርበትም ይቅር ተብሏልና።

ጌታ ኢየሱስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ እነዚህ ሁሉ መስዋእቶች ምሣሌ እና ጥላ ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል። የክርስቶስ ደም ግን የእነዚህ ምሣሌዎች እውነተኛ አካል ሆኖ ተገልጧል።

የክርስቶስ ደም በራሱ የማይመጠን ዋጋ አለው። ምክንያቱም በደሙ ውስጥ የክርስቶስን ነፍስ ወይም ሕይወት በመያዙ ነው ከፈሰሰበትም ዓላማ የተነሣ ደሙ የማይወሰን የማስተሰርይ ኃይል አለው። ጌታ ኢየሱስ ይህንን እውን ያደረገው ለአባቱ ፈቃድ በመታዘዝ በአዳም የተጣሰውን ትዕዛዝ በቅጣት የከፈለው ደሙን በማፍሰስ እና ራሱን ለሞት አሣልፎ በመስጠቱ ነው። በእርሱ ሞት ቅጣት ብቻ አልተፈጸመም ሕጉም ተሟልቷል አብም በውጤቱ ረክቷል። ደሙ ለኃጢአት ማስተሰሪያነት በመፍሰሱ ኃጢአትን ኃይል አልባ ሊያደርገው ችሏል። ደሙ ኃጢአተኛውን አንጽቶና ቀድሶ ኃጢአትን ለማስወገድ ኃጢአተኛውን ወደ ሰማይ ለማስገባት የተገለጠው በአስደናቂ ኃይሉ ነው።

ደሙን ካፈሰሰው ድንቅ ጌታ የተነሳ እና ደሙም ከፈሰሰበት ታላቅ ዓላማ የተነሳ የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ በማርካት ሕጉ እንዲሟላ ተደረገ። የኢየሱስ ደም እርሱም የሥርየቱ ደም ይህን የመሰለ አስደናቂ ኃይል አለው ደሙ ያስከተለው የመዋጀት ኃይል ለኃጢአተኛው ድነት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ አሟልቶለታል።

## የደሙ ኃይል የፈጸመው ነገር ምንድን ነው?

ደሙ ያከናወናቸውን አስደናቂ ነገሮች ስንረዳ በእኛም ሕይወት ተመሣሣዩን ነገር ሊፈጽም እንደሚችል በማመን እንበረታታለን። ቅዱሳት መጻሕፍት በክርስቶስ የደሙ ኃይል የተከናወኑ ታላላቅ ነገሮችን በመያዛቸው እንዴት የከበሩ እንደሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።

## ደሙ መቃብርን ከፈተ

በዕብራውያን 13፡20 ላይ "በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያወጣው የዘለዓለም አምላክ..." የሚለው ቃል የጌታ

የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ኃይል ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው ያለ ደሙ አልነበረም። የጌታ ኢየሱስ የትንሣኤው ኃይል የተከናወነው በአስደናቂው የደሙ ኃይል መሆኑን ያረጋግጣል።

ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ የሰውን ኃጢአት ወስዶ በሥጋው ለመሸከም ነበር። እንደ ሰው ከሞት በመነሣት የዘለዓለም ሕይወት በትንሣኤ የመቀዳጀት መብት ያገኘው በፈሰሰው በራሱ የደም ኀይል ብቻ ነበር። ደሙ ሕግንና የእግዚአብሔርን ጽድቅ ማሟላት በመቻሉ የኃጢአትን ኃይል በመስበር ኃጢአትን ዋጋ ቢስ አደረገው። የኃጢአት መውጊያ ሲሰበር ሞትም ተሸናፊ ሆነ። በሞት ላይ ሥልጣን የነበረው ዲያብሎስም ተሸነፈ በዚህ ምክንያት በእኛ ላይ ያለውን ሥልጣን ሁሉ አጣ የክርስቶስ ደም የሞትን የሰይጣንንና የሲኦልን ኃይል ድል ነሳ መቃብርንም ከፈተ። በእርግጥ ያመነ ሁሉ በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ኃይልና በደሙ መካከል ያለውን የቅርብ ትስስር በሚገባ ይገነዘባል። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነቱን ለኃጢአተኛ ሰው የገለጠበት ብቸኛ መንገድ ደሙ ነው። ደሙ ባለበት በዚያ የእግዚአብሔር የትንሣኤው ኃይል ወደ ዘለዓለም ሕይወት መግቢያ በሩን ይከፍታል። ደሙ የሞትንና የሲኦልን ኃይል ወደ ፍጻሜ ማምጣት ችሏል። የክርስቶስ ደም የፈጸመው ነገር ከሰው መረዳት በላይ ነው።

## የክርስቶስ ደም ሰማያትን ከፈተ

በዕብራውያን 9፡12 ላይ "ክርስቶስ የዘለዓለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ" የሚለውን ቃል እናነባለን።

በብሉይ ኪዳን የመገናኛ ድንኳን የተገለጠው የእግዚአብሔር መገኘት ከመጋረጃው በስተጀርባ እንደነበር እናውቃለን ያንን መጋረጃ አልፎ መሄድ የደፈረ ወይም መጋረጃውን ማስወገድ የቻለ የሰው ኃይል አልነበረም። መጋረጃውን አልፎ ወደ ውስጠኛው ክፍል መግባት የሚችለው በዓመት አንድ ጊዜ ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበር። ይህም ሲሆን ደም ሳይዝ አይገባም አለበለዚያ የራሱን ሕይወት ያጣል መጋረጃው በሥጋ ላይ ተገልጦ ከእግዚአብሔር የለያየን የኃጢአት ምሣሌ ነበር። የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ጽድቅ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንዳንገባ ስለ ከለከለን ማንም ሥጋ የለበሰ ወደ እርሱ መቅረብ አልተቻለውም።

አሁን ግን የእኛ ጌታ በቁሣዊ ነገር ሣይሆን በእውነተኛ መቅደስነት ተገለጠ። እንደ ሊቀካህንና የራሱን ሕዝብ እንደሚወክል ሆኖ ስለ አዳም ኃጢአተኛ ልጆች በገዛ ደሙ ወደ ቅዱሱ እግዚአብሔር መገኛ መግቢያ ሲጠይቅ ይታያል። "እኔ ባለሁበት በዚያ እነርሱ ደግሞ



ይሆናሉ" የሚለው የእርሱ ጥያቄ ነው። ሰማይ በእርሱ ለሚያምን ኃጢአተኛ ሁሉ እንዲከፈትለት ጠየቀ ጥያቄው ዋስትና ያለው ነው ይህ ግን እንዴት ሊሆን ቻለ? ይህም የሆነው በደሙ አማካይነት ነው። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር መገኛ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በገባ ደሙ ገባ የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ሰማያትን ከፈተ።

የጸጋው ዙፋን ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖረው በደሙ አማካይነት ነው። (ዕብ. 12፡22-24) ከተጠቀሱት በሰማያት ካሉት ሰባት እውነታዎች መካከል የሁሉም ዳኛ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር እና የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሆነው ወደ ኢየሱስ መቅረብ የተቻለው መንፈስ ቅዱስ እንደሚነግረን "የመርጨት ደም" ከፍ ያለና መካከለኛ ስፍራ ስለተሰጠው ነው።

ሰማያት ለኃጢአተኞች መከፈቱን እና ልክ የሌለው በረከት ከሰማይ ወደ ምድር መለቀቁን መንፈስ ቅዱስ ደጋግሞ ይነግረናል። ይህ የሆነው መካከለኝነቱን ሳይለቅ በሚሰራው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም አማካይነት ነው። የጸጋው ዙፋን ዘለዓለማዊ ህልውናውን አግኝቶ የሚኖረው በዚያ ደም ኃይል ነው።

የክርስቶስ የደሙ ኃይል እንዴት የሚያስደንቅ ነው! የሲኦልንና የመቃብርን ደጆች ሰብሮ እኛን ከኢየሱስ ጋር እንድንወጣ አደረገን። እንዲሁም የሰማይን ደጆች ከፍቶ እኛን ከእርሱ ጋር እንድንገባ አደረገን። ደሙ በታች ባሉት በጨለማው መንግሥትና በሲኦል ላይ ብርቱ ኃይል አለው። በላይ ባለው በመንግሥተ ሰማይና በክብሩም ላይ ኃይልን የሰበሰ ነው።

## በሰው ልብ ውስጥ ባሉ ኃያል ነገሮች ሁሉ ላይ

ደሙ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሰይጣን ላይ በኃይል ተገልጦ ከዚያ ይልቅ በሰው ላይ በኃይል ባይገለጥ እንግዲያውስ ደሙ የፈሰሰው ለማን ሲል ነው? ስለዚህ ነገር ሁላችን መልስ ልንሰጥ ያስፈልጋል።

የደሙ አስደናቂ ኃይል የተገለጠው በተለይ በምድር ላይ ለሚኖሩ ኃጢአተኞች ሲባል ነው። ይህን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተሰጡት ብዙ ምንባቦች 1ኛጴጥ. 1፡18-19 ልዩ አጽንኦት ይሰጣል። ቃሉም "ከከንቱ ኑሮአችሁ... በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ" ይላል።

"መዋጀት" የሚለው ቃል ጥልቅ ትርጉም ያለው ነው። ይኸውም በመግዛት ወይም ነፃ በመውጣት ከባርነት መላቀቅን የሚያመለክት ቃል ነው። ምክንያቱም ኃጢአተኛው ጠላት

በሆነው በሰይጣን ኃይል ሥር፣ከሕግ እርግማን ሥር እና ከኃጢአት ኃይል በታች ባርያ ነው። ስለዚህ "በደም ተዋጅተሃል" የሚለው አዋጅ ሲታወጅለት ያስፈልገዋል። ይህም ደም ተራ ደም ሳይሆን የኃጢአትን ዕዳ መክፈል የቻለ የሰይጣንን ኃይል የደመሰሰ እርግማንን እና ኃጢአትን ያወደመ ብርቱ ኃይል ነው።

ይህ አዋጅ በሚነገርበትና ተቀባይነት በሚያገኝበት ሥፍራ ሁሉ ከከንቱ ኑሮ እና ከኃጢአት ሕይወት መዋጀት እውነተኛ ሥራውን ይፈጽማል። መዋጀት የሚለው ቃል እግዚአብሔር የኃጢአተኛውን ዕዳ ከመክፈል ጀምሮ እስከ ሙሉ ነፃ መውጣት ድረስ ያለውን የሥጋ ትንሣኤ የሚያጠቃልል ሰፊ ትርጉም አለው (ኤፌ.1፡4፣4፡30 ፤ሮሜ.3፡23-24)

ጴጥሮስ ለመልእክቱ ተቀባዮች "በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት" በማለት ጽፎላቸው እንመለከታለን (1ኛጴጥ.1፡2)። ይህ ክፍል የክርስቶስ ኢየሱስ ክቡር ደም ልባቸውን በመንካት ወደ ንሥሐ እንዳመጣቸው እምነታቸውንም በውስጣቸው እንዳነሳሳ ነፍሳቸውን በሕይወትና በሐሴት እንደሞላ የሚያረጋግጥ ክፍል ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ የአስደናቂው የደሙ ኃይል ታላቅ ሥራ ውጤት ነው ማለት ነው። በተጨማሪም ጴጥሮስ የክርስቶስን ክቡር ደም ዋናው መሠረቱ በማድረግ ለቅድስና ሕይወት ጥሪ ሲያደርግላቸው እናያለን። ስለሆነም ትኩረታቸውን በደሙ ላይ እንዲያደርጉ አጥብቆ ይገፋፋቸዋል።

የራሱን ጽድቅ ለመሥራት ለሚታገለውና ክርስቶስን ለሚጠላው የአይሁድ ሕዝብ ለሃይማኖተኛው እና ለአምላክ የለሹ ከኃጢአት ኃይል መዳኛ አንድ ብቸኛ መንገድ አለ ይኸውም ኃጢአተኞችን በየእለቱ ማዳን የሚችለው የኢየሱስ ክቡር የደሙ ኃይል ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ ሊኖረን ይችላል። ይህ የሚሆነው ደሙ በሰማይና በሲኦል ኃይላት ላይ ኃያል እንደሆነ ሁሉ በኃጢአተኛው የሰው ልብ ውስጥም እንዲሁ ኃያል ነው። የደሙን ኃያልነት መረዳት የማይቻል ወይም የማይሆን አድርገን ማሰብ የለብንም በተጨማሪም ያለ እምነት ሆነን ከክርስቶስ ደም ምንም ልንጠብቅ አይገባንም።

## ይህ ኃይል እንዴት ይሰራል ?

ይሄ ሶስተኛው ጥያቄአችን ነው። የደሙ ኃይል ያለ ምንም እንቅፋት በእኛ ውስጥ የታቀደውን ውጤት ማምጣት የሚችለው በምን ዓይነት ሁኔታ እና ክንውን ውስጥ ነው?



## ኃይሉ በእምነት ውስጥ ይሰራል

ከላይ ለቀረበው ጥያቄ መልስ የሚሆነን የትም ስፍራ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የደሙ ኃይል የሚሰራው በእምነት ነው። ነገር ግን እምነት በስፋት የሚደገፈው በእውቀት ላይ ነው ደሙ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ያልተሟላ ዕውቀት ካለ እምነት አናሳ ስለሚሆን የደሙን ኃይል ትልቅ ውጤት መጠበቅ አዳጋች ይሆናል። ዛሬ የብዙ ክርስትያኖች እምነት በደሙ በኩል በእምነት የኃጢአታቸውን ሥርየት ከተቀበሉ ስለ ደሙ ሥራ በቂ ዕውቀት እንዳላቸው አድርገው ያስባሉ። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል መረዳቱ የሌላቸው ናቸው። ሰዎች በቃላት ዕውቀት ብዛት የበለጸጉ ቢሆኑ እና ከአእምሮ በላይ የሆነ የንግግር ችሎታ እንኳ ቢኖራቸው የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ከሌላቸው እግዚአብሔር በሙላት ሊጠቀምባቸው አይችልም።

መንፈስ ቅዱስ በደም ስለመንጻት የሚናገረውን ታላቅ በረከት ስለማያስተውሉ እንደ ቀላል ነገር ቆጥረውት ሊያልፉ ይችላሉ። የቃላት እውቀትና የንግግር ችሎታ የሰው ጥበቦች ስለሆኑ የክርስቶስ ክቡር ደም ለነፍስ የሚሰጠውን ሰማያዊ ኃይል እና ከአእምሮ በላይ የሆነውን ክብር ለመግለጥ ብቃት የላቸውም። ስለ ደሙ ኃይል ያለን አናሳ እውቀት የጠለቀውን እና ፍፁም የሆነውን የደሙን በረከት እንዳንገልጥ ይከለክለናል።

ደሙ ያደረገልንን ነገር ከልባችን አስተውለን በመገንዘብ እምነታችን ሊበረታ ይችላል። ስለ እምነት ታላቅነት መንግሥተ ሰማይና ሲኦል ምስክሮች ናቸው። በእግዚአብሔር የተሰፋ ሙላት ልምምድ ውስጥ እምነት ያድጋል። የሚያነጻውና ሕይወት የሚሰጠው ኃይል በታላቅ በረከት ፈጥኖ እንዲገለጥልን ወደ ምንጩ ጠልቀን ለመግባት ከልባችን መፈለግ አለብን።

በደሙ መጠመቅ ከክርስቶስ ጋር ወዳለው የጠበቀ ህብረት ሲያስገባን ለመንፃት ራሣችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ያደርገናል። የክርስቶስ ደም "ከኃጢአትና ከርኩሰት የሚያነጻ ምንጭ" ተብሎ ተጠርቷል(ዘካ.13፡1)። እርሱም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት ከሰማያዊው መቅደስ ውስጥ ይመነጫል። በእምነት ወደዚህ ሰማያዊ ምንጭ ራሴን አስጠጋለሁ ምርኮኛም አደርጋለሁ እንዲሸፍነኝም በውስጤም እንዲፈስ እፈቅድለታለሁ በዚህ ምንጭ ውስጥ እገባለሁ ይህን ካደረግሁ የሚያበረታ ኃይሉንና ማንጻቱን ሊከለክለኝ የሚችል ነገር የለም። ከሚታየው ነገር ፊቴን መልሼ በውስጥ ሕይወቴ የተባረከውን ኃይሉን መግለጥ ወደሚችለው የክርስቶስ ደም ወደሚወከለው መንፈሳዊ ምንጭ ፊቴን በእምነት አዞራለሁ።

እንግዲህ አስደናቂውን የደሙን በረከት ለመቀበል እንደ እግዚአብሔር ልጆች ፀንተን ልባችንን በእምነት እንክፈት::

## መንፈሱ እና ደሙ

ደሙ ኃይሉን እንዲገልጥ ሌላው አስፈላጊ ነገር ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ደሙን ከመንፈሱ ጋር ያያይዘዋል:: መንፈስ ቅዱስ በሚሠራበት ጊዜ የደሙ ኃይል ደግሞ ይገለጣል::

“የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሶስት ናቸውና ሶስቱም በአንድ ይስማማሉ” የሚለውን ቃል በ1ኛዮሐ.5፡8 ላይ እናነባለን:: ሶስቱም በየራሣቸው ትርጉም አላቸው:: ውኃው ለንሥሐ ጥምቀትንና ከኃጢአት መለየትን ያመለክታል፣ ደሙ ደግሞ በክርስቶስ መዋጀትን ይመሰክራል፣ ለውሃውና ለደሙ ኃይል የሚሰጣቸው መንፈሱ ነው:: የዕብራውያን ጸሐፊም በመንፈሱና በደሙ መካከል ያለውን ትስስር “በዘለዓለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያው እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ህሊናችሁን ያነፃ ይሆን” በማለት ይገልፃል:: (ዕብ.9፡14) በጌታችን በኢየሱስ ውስጥ ደሙ ዋጋ እና ኃይል ያገኘው በዘለዓለም መንፈስ ነው:: ደሙ በሰማይና በሰዎች ልብ ውስጥ ሕያው ርስትን ወራሽ የሆነው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው::

ደሙና መንፈሱ ሁልግዜ ተስማምተው ይመሰክራሉ:: ሰዎች በደሙ ላይ ጽኑ እምነት ሲኖራቸውና ደሙን ማዕከል ያደረገ ስብከት ሲሰበክ የዚያን ጊዜ መንፈሱ ይሠራል:: መንፈሱ በሚሠራበት ጊዜ ደግሞ ነፍስን ወደ ደሙ ይመራል ደሙ እስከ ፈሰሰበት ጊዜ ድረስ መንፈስ ቅዱስ አልወረደም ነበር:: በመንፈሱና በደሙ መካከል ያለው ሕያው ትስስር ሊሰበር የሚችል አይደለም::

የደሙ ሙሉ ኃይል በነፍሳችን እንዲገለጥ ካስፈለገ ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ትምህርት መስጠት እንዳለብን ልንገነዘብ ያስፈልገናል::

እርሱ በእኛ ውስጥ እንዳለና ሥራውንም በልባችን ውስጥ እንደሚሠራ በጽኑ ልንታመን ያስፈልጋል:: የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን የሕይወት ዘር ሆኖ እንደሚኖርና የደሙን ያልተገለጠ ኃይል ወደ ፍጹም መገለጥ እንደሚያመጣ በእምነት መቀበል አለብን:: እንዲመራንም ራሳችንን በመስጠት ልንፈቅድለት ያስፈልጋል::



በመንፈሱ በኩል ደሙ ያነፃናል፣ይቀድሰናል፣ከእግዚአብሔርም ጋር አንድ ያደርገናል:: የሐዋርያው ምኞት አማኞች ለእግዚአብሔር የቅድስና ጥሪ ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ ማንቃት ነበር:: ስለዚህ “እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተፃፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ” 1ኛጴጥ.1፡15 በማለት ቅዱሳንን ሲያነቃቃ እንመለከታለን::

## ዕውቀት አስፈላጊ ነው

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መልዕክቱን የጻፈላቸው አማኞች እንደተዋጁ እና የመዋጀታቸውም ትርጉም ምን እንደሆነ ማወቅ አለባቸው:: ከሁሉም በላይ “በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጁ” ሊያውቁ ያስፈልጋቸዋል (1ጴጥ.1፡19):: በተጨማሪም ፍፁም እንደሚዋጅ ኃይል የደሙን ክቡርነት ሲገነዘቡ የአዲስ እና ቅዱስ ሕይወት ኃይል ይኖራቸዋል::

የተወደድክ ክርስትያን ሆይ ይህ መልዕክት እኔና አንተን/ቺንም ይመለከታል እኛም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጀን ማወቅ አለብን:: የደሙን ኃይል መለማመድ ከመጀመራችን በፊት በቅድሚያ ስለ ደሙ ምንነትና ስለመዋጀት የጠራ እውቀት ሊኖረን ያስፈልጋል:: በዚያን ልክ የመዋጀትን ምንነት ስንረዳና የተዋጀንበትን ደም ክብር ስንገነዘብ ከፊት ይልቅ በሙላት የደሙን ዋጋ ታላቅነት እንረዳለን::

## ፍላጎትና ከፍተኛ ምኞት

በክርስቶስ ክቡር ደም ውስጥ ወደ ጠለቀው የመዋጀት ዕውቀት መመራት የምንፈልግ ከሆነ ራሳችንን ወደ መንፈስ ቅዱስ ትምህርት ቤት መውሰድ አለብን:: ለዚህም ሁለት አብይ ነገሮች አስፈላጊዎች ናቸው:: የመጀመሪያው ጥልቅ ፍላጎት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ደሙን በተሻለ ሁኔታ የመረዳት ጽኑ ምኞት ናቸው:: ኃጢአትን ለማስወገድ ደም መፍሰስ አለበት:: የደሙ ኃይል የኃጢአትን ኃይል ከንቱ አድርጎታል::

ብዙ ግዜ ድነት በማግኘት ከኃጢአት ነፃ በምንወጣበት የመጀመሪያው እርምጃ አካባቢ ልባችን ተነክቶ በጸጸት እናለቅሳለን ስለሆነም በዚህ የጅማሬ ሕይወት ረከተን የምንቀመጥበት ጊዜ አለ:: ነገር ግን በውስጣችን የሚቀረው የኃጢአት ቅሬታ ልንሸከመው የማንችለው የሆንብናል:: ኃጢአት በተለያዩ መንገዶች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለሚቃረን ረክተን መቀመጥ አንችልም:: በውስጣችን የቅድስና ፍላጎት ግፊት ሊበረታ ይችላል:: ሆኖም እኛ

ከምናውቀው ይልቅ ደሙ ታላቅ ኃይል እንዳለው ከእኛ ልምምድ የሚያልፍ ነገር ሊያደርግና ልባችንንም ለትልቅ የቅድስና ምኞት ሊያነሳሳ እንደሚችል አናውቅምን? ከኃጢአት ነፃ የመውጣት፤ የቅድስናና ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር የቀረበ ሕብረት የማድረግ ፍላጎት ካለ በመጀመሪያ የሚያስፈልገው ነገር ደሙ ማድረግ ወደሚችለው ነገር እውቀት መመራት ነው።

### በጉጉት መጠበቅ

የፍላጎትና ምኞት መኖርን አስፈላጊነት ተመለከትን። እነዚህ በራሳቸው በቂ አይደሉም የምንፈልገውንና የምንመኘውን ነገር በጉጉት መጠበቅ ይኖርብናል። ደሙ ምን እንዳደረገ ከቃሉ በእምነት እንደ ተማርን ሁሉ በእኛም ሕይወት ውስጥ በሙሉ ኃይሉ መገለጥ እንደሚችል ማመን አለብን። ያለመብቃት፣ያለማወቅ ወይም የደካማነት ስሜቶች በውስጣችን ተቀምጠው ወደ ጥርጣሬ ሊመሩን አይገባም። ደሙ በምርኮኛ ነፍስ ውስጥ ሆኖ በህያው የሕይወት ኃይል ይሠራል።

ራስህን ለእግዚአብሔር መንፈስ ምርኮኛ አድርግ፤ የልብህን ዓይኖች በደሙ ላይ አድርግ፤ ውስጣዊ ማንነትህን ለደሙ ኃይል ክፈት፤ ራስህን በማያቋርጠው የመርጨት ደም ውስጥ አስጠልል። በሰማይ በጸጋው ዙፋን ላይ ያለው ደሙ የአንተንም ልብ የእግዚአብሔር ዙፋንና መቅደስ አድርጐ ሊሰራው ይችላል።

ደሙ በአንተም ሕይወት ውስጥ ፍሬያማ እንዲሆን የእግዚአብሔርን በግ ጠይቀው ያን ግዜ ከክርስቶስ ደም ኃይል ጋር የሚወዳደር ምንም ነገር እንደሌለ አረጋግጠህ ያለ ጥርጥር አንተም መለማመድ ትጀምራለህ።



# ምዕራፍ ሶስት

## በደም አማካይነት መታረቅ

"በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ፤ እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተሥሪያ አድርጐ አቆመው" (ሮሜ 3:24-25)።

በኢየሱስ ክርስቶስ የደም ኃይል ያገኘናቸውን የተለያዩ በረከቶች ስናስብ "መዋጀት" የሚለው ቃል ሁሉንም ያጠቃልላቸዋል ሆኖም ከነዚህ በረከቶች መካከል መታረቅ የመጀመሪያውን ስፍራ ይይዛል። ስለዚህ "እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው" ይላል። በጌታችን በኢየሱስ የመዋጀት ሥራ ውስጥ እርቅ በባህርዩ ግንባር ቀደም ይሆናል። በመዋጀት ሥራ ተካፋይ መሆን የፈለገ ኃጢአተኛ መፈጸም ከሚገባው ነገሮች መካከል የመጀመሪያው እርቅ መሆን አለበት። እርቅን ተከትለው ሌሎቹ በረከቶች ይመጣሉ።

ሌላው ዋና አስፈላጊ ነገር አንድ ጊዜ መታረቅን ያረኘ አማኝ የመዋጀትን ጥልቅ መንፈሳዊ ትርጉምና በረከት ማግኘቱን መረዳት ነው። በደሙ ኃይል የተገኘ መዋጀት በእርቅ ላይ ሥር ስድዶ ከተተከለ የእርቅን ምንነት ሙሉ መረዳት ይሰጣል። የደሙን ኃይል በሙላት የመለማመጃው ብቸኛ መንገድ ይሄ ነው። ለመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ምርኮኛ የሆነ ልብ ያለጥርጥር የእርቅን ምንነት ይማራል። ስለዚህ የተባረከውን እውነት ለመማር ልባችን ሰፋ ብሎ መከፈት አለበት።

በደም መታረቅ የሚለውን ሐሳብ ለመረዳት የሚከተሉትን በቅድሚያ መገንዘብ አለብን።

*• መጀመሪያ :ኃጢአት እርቅን አስፈላጊ እንዳደረገው • ሁለተኛ: የእግዚአብሔር ቅድስና እርቅን ስለመወሰኑ • ሶስተኛ: የክርስቶስ ደም እርቅን ስለማምጣቱም • መጨረሻ: ውጤቱ የኃጢአት ይቅርታ መሆኑ ናቸው።*

### ኃጢአት እርቅን አስፈላጊ አደረገው

በክርስቶስ የማስታረቅ ሥራ ውስጥ ከሁሉ በላይ ከፍ ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ ኃጢአትን ማስወገድና ማጥፋት ነው። የኃጢአት እውቀት ለእርቅ እውቀት አስፈላጊ ነው

በኃጢአት ውስጥ የሚገኝ እርቅን ተፈላጊ እንዲሆን ያደረገው ነገር ምን እንደሆነ እና እርቅ ደግሞ እንዴት ኃጢአትን ኃይል አልባ እንዳደረገው ማወቅ ያስፈልገናል። ይህን መሰል ትክክለኛ ግንዛቤ ካለን እምነት ሥፍራ ያገኛል በረከቱንም መለማመድ የሚቻል ይሆናል።

ኃጢአት ለዘመናት ባለ ሁለትዮሽ ውጤቶችን ሲያስከትል ኖሯል። አንደኛው ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሰው ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ ነው። በአጠቃላይ በሰው በኩል ባለው ተፅእኖ ላይ የበለጠ እናተኩራለን። ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ረገድ ኃጢአት የሚያመጣው ውጤት በጣም አስፈሪና ጽኑ ነው በእግዚአብሔር በኩል ከሚያመጣው ውጤት የተነሳ ኃጢአት በእኛ ላይ ኃያል ሊሆን ችሏል። እግዚአብሔር ፍፁም ዳኛ እንደመሆኑ ኃጢአትን ላይ ላዩን አይቶ ማለፍ አይችልም። ኃጢአት ሐዘንና ሞትን ያመጣ ዘንድ የእግዚአብሔር የማይለወጥ ሕግ ነው። ሰው በኃጢአት ሲወድቅ በማይለወጠው በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት ከኃጢአት ኃይል ስር ለመሆን ይገደዳል። በእግዚአብሔር ሕግ ምክንያት መዋጀትም ሥራውን የሚጀምረው ያኔ ነው። ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ያለው የተቃውሞ ኃይሉን ካጣ እና የእግዚአብሔር ሕግ ኃጢአት በእኛ ላይ እንዳይሰለጥን ከከለከለው እንግዲያው ኃጢአት በእኛ ላይ ያለው ኃይሉ ተንኮታኩቶበታል ማለት ነው። በእምነት ላይ የተመሰረተ የኃጢአት እውቀት ኃጢአት በእኛ ላይ ሥልጣን እንደሌለው ጽኑ ማረጋገጫ ነው።

ኃጢአት በእግዚአብሔር በኩል ያስከተለው ውጤት ምን ነበር? በመሠረቱ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባህርይ ባለመለወጥ ጸንቶ ይኖራል ሊለወጥም አይችልም። ነገር ግን ከሰው ጋር ባለው ግንኙነት ሙሉ ለውጥን ማስከተሉ አይቀርም። ከኃጢአት መልኮች አንዱ አለመታዘዝ ፣ የእግዚአብሔርን ሥልጣን መፈታተንና የእግዚአብሔርን ክብር አምላክነትና ጌትነት ለመስረቅ መከጀል ነው። በአጠቃላይ ኃጢአት ቅዱሱን እግዚአብሔርን መቃወም ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። በተጨማሪም ኃጢአት የእግዚአብሔርን ቁጣ ማምጣት የሚችል ብቻ ሳይሆን እንዲመጣ የሚገፋፋ ውጤትም ነው።

ከሰው ጋር ኅብረትና ፍቅር ማድረግ የእግዚአብሔር ተቀዳሚ ዓላማ ሆኖ ሳለ ኃጢአት ግን ጠላት እንዲሆን ምክንያት ይሆነዋል። የእግዚአብሔር ፍቅር ለሰው የማይለወጥ ቢሆንም እንኳ ሰውን በህብረቱ ውስጥ ከእርሱ ጋር ተካፋይ አድርጐ እንዳይቀበለው ኃጢአት ከለከለው። ፍቅሩን ከመግለጥ ይልቅ ቁጣውን እርግማኑን እና ቅጣቱን በሰው ላይ



እንዲያፈስስ አስገደደው። በእግዚአብሔርና በሰው ግንኙነት ላይ ኃጢአት ያስከተለው ጠባሳ በጣም ሰፊና እጅግ አስከፊ ነው።

ሰው በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ነው። ተጠያቂነት ደግሞ ዕዳ ነው። ዕዳ ምን እንደሆነ እናውቃለን? ዕዳ ማለት አንድ ሰው ከሌላው ሰው የሚፈልገው ነገር ማለት ነው። የሚፈለገውም ነገር የግድ መሟላት ወይም መስተካከል አለበት። ኃጢአት በሚሠራበት ጊዜ ምናልባት ድርጊቱ ሊረሳ ይችላል ካልተስተካከለ ግን እዳው ይኖራል። ኃጢአተኛ ባለ ዕዳ ነው እግዚአብሔር የኃጢአትን ዕዳ እንዲሁ መተው አይችልም። ኃጢአት መቀጣት ወይም ዕዳው መከፈል አለበት በኃጢአት ምክንያት የተዋረደውም የእግዚአብሔር ክብር ወደ ስፍራው መመለስ አለበት። የኃጢአት ዕዳ ካልተከፈለና ዕዳው ካልተወገደ ቅዱሱ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ሰው ወደ እርሱ መገኛ ኅብረት እንዲገባ አይፈቅድለትም።

ብዙ ግዜ የምናነሣው ትልቁ ጥያቄአችን የኃጢአት ኃይል ማደሪያ ከመሆን እንዴት እንድናለን የሚለው ነው። ከዚህ ይልቅ የሚያሳስበን ጥያቄ በእግዚአብሔር ፊት ከተከመረ የኃጢአት ዕዳ እንዴት እንድናለን የሚለው መሆን ነበረበት የኃጢአት ዕዳ ሊወገድ ይችላልን? የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚቀሰቅሰው የኃጢአት ፍሬ ሊቀርልን ይችላልን? ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ሊሰወር ይችላል? እነዚህ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ከቻሉ በእኛ ውስጥ ያለው የኃጢአት ኃይልም መሰበር ይችላል። የኃጢአትም ዕዳ ሊወገድ የሚችለው በእርቅ በኩል ብቻ ነው።

"እርቅ" የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ "መሸፈን" ማለት ነው ሃይማኖተኞች እንኳ ለዚህ ቃል የራሣቸው የሆነ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር በሰውና በእርሱ መካከል የነበረውን እና ኋላ የፈረሰውን የመጀመሪያውን ግንኙነት ወደ ስፍራው የሚመልስ የኃጢአትን ዕዳ በመሸፈን የሚያስወግደውን እርቅ በእስራኤል መካከል ገልጦታል። እግዚአብሔር እውነተኛ እርቅ ማድረግ የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው የኃጢአት ዕዳ መወገድ አለበት። ኃጢአት በእግዚአብሔር በኩል ያስከተለው ውጤት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። የኃጢአት ዕዳ ከተወገደ ያለ አንዳች የህሊና ክስ ሰው በተባረከ ተስፋ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይችላል።

## እርቅ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ቅድስና ተወስኗል

የእርቅን ምንነት በትክክል መገንዘብ ከፈለግን በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ቅድስና መገንዘብ አለብን። የእግዚአብሔር ቅድስና ወሰን የሌለው የከበረ ፍጻሜ ነው። እግዚአብሔር በሰዎች ውስጥ ሁልግዜ መልካምን ነገር እንዲፈልግ የሚያደርገው ቅድስናው ነው። ስለዚህ ቅድስናውን በሰዎች ውስጥ አስቀምጦ በእርሱ መልካምን ነገር ይሰራል የመልካም ነገር ጠንቆችን ደግሞ ይጠላል ይፈርድባቸዋል።

በእግዚአብሔር ቅድስና ውስጥ ቁጣውና ፍቅሩ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆነው ይኖራሉ። ፍቅሩ ራሱን መስዋዕት አድርጐ ሲሰጥ ቁጣው ደግሞ ከመለኮታዊ ሕጉ የተነሣ ክፉ የሆነውን ነገር ሁሉ አሽቀንጥሮ ይጥላል እንደ እሳትም ይበላዋል። ቅዱሱ እግዚአብሔር በእስራኤል ውስጥ እርቅን በመደንገጉ ምክንያት ማደሪያውን በሥርየት መክደኛው ላይ አደረገ። ሊመጣ ያለውን የአዲስ ኪዳንን ዘመን አሻግሮ በመመልከት "የምቤዣችሁ የእስራኤል ቅዱስ እኔ ነኝ" በማለት አዘውትሮ ለእስራኤል ይናገር ነበር። ቅዱሱ እግዚአብሔር የእርቅ ምክር ሥራውን በክርስቶስ ውስጥ አደረገ። በክርስቶስ ውስጥ የተሰራው የእርቅ ምክር ሥራው የሚያስደንቀው የእግዚአብሔር ቅዱስ ቁጣና ቅዱስ ፍቅሩ በአንድነት ተጣምረው ለእግዚአብሔር እርካታን ማምጣታቸው ነው። ቁጣውና ፍቅሩ ከባህሪያቸው የተነሳ በመካከላቸው የማይታረቅ ቅራኔ ያለ ይመስላል። የእግዚአብሔር ቅዱስ ፍቅር ሰው ከእግዚአብሔር ፊት እንዲርቅ አይፈልግም የሰውን ኃጢአትም ሁሉ መቋቋም አይችልም ኃጢአቱን ሊተውለት ይፈልጋል ነገር ግን ኃጢአተኛው መዋጀት አለበት። ቅዱስ ቁጣው በበኩሉ የሚፈልገው ነገር ሳይሟላለት እጁን አይሰጥም። ምክንያቱም ሕጉ ተንቋል የእግዚአብሔርም ክብር ስለተዋረደ ስለዚህ የእግዚአብሔር ክብር መረጋገጥ አለበት። ሕጉ እስካልተሟላ ድረስ ኃጢአተኛውን በነፃ የመልቀቁ ጉዳይ የሚታሰብ አይደለም። የኃጢአት አስፈሪ ውጤት እግዚአብሔር እጅግ አጥብቆ ኃጢአትን መቃወሙ ነው። ስለዚህ የኃጢአት ዕዳ መከፈል አለበት አሰበለዚያ ኃጢአተኛው ሊድን አይችልም። ለዚህ ችግር ብቸኛው መፍትሔ ደግሞ እርቅ ብቻ ነው።

እርቅ ማለት መሸፈን እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። እርቅ እንዲፈጠር አንድ ነገር የኃጢአትን ቦታ መውሰድ አለበት ከዚያ በኋላ ኃጢአት ስለሚሸፈን በእግዚአብሔር ዓይኖች ሊታይ አይችልም ማለት ነው።



እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑና ዓይኖቹም የእሳት ነበልባል በመሆናቸው ኃጢአትን የሚሸፍነው ነገርም በባህሪው ከኃጢአት ክፉ ድርጊት ጋር የሚቃረን ሆኖ ኃጢአትን ከእግዚአብሔር ፊት በማራቅ በእግዚአብሔር ዓይኖች እንዳይታይ የማድረግ ብቃት ያለው መሆን አለበት።

የኃጢአት ይቅርታ ሊመጣ የሚችለው በመሟላት መንገድ ብቻ ነው። መሟላት ማለት መታረቅ ማለት ነው። ኃጢአት በምትክ ውስጥ ቅጣቱን ሲቀበል ኃጢአተኛው ይድናል የእግዚአብሔር ቅድስናም ይከበራል ፍላጎቱም ይፈጸማል። የእግዚአብሔር ፍቅር ጥያቄ በኃጢአተኛው መዋጀት ውስጥ መልስ ሲያገኝ የእግዚአብሔር ጽድቅ ጥያቄ ደግሞ የእግዚአብሔር ክብር ወደ ሥፍራው በመመለሱና ሕጉ በመፈጸሙ መልስ ያገኛል ማለት ነው።

በብሉይ ኪዳን የመስዋዕት ሕግ ውስጥ ምትክነት እንዴት ተግባራዊ ይሆን እንደነበር ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንማራለን። ነውር የሌለበት እንስሳ የኃጢአተኛውን ቦታ ይወስዳል። ኃጢአተኛው እጁን በመስዋዕቱ እንስሳ ራስ ላይ ጭኖ ኃጢአቱን ይናዘዛል። እንሰሳው የኃጢአተኛውን ኃጢአት ተሸክሞ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል ደሙም ኃጢአትን ተሸክሞ ዕዳን የከፈለ ንጹህ ሕይወትን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ይችላል። የእንስሳው ደም ወይም ሕይወት በኃጢአተኛው ቦታ ሆኖ የኃጢአተኛውን ቅጣት ተቀበለ ማለት ነው። ያ ንጹሕ ደም ኃጢአተኛውንና ኃጢአትን በመሸፈን እርቅ ያመጣል ይህም የሚሆንበት ምክንያት የኃጢአተኛውን ቦታ በመውሰድ የኃጢአትን ይቅርታ ማምጣት በመቻሉ ነው።

## እርቅ የተገኘው በክርስቶስ ደም ነው

እርቅ የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕግ ጥያቄ ማርኪያ ነው። ሕጉ የጠየቀውን ጥያቄ ማርካት የቻለ ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው። በፍጹም ፈቃደኝነትና መታዘዝ ራሱን ከሕግ ስር አድርጎ ሕጉን ፈጸመ። የእግዚአብሔር አብን ፈቃድ ለመፈጸም በዘለዓለም መንፈስ ራሱን በመስጠት በኃጢአት ላይ የተቀመጠውን የሕግ እርግማን በሥጋው ተሸከመ። -ገለትም በፍጹም ፈቃደኝነት ለመታዘዝ ወይም ለቅጣት ራሱን አሳልፎ ሰጠ። የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕግ ጥያቄ ይሄ ነበር። ሕጉ ሙሉ በሙሉ እርካታ ያገኘው በክርስቶስ ነው። ክርስቶስ የሕጉን ጥያቄ ማሟላቱ እንዴት ለሌሎች የኃጢአት ይቅርታ ማስገኛ ሊሆን ይችላል ? እግዚአብሔር

አብ በፍጥረት ውስጥ እና በቅዱሱ የፀጋ ቃልኪዳኑ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ከክርስቶስ ጋር ወስኗል። እርሱንም የሰው ዘር ራስ አድርጐታል። በዚህ ምክንያት ሥጋ ለብሶ ሁለተኛው አዳም በመሆን ይህንን መፈጸም ተችሎታል። ቃል የነበረው ሥጋ በመሆን ከኃጢአት ኃይል ሥር ከሆነው ከእኛ ሥጋ ጋር እውነተኛ ኅብረት አድርጓል። ኃጢአት በሥጋ ላይ ሆኖ የእግዚአብሔር ጠላት የሆነበትን ሁኔታ ሙሉ ኃላፊነት ወሰደ። መታዘዙና ፍጹምነቱ በራሱ የግል ሕይወት ዙሪያ ያበቃ ሳይሆን ከሌሎች ሰዎች ጋር ኅብረት በማድረግ ኃጢአታቸውን የራሱ አድርጎ ተቀበለ።

በፍጥረት በኩል የሰዎች ሁሉ ራስ በመሆን በቃል ኪዳንም እነርሱን ወክሎ በመቅረብ የሰዎች ዋስ ሆነ የሕግ ጥያቄም ሙሉ በሙሉ በፈሰሰው ደሙ ፍፃሜ አገኘ ከእግዚአብሔር ጋር የመታረቃችን ምክንያት የሆነው የኃጢአት ሥርየት ይሄ ነው።

ከዚህ በላይ ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደሆነ በፍጹም ልንዘነጋ አይገባንም። እራሱን ከፍጥረቱ ጋር አንድ በማድረግና እርሱ ወዳለበት ስፍራ ያዳናቸውን ለማስገባት መለኮታዊ ኃይል አለው። በመከራው ዘለዓለማዊ ቅድስና እና ኃይልን ተቀዳጅቶ ለኃጢአት ይቅርታ የፈሰሰው የደሙ ክብር የሰዎችን የኃጢአት ዕዳ ለማስወገድ ከበቂም በላይ ነው። ደሙ እውነተኛ መታረቂያ እና ፍጹም የኃጢአት መሸፈኛ ሆኖ ስለተቆጠረ የእግዚአብሔር ቅድስና ወደ ተወገደው ኃጢአት ዳግመኛ አይመለከትም። የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እውነተኛ ፍጽምናንና ዘለዓለማዊ እርቅን አምጥቷል።

እስኪ ይህን ሐሳብ በተብራራ መልኩ እንመልከተው ክርስቶስ በኃጢአተኛ ጫማ መቆሙን ስንናገር ኃጢአት በእግዚአብሔር በኩል የሚያስከትለውን አስከፊ ውጤት መናገራችን ነው። በተጨማሪም በሰማይ በኃጢአት ምክንያት የሚከሰተውን አስፈሪ ፍርድ መናገራችን ነው። የሰው ዘር ከሰማይ በጎነት፣ ወዳጅነት ፣በረከትና የእግዚአብሔር ሕይወት ከማግኘት ይልቅ ቁጣ፣እርግማን፣ሞትና ዘለዓለማዊ ፍርድ ይፈስበታል። ስለዚህ ሰው እግዚአብሔርን በፍርሃትና በመርበትበት፣ ፍቅርና ተስፋ በሌለበት ሁኔታ እንዲያስበው ይገደዳል። የኃጢአት ዕዳ ሙሉ በሙሉ እስካልተከፈለ ድረስ በቀል ማስከተሉ አይቀሬ ነው።

ውድ አማኝ ሆይ! የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንደ ፈሰሰ ተመልከት የኃጢአት ማስተሰሪያ ተዘጋጅቷል፣ሰላም ተመስርቷል። ኃጢአት በሁሉም ቦታ በመዳረስ እውነተኛ የጥፋት ሰውጥ አስከትሏል። እርቅን የሚቀበሉ ሁሉ ኃጢአት በእነርሱ ላይ ኃይል



አልባ ነው። የእግዚአብሔር ቁጣ ዙሪያውን ዞሮ በእግዚአብሔር ጥልቅ መለኮታዊ ፍቅር ውስጥ ራሱን የሚሰውረው ኃጢአተኛ ወደ እርቅ ሲመጣ ብቻ ነው።

የእግዚአብሔር ቅድስና ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የሚያስፈራራ ሳይሆን በፍፁም ቅድስና ወዳጅ ሆኖ ከሰው ጋር ኅብረት ያደርጋል። የእግዚአብሔር የማያቋርጥ ደስታ ኃጢአተኛው ሰው ወደ እርሱ እንዲቀርብ ይፈቅድለታል። እንዲሁም ከእርሱ ጋር ወደ አለው የቀረበ ኅብረት ግብዣ ያቀርብለታል። የበረከትንም መዝገብ ይከፍትለታል። ያንን ምስኪን ኃጢአተኛ ሰው ከእግዚአብሔር ሊለየው የሚችል ምንም ነገር የለም።

የክርስቶስ ደም በእርቅ ምክንያት ኃጢአቱን ስለሸፈነለት ከእንግዲህ ወዲህ ኃጢአቱ በእግዚአብሔር እይታ ውስጥ አይሆንም፤ የውርስ ኃጢአትም አይታሰብበትም ምክንያቱም እርቅ ፍፁምና ዘለዓለማዊ የመዋጀትን ሥራ ሰርቶለታልና።

አቤት ! የክርስቶስን የደም ክብር ማን ሊናገር ይችላል? የደሙ ክብር በተዋጁት ሰዎች ለዘለዓለም ቢዘመር የሚበዛበት አይሆንም። በሰማይ ያሉ ቅዱሳን ስለ ደሙ ክብር "ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ካህናት... እንሆን ዘንድ አደረግኸን" እያሉ ይዘምራሉ። የሚያሣዝነው ግን በምድር ላይ የምንኖር ቁጥር ስፍር የሌለን የተዋጀን የደሙ ኃይል ያስገኘልንን የማስታረቅ ሥራ በማሰብ ከልባችን ተፈትተን መዘመር አለመቻላችን ነው።

## ይቅርታ እርቅን ይከተላል

ደሙ ኃጢአትን በመከደን እርቅን በማምጣቱ ምክንያት በሰማያዊ ስፍራ አስደናቂ ሰውጥ አስከተለ። ከዚህ ድንቅ በረከት በግላችን ተካፋይ እስካልሆንን ድረስ ምንም አይጠቅመንም።

እርቅ የመጣው በኃጢአት ምክንያት ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ከኃጢአታችንና ከዕዳችን ሁሉ ፈጽሞ ነፃ ያደረገን በእርቅ በኩል ነው። ዕርቅ ለኃጢአት በመዘጋጀቱ ምክንያት አሁን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ እንችላለን። "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውንም አይቆጥርባቸውም ነበር።" የኃጢአትን ይቅርታ ተከትሎ "ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ" የሚለው ግብዣ ይከተላል። ምንግዜም የኃጢአትን ይቅርታ የሚቀበል ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቃል፤ ኃጢአቱ ሁሉ ይቅር እንደተባለለትም ይገነዘባል።

መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአትን ይቅርታ ሙሉነት በመግለጽና በፍርሃት የተሞላውን የኃጢአተኛውን ልብ ለማረጋጋት ደሙ በእርግጠኝነት ኃጢአቱን ፈጽሞ እንዳስወገደለት ለመግለጽ የተለያዩ ምሣሌዎችን ይጠቀማል። ለምሣሌ "መተላለፍህን እንደ ደመና ኃጢአትህንም እንደ ጭጋግ ደምስሼዋለሁ" (ኢሳ.44:22) ፤ "ኃጢአቴን ሁሉ ወደ ኋላህ ጣልህ" (ኢሳ.38:17)። "ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል" (ሚክ. 7:19) "በደል ከእስራኤል ይወገዳል ኃጢአትም ከይሁዳ ተፈልጐ አይገኝም እኔም ኃጢአታቸውን ይቅር እላቸዋለሁ" (ኤር.1:20)።

እንግዲህ አዲስ ኪዳን ቅድስና የሚለው ይህንን ነው። በሮሜ መልዕክት ላይ "ሁሉ ኃጢአትን ሰርተዋልና ... እንዲያው በፀጋው ይጸድቃሉ እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጐ አቆመው ጽድቁንም ያሳይ ዘንድ ነው... ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ" ይላል (ሮሜ. 3:23-26) ።

እርቁ ፍፁም ስለሆነ ኃጢአትም በእርግጠኝነት ስለተሸፈነ እና ስለተደመሰሰ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ በእግዚአብሔር እይታ እርሱ ጻድቅ ነው ከእግዚአብሔር የተቀበለው የበደል ይቅርታ የተሟላና ፍፁም ከመሆኑ የተነሳ ወደ እግዚአብሔር በሙሉ ነፃነት እንዳይቀርብ የሚከለክለው አንዳች ነገር የለም።

በዚህ በረከት ለመደሰት በደሙ ከመታመን የበለጠ የሚያስፈልግ ነገር የለም። ደሙ ብቻውን ሁሉን ነገር ማድረግ ችሏል። ልቡ የተነካ ኃጢአተኛ ከኃጢአቱ ፊቱን ወደ እግዚአብሔር በሚመልስበት ጊዜ የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር በዚያ ደም ላይ የተመሰረተ እምነት ብቻ ነው። በደሙ ኃይል ላይ ያረፈ እምነት ማለት ይሄ ነው። ደሙም ለኃጢአት ይቅርታ የፈሰሰ እና ለኃጢአተኛውም ይቅርታን ሲያመጣለት የሚችል ነው በዚያ እምነት በኩል ከእግዚአብሔር ጋር እንደታረቀ ያውቃል። እንዲሁም እግዚአብሔር ፍቅሩንና በረከቱን በኃጢአተኛው ላይ እንዳያፈስ የሚከለክለው አንዳች ነገር እንደማይኖር ይገነዘባል።

ከዚህ ቀደም በፍርድ ደመና ተሸፍኖ በእግዚአብሔር መዓትና ቁጣ ጠቁሮ የእግዚአብሔር አስፈሪ ፍርድ ይጠበቅበት የነበረው ሰማይ አሁን በዚያ መልኩ አይታይም። በእግዚአብሔር የፊቱ ደስታ ብርሃንና በፍቅሩ ብሩህ ሆኖ እና ደምቆ ይታያል። በደሙ የሆነ እምነት በኃጢአተኛው ልብ ውስጥ ሲገለጥ በተመሣሣይ ሁኔታ አስደናቂ የሥራ ኃይል



በሰማይ ይሰራል። በደሙ ላይ ባለ እምነት የተነሣ ደሙ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያመጣለትን በረከት ሁሉ ተካፋይ ይሆናል።

ውድ አማኞች ሆይ በትጋት ከጸለያችሁ መንፈስ ቅዱስ በደሙ የተገኘውን የታላቁን እርቅ ክብር ይገልጥላችኋል በደሙ ውስጥ የተገኘው የኃጢአት ይቅርታም የእናንተ ይሆናል። የሚከሳችሁና የሚፈርድባችሁ የኃጢአት ኃይል እንደተወገደ የልባችሁ ዓይኖች በርተው ሙሉ በሙሉ ማየት እንድትችሉ ጸልዩ በተጨማሪም እግዚአብሔር በፍቅሩ ሙላትና በፍጹም ደስታ ወደ እናንተ ፊቱን እንደመለሰ እንድትገነዘቡ ጸልዩ ደሙ በሰማይ ያመጣውን የከበረ ፍሬ መንፈስ ቅዱስ እንዲገልጥላችሁ ልባችሁን ክፈቱለት። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጐ አቆመው እርሱ የኃጢአታችን ማስተስሪያ ነው። በእርሱ ላይ ባለን መታመን ምክንያት ኃጢአታችን በእግዚብሔር ፊት ተሸፍኖአል። በእኛና በኃጢአታችን መካከል ደሙን ብናስገባ እርሱ የሰጠን መዋጀት እንዴት ሙሉ እንደሆነ መገንዘብ እንጀምራለን። በደሙም ውስጥ ባለ እምነት እርቅ እንዴት ኃያል እንደሆነ እንገነዘባለን።

በሰማይ የሚሰራው የደሙ ኃይል በሕያው ክርስቶስ አማካይነት በአንተም/ቺም ልብ ውስጥ የበለጠ እየተገለጠ ይሄዳል፤የዚያን ጊዜ በይቅርታ በሙሉ ብርሃንና ደስታ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መመላለስ ምን እንደሆነ መማር አስቸጋሪ አይሆንም።

እስከ አሁን የኃጢአትህን ይቅርታ ያላገኘህ ውድ የአዳም ዘር ሆይ! ይህ መልዕክት በደሙ እንድታምን ለአንተ የቀረበ አስቸኳይ ጥሪ አይመስልህምን? እንደ ኃጢአተኛ እግዚአብሔር ለአንተ ያደረገውን ነገር ላለመቀበል በእምቢተኝነት አልገፋህምን? "ፍቅር እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም" (1ዮሐ. 4:10)።

መስኮታዊ የክርስቶስ ደም ፈስሶ እርቅ ሙሉ ሆኗል። ስለሆነም "ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅ" የሚለው ጥሪ አሁን ወደ አንተ/ቺ መጥቷል። ምላሽህ/ሽ ምን ይሆን? ኃጢአትህ/ሽን በመናዘዝ ከኃጢአት ኃይልና ባርነት ነፃ መውጣት ብትፈልግ በደሙ እምነትን ተለማመድ እንዲናገርህ ለተላከልህ ቃል ልብህን በሙሉ ክፈትለት በዚህ ቅጽበት በደሙ ሊያድነኝ ይችላል የሚል ጽኑ እምነት ይኑርህ/ሽ ። የሚያስፈልግህ/ሽ ማመን ብቻ ነው። ቀጥለህ/ሽ "የክርስቶስ ደም የፈሰሰው ለእኔ ነው" ብለህ/ሽ ተናገር/ሪ እንደ በለ ዕዳ የጠፋ ኃጢአተኛ እና የኃጢአትን ይቅርታ እንደሚፈልግ ሰው ሆነህ/ሽ ከቀረብክ/ሽ ፍጹም መታረቅን ያመጣው

ደሙ ኃጢአትህን/ሽን ይሸፍናል። እንደገናም ያድስሃል። በቅጽበትም ወደ እግዚአብሔር ርህራሄና ፍቅር ውስጥ ትገባለህ/ትገቢያለሽ።

ስለዚህ በደሙ እምነት እንድትለማመድ/ጂ ልባዊ ምኞቴ ነው አሁን በዚህ ቅጽበት በእግዚአብሔር ፊት ወድቀህ/ሽ ለገዛ ነፍስህ/ሽ የክርስቶስን የደሙን ኃይል እንደምታምን/ኚ ልትነግረው/ሪው ትችላለህ/ያለሽ ከኑዛዜህ/ሽ በኋላ በተናገርከው ቁም በእርሱም ጽና/ኚ በደሙ በኩል በእምነት ኢየሱስ ክርስቶስ የአንተም ኃጢአት ማስተሥርያ ይሆንልሃል/ሻል።



# ምዕራፍ አራት

## በደም አማካይነት መንፃት

"እርሱ በብርሃን እንደአለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል" (1ኛዮሐ.1:7) ደሙ ያደረገው ዋናው አስፈላጊ ነገር ከኃጢአት ተመልሶ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ እንደሆነ ተመልክተናል። የኃጢአት ይቅርታ የሚባለው ስለ እርቅ ያለን የዕውቀት ፍሬ እና እምነት ማለት ነው። በተጨማሪም የኃጢአት ይቅርታ ማለት አንድ ጊዜ በሰማይ ስለ ኃጢአተኛው የተደረገውን ነገር ማወጅ እና የኃጢአተኛው ልብ በእምነት እንዲቀበለው ማድረግ ነው።

የመጀመሪያው የደሙ ፍሬ የኃጢአት ይቅርታ ብቻ አይደለም። በተንዳኝ ነፍስ ራሷን ለእግዚአብሔር መንፈስ በመስጠት በእርቅ ኃይል በእምነት መደሰቷ ነው። የቀሩትንም በረከቶች ለመግለጥ ደሙ የበሰጠ ኃይሉን እንደሚጠቀም መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

የእርቅ የመጀመሪያው ፍሬ ከኃጢአት መንጻት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚል እስቲ እንመልከት። አብዛኛውን ግዜ ስለ መንፃት በመካከላችን ይነገር የነበረው የኃጢአት ይቅርታ ከማግኘት ወይም ከእዳ ከመንፃት ባለፈ ሁኔታ አልነበረም። ከኃጢአት መንፃት ማለት ከኃጢአት ብክለት መዳን ማለት እንጂ ከሕሊና ክስ መዳን ማለት ብቻ አይደለም። የኃጢአት ክስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ይመለከታል ለተሳሳትነው ነገር የማስተካከል ኃላፊነታችንን ወይም ቅጣቱን መሸከም እንዳለብን ያሳያል። የሕሊና ክስ በሌላ በኩል የኃጢአት ብክለት ማለት ኃጢአት ወደ ውስጣችን የሚያመጣው የመርከስና የመቆሸሽ ስሜት ነው በዚህ ምክንያት መንፃት አስፈላጊ ሆኗል።

እግዚአብሔር ባዘጋጀለት ሙሉ መዳን መደሰት ለፈለገ አማኝ ሁሉ ይህ ትምህርት ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ይገነዘባል ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመንፃት የሚያስተምረውን በትክክል ለመገንዘብ የሚከተለውን በጥንቃቄ እንመልከት።

- *በመጀመሪያ በብሉይ ኪዳን መንጻት የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው ?*
- *ሁለተኛ በአዲስ ኪዳን በዚህ ቃል የተነገረው በረከት ምንድን ነው?*
- *ሶስተኛ በዚህ በረከት ሙላት እኛስ እንዴት ደስታውን መለማመድ እንችላለን?*

## መንጻት በብሉይ ኪዳን ጊዜ

በሙሴ እጅ ከእግዚአብሔር ወደ እስራኤል የተላለፈው የአገልግሎት ሥርዓት የእስራኤልን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ የሚያዘጋጁት ሁለት ሥርዓቶች ነበሩት። እነርሱም መባ ወይም መስዋዕት እና መታጠብ ወይም የመንጻት ሥርዓቶች ናቸው። ሁለቱንም በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ለመመልከት እንሞክራለን። ሁለቱንም ሥርዓቶች ሰው በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል ኃጢአተኛ እንደሆነ እና ይህ ብቃት የሌለው ኃጢአተኛ ሰው እንዴት ወደ ቅዱሱ እግዚአብሔር እንደሚቀርብ ለማሳየት ታቅደው የተሰጡ ናቸው። ሁለቱም ሰውን ወደ እግዚአብሔር ኅብረት የመለሰውን የክርስቶስ የመዋጀት ሥራ ምሣሌዎች ናቸው እንደ ሕጉ እነዚህ መስዋዕቶች ሊመጣ ስላለው በክርስቶስ መዋጀት የሚናገሩ ሥራዎች ነበሩ። የዕብራውያን ፀሐፊ መንፃትን በዋንኛነት እንደሚከተለው ጠበቅ አድርጎ ይገልጸዋል። "ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሣሌ ነው። እንደዚህም መባና መስዋዕት ይቀርባሉ...ስለ ልዩ ልዩ መታጠብም የሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸው" ይላል። (ዕብ. 9:9-10)

የእስራኤላውያንን ሕይወት መገመት ከቻልን የኃጢአት ግንዛቤና የመዋጀት አስፈላጊነት ሕሊናችንን የሚያነቃው ከመስዋዕት ባነሰ መንፃት እንዳልሆነ እንገነዘባለን። የክርስቶስ የደሙ ኃይል ምን እንደሆነ ከእነርሱም ደግሞ መማር እንችላለን።

በጣም አስፈላጊ የሆነውን አንዱን የመንፃታቸውን ምክንያት በምሣሌ እንመልከት ሬሳ ባለበት ቤት ውስጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው አለበለዚያ ሬሣ ወይም የሙታን አጽም በእጁ የነካ ለሰባት ቀን ያህል የረከሰ ይሆናል። ሞት እንደ ኃጢአት ዋጋ ከሞተው ነገር ጋር ንክኪ ያደረገውን ሰው ሁሉ ያረክሰዋል ከዚህ ርኩሰት መንጻት የሚቻለው በዘኁልቁ 19 እንደተገለጸው የጊደር ሥጋ አመድ በመጠቀም ነው። ይህንን (ከዕብ. 9:13-14) ጋር ማስተያየት ይቻላል። ይህም አመድ በውሃ ውስጥ በጥብጦ በሂሶጵ ቅጠል አማካይነት በረከሰው ሰው ላይ ይረጫል አንድ ግዜ ከነፃ በኋላ ሰውነቱን በንጹህ ውሃ ይታጠባል።

ያልነፃ፣መንጻት እና ንፁህ የሚሉት ቃላት ከለምጽ መፈወስን የሚያመለክቱ ቃላት ናቸው። ይህ በሽታ ምናልባት የቁም ሞት ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። የሚነፃው ሰው በመጀመሪያ የእርግብ ደም መስዋዕት ሆኖ በተቀላቀለበት ውሃ ይረጫል ከዚያም በንጹህ ውሃ



ሰውነቱን ይታጠባል ከሰባት ቀናት በኋላ በመስዋዕቱ ደም እንደገና ይረጫል ዘሌ.13 እና 14 ይመልከቱ።

ሐሳብን የሚስበው የመንጻት ጥልቅ ሕግ በመንጻትና በመስዋዕት መካከል ያለውን ልዩነት በሁለት መንገድ ያሳየናል በመጀመሪያ ደረጃ መስዋዕት እርቅን እውን ወዳደረገው መተላለፍ በግልጽ ያመለክታል መንጻት ግን በራሣቸው ኃጢአት ካልሆኑ ነገሮች ጋር የተገናኘ ነው። ለምሣሌ ሰው ሬሣ ቢነካ ይረክሳል ሬሣ መንካት በራሱ ኃጢአት አይደለም ሞት ግን የኃጢአት ውጤት ነው የኃጢአት ውጤትን በመንካቱ ረክሷልና መንጻት አለበት። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ ከኃጢአት ውጤቶች ጋር መነካካት እንደ መርከስ መታወቅ ይኖርበታል። በሁለተኛ ደረጃ መስዋዕትን ስንመለከት ለመስዋዕት አቅራቢው ለራሱ የሚደረግለት ምንም ነገር አልነበረም ኃጢአተኛው የመስዋዕቱ ደም በመሰዊያው ላይ ሲረጭና ወደ ቅድስት ውስጥ ካህኑ ይዞት ሲገባ ይመለከታል የእርሱ ድርሻ ይህ ድርጊት በእግዚአብሔር ዘንድ እርቅን እንደሚያስገኝለት ማመን ብቻ ነው። ቢሆንም ለኃጢአተኛው በቀጥታ የተደረገለት ነገር የለም። በሌላ በኩል መንጻት በሰውየው ላይ በቀጥታ የሆነውን ነገር ያሳያል። መርከስ በሁለት አቅጣጫ ሊከሰት ይችላል ይኸውም በውስጥ ደዌ አለበለዚያም በውጪ መነካካት ሊሆን ይችላል። ይህን መሰል ሁኔታ የተፈጠረበት ሰው እግዚአብሔር እንዳዘዘው በውሃ መታጠብ ወይም መረጨት ይኖርበታል አለበለዚያ ሳይነፃ እንደረከሰ ሊኖር ይችላል።

መንፃት ኃጢአተኛው ሊሰማው የሚችል እና የሚለማመደው ነገር ነው። በመንፃት የሚመጣው ለውጥ ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ግንኙነት ብቻ አይደለም። በኃጢአተኛውም ሁኔታ ውስጥ የለውጥ ምክንያት ይሆናል። መስዋዕት በማቅረብ ለኃጢአተኛው አንድ ነገር ይደረግለታል መንፃት ደግሞ በኃጢአተኛው ውስጥ አንድ ነገር ይፈጽማል። መስዋዕት ለኃጢአት ክስ ማስወገጃ የሚቀርብ ነው መንፃት ግን ከኃጢአት ብክለት መላቀቂያ ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ "መንጻት" እና "ንፁህ" የሚሉት ቃላት ተመሣሣይ ትርጉም አላቸው። ዳዊት በመዝሙር (51) ሲጸልይ "ከኃጢአቴ አንጻኝ... በሂሶጵ እርጨኝ እነፃማለሁ" ይላል ዳዊት በዚህ ጸሎት የሚጠቀመው ቃል አብዛኛውን ጊዜ ሬሣ ነክቶ ስለሚነፃ ሰው የሚነገረውን ዓይነት ቃል ነው። ሂሶጵ የሚያገለግለው በረከሰ ነገር ላይ ለመርጫነት ነው። የዳዊት ጸሎት ከኃጢአት ይቅርታ ያለፈ ነው በደለኛ እንደሆነ ይናገራል ኃጢአተኛ ተፈጥሮ እንዳለው ኃጢአቱን ይናዘዛል ከዚህ ኃጢአቱም እንዲነፃ ይጸልያል በጸሎቱ መሐል ተመሣሣይ

ቃል እንደገና ሲጠቀም እናያለን ይኸውም "ንፁህ ልብን ፍጠርልኝ" በማለት ነው እንግዲህ መንፃት ከኃጢአት ይቅርታም ያለፈ ነገር እንደሆነ እናያለን። በተመሣሣይ ሁኔታ ሕዝቅኤል ይህንን ሁኔታ ከውስጣዊ ሕይወት መቀየር ጋር በተያያዘ መልኩ ሲጠቀምበት ይታያል። እግዚአብሔር መወገድ ስላለበት ኃጢአት የተናገረው በሕዝቅኤል ምዕራፍ 35 ቁጥር 25 ላይ ነው። "ቃሉም ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ" ይላል።

ነብዩ ሚልኪያስ ደግሞ ይህንን ቃል ከእሳት ጋር በማያያዝ ተመሣሣይ ቃል ሲጠቀም እንመለከታለን "እርሱም ብርን እንደሚያነጥር እና እንደሚያጠራ ሰው ይቀመጣል። የሌዊንም ልጆች ያጠራል " ይላል። (ሚልክ.. 3:3) በውኃ፣ በደም እና በእሳት መንጻት በአዲስ ኪዳን ሥር የሚከናወኑ የውስጣዊ ሕይወት መንጻት እና ከሃጢአት መውጊያ የመዳኛ ምሣሌዎች ናቸው።

## በአዲስ ኪዳን መንጻት እንደ በረከት ነው

የጠራ ወይም ንጹህ ልብ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሷል። ጌታ ኢየሱስም ይህን አስመልክቶ ሲናገር "ልበ ንፁሆች ብፁዓን ናቸው" ብሏል። (ማቴ. 5:8) ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1:5 ላይ ሲናገር " ፍቅር ከንፁህ ልብ … የሚወጣ" መሆኑንና "ስለ ንፁሕ ህሊናም" ገልፆአል። ጴጥሮስም የመልዕክቱን ተቀባዮች "በንፁሕ ልብ እርስ በእርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ" ይላል እዚህ ላይ መንፃት የሚለው ቃል ሥራ ላይ ውሎ እናያለን። እግዚአብሔር በእምነት ልባቸውን ያነፃቸውና የእግዚአብሔር ሕዝብ ተብለው ስለተጠሩ ሰዎች ከቃሉ እናነባለን። (ሐዋ. 17:9) ጌታ ኢየሱስ የእርሱ ለሆኑት ያለውን ዓላማ ሲገለጽ "መልካሙን ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነው ሕዝብ ለራሱ እንዲያነፃ" ይላል። (2ቆሮ. 7:1)

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ መንፃት በሰው ልብ ውስጥ የሚከናወን የኃጢአትን ይቅርታ የሚከተል ድርጊት መሆኑን ያስተምሩናል።

በ1ኛ ዮሐንስ 1:7 ላይ "የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል" የሚል ተጽፎልናል። "ያነፃል" የሚለው ቃል በተለወጥንበት ግዜ የተቀበልነውን የኃጢአት ይቅርታ ፀጋ አያመለክትም ነገር ግን በብርሃን የሚሄዱ የእግዚአብሔር ልጆች የጸጋ ፍሬ ነው እንዲሁም "እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ… የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም



ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል" ይላል ከቁጥር 9 በኋላ ያለውን ሃሳብ ስንመለከት ከኃጢአት ይቅርታ በላይ እንደሆነ ያሳያል "ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው" ይላል።

መንጻት የክርስቶስ ኢየሱስን የደም ኃይል በአማኝ ልብ ውስጥ በእምነት የሚቀበሉት ውስጣዊ ልምምድ እና ከኃጢአት ይቅርታ በኋላ የሚመጣ የኃጢአት ይቅርታ ፍሬ ነው።

በቃሉ መሠረት ይህ ድርጊት መጀመሪያ የሚከናወነው ሕሊናን በማንጻት ነው "ነውር የሌለው ሆኖ በዘለዓለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት… ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነፃ ይሆን" ይላል (ዕብ.9:14)። የጊደር ሥጋ አመድ በረከሰው ላይ መረጨት የክርስቶስን ክቡር ደም በግል ለመለማመድ በምሣሌነት የቀረበ ነው ህሊና ለድርጊታችን ፍርድ የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለውን እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ምስክርነት የሚሰጥ ውስጣዊ ድምጽ ነው ህሊና በደም በሚነፃበት ጊዜ እግዚአብሔርን ደስ እንደምናሰኝ ምስክር ይሆናል።

በዕብራውያን 10:2 ላይ "የሚያመልኩት አንድ ግዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በህሊናቸው ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን?" ይላል ደሙ ሙሉ በሙሉ በህሊና ክስ እና ከኃጢአት ኃይል እንደ አዳነን መንፈስ ቅዱስ ለውስጣችን ይመሰክርልናል። ዳግም የተወለደው ውስጣዊ ማንነታችን ደግሞ ከኃጢአት ተጽዕኖ ያመልጣል። ኃጢአት ከነመፈታተኛው አሁንም በሥጋችን ውስጥ ይኖራል ይሁን እንጂ እኛን የመግዛት ኃይል አይኖረውም። ህሊና ሲነፃ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል የሚጋርድ ትንሽ የኃጢአት ጥላ እንኳ ሥፍራ አይኖረውም በዚህ ጊዜ ጌታን በሙሉ የመዋጀት ኃይሉ መመልከት እንችላለን በደም የነፃ ህሊና ፍጹም መዋጀቱን እና የእግዚአብሔርን ፍጹም ደስታ ከመመስከር የሚበልጥበት ነገር የለም።

ህሊና ሲነፃ የህሊና ማዕከል የሆነው ልብም ይነፃል። ልብ ከክፉ ህሊና መንጻት እንዳለበት ከዕብራውያን 10:22 ተመልክተናል። መንጻት ያለበት ህሊና ብቻ ሳይሆን ልብም ጭምር ነው። ልብ ሲነፃ አእምሮአችን፣ፈቃዳችን፣ከሃሳባችንና ከምኞታችን ጋር አንድ ላይ ይነፃሉ። ክርስቶስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ ባፈሰሰው ደሙ እንዲሁም ወደ ሰማይ በገባበት ኃይሉ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤው በማያቋርጥ ሁኔታ ውጤታማ ሲሆኑ በሞትና በትንሣኤ ኃይሉ ክንውን ጠላትነትና የኃጢአት ምኞት ታረዱ።

የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ከስውር እና ከልምምድ ኃጢአቶች ሁሉ ያነፃል። ደሙ በነፍስ ውስጥ በሰማያዊ መንፈሳዊ ኃይል ሲሰራና በአንድ አማኝ ውስጥ የደሙ ሥራ በሙላት በሕይወቱ ሲገለጥ አዲሱ ልምምድ አሮጌው ተፈጥሮ ኃይሉን እንዳይገለጥ ይከለክለዋል። በደሙ ውስጥ ክፉ ምኞትና መሻት ይሸነፋሉ። መንፈስ ቅዱስ የከበረውን የደሙን ፍሬ በሚገልጥበት ጊዜ ሁለንተናን ያነፃል። መሰናክል ቢከሰት እንኳ ነፍስ ቅጽበታዊ መንፃትና መታደስን ስታገኝ በንስሐ ያልተወገዱ ያልተነቃባቸው ኃጢአቶች በዚህ ሂደት ውስጥ ይከስማሉ። በህሊና ክስ እና በኃጢአት ብክለት መካከል ልዩነት ያለ ቢመስልም ነገሩን የበለጠ በጠራ ሁኔታ ለመገንዘብ ያህል እንጂ በእውነተኛው ሕይወት ውስጥ ስንመጣ ግን እነዚህ ነገሮች በመካከላቸው የጐላ ልዩነት እንደሌለ እንረዳለን። እግዚአብሔር በደም ውስጥ በኃጢአት ሁለንተና ላይ ይፈርዳል ሁሉም የደሙ እውነተኛ ሥራ ኃይሉን በሙላት በአንድ ጊዜ በህሊና ክስ እና በኃጢአት ብክለት ላይ ይገልጣል መታረቅና መንፃት ሁልግዜ ባለመነጣጠል አብረው ይሄዳሉ ደሙም ሳያቋርጥ ይሰራል።

ብዙ ሰዎች ደሙ ስለፈሰሰልን ደግመን ኃጢአት ብንሠራ እንኳ እንደገና ወደ ደሙ በመቅረብ መንጻት እንችላለን ብለው ያስባሉ ሀቁ ግን ከዚህ የተለየ ነው። ደሙ እንደ ምንጭ ወይም እንደ ፏፏቴ የሚፈስሰው በውስጡ ወይም ከስሩ የሚሆኑትን ሰዎች ለማንፃት ነው። "ኃጢአትንና ርኩሰትን የሚያነፃ ምንጭ ተከፍቷል" (ዘካ.13፡1) የዘለዓለም መንፈስ ኃይል የሆነው የዘለዓለም ሕይወት በደሙ ውስጥ ይሠራል። ስለዚህ ልብ ዘወትር በማያቋርጠውና በሚያነፃው የደም ፏፏቴ ስር ሊያድር ያስፈልገዋል።

በዘመነ ብሉይ ኪዳን መንፃት ለእያንዳንዱ ኃጢአት አስፈላጊ ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን መንፃት የተመሠረተው ዘለዓለም ህያው ሆኖ በሚኖረው በክርስቶስ ላይ ነው። እምነት ይህንን እውነት ትኩር ብሎ በሚመለከትበት ፣በሚፈልግበት እና በሚያርፍበት ጊዜ ልብ በእያንዳንዱ ቅጽበት በደሙ ኃይል ጥበቃና ማንጻት ውስጥ ይኖራል።

## የዚህን በረከት ሙሉ እርካታ መለማመድ

በክርስቶስ ደም አማካይነት የተገኘውን የኃጢአት ሥርየት በእምነት ተካፋይ የሆነ ማንኛውም አማኝ ከመንጻቱም ውጤት ደግሞ ተካፋይ ይሆናል ነገር ግን የመንጻቱ ልምምድ በልዩ ልዩ ምክንያት የተሟላ ሆኖ አናይም። ይህን የከበረ በረከት በሙላት ለመለማመድ የሚያስፈልገው ቅድመ ሁኔታ ምን እንደሆነ መረዳት ትልቅ ጠቀሜታ አለው።



ከሁሉ አስቀድሞ የእውቀቱ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም፤ ብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ በደሙ አማካይነት ነው ብለው ይለምናሉ ስለሆነም ይፀልያሉ የሚያገኙት ብዙ ነገር የለም ከሁሉ አስቀድሞ ስለ ደሙ የበለጠ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል።

የእግዚአብሔር መንፈስ የክርስቶስን ደም ለመግለጽ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያዩ አገላለፆች ሲጠቀም ልዩ ዓላማ እንዳለው መረዳት መባረክ ነው። ቀጥሎ የቃሎቹን ልዩ ትርጉም መረዳት ያስፈልጋል። እያንዳንዱ አማኝ መንጻት በሚለው ቃል ጌታ ምን ሊያስተምረው እንደፈለገ ቃሉ በተጠቀሰበት ሥፍራ ሁሉ ትኩረት ሰጥቶ ይመርምር። መንጻት የሚለው የተነገረበትን ቦታ እና ምክንያት በማመሳከር ይወቅ። ቃሉ የኃጢአትን ክስ ከማስወገድ ይልቅ ለአማኞች ብዙ ተስፋ ሰጪ እንደሆነ ፈጥኖ ይረዳል። በመታጠብ የሚደረገው መንጻትን በሙላት ባይገልጽም አማኙ በውስጡ መባረክንና ከኃጢአት ውጤት በደም መንፃትን በጉጉት እንዲጠባበቅ መንደርደሪያ ይሰጠዋል። የደሙንም በረከት የመለማመጃው የመጀመሪያ እርምጃ የመንፃት እውነታ ዕውቀት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ፍላጎት ወይም መሻት መኖር አለበት። "ልበ ንፁሆች ብፁዓን ናቸው እግዚአብሔርን ያዩታልና" የሚለው ቃል ጌታ ኢየሱስ ለምድራዊ ሕይወታችን የወሰነውን ብፅዕና ለሚመጣው ሕይወት በማስተላለፍ የምንጠባበቅ ከሆነ ክርስትናችን የሚያስፈራ ነው። የልብ ንጽሕና የእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ባህሪ እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ በቂ ግንዛቤ አላገኘም፤ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረጊያውና በእርሱ ማዳን መደሰቻው መንገድ ነው። በዘመናችን በሁሉም ነገር ጌታን ደስ የማሰኘት ውስጣዊ ፍላጐት አለን ኃጢአትና የኃጢአት ቆሻሻ ደግሞ ውስጣችንን ይረብሸናል።

ውስጣዊ ፍላጎታችንን ወይም መሻታችንን የሚቀሰቅስ የእግዚአብሔር ቃል የበረከት ተስፋን አዝሎ ወደ እኛ ይመጣል። የክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነፃ እንመን። ለእግዚአብሔር ሥራ ራስህን እንዴት አሳልፈህ እንደምትሰጥ ካወቅህ በአንተ ውስጥ ታላቅ ኃይሉን ይገልጣል። በኃጢአተኛ ተፈጥሮህ ምክንያት ህሊናህ በኃጢአት ቆሻሻ እየረከሰና እየተከሰሰ ከመኖር በደሙ ነጽተህ ከኃጢአት ቆሻሻም ተጠብቀህ የመኖር ፍላጎት ኖሮህ አያውቅም? ምናልባት ፍላጎትህ ለዚህ በረከት ሊያነቃህ ይችላል። "ከእርኩሰት ሁሉ ንፃ" በማለት ያዘዘው እግዚአብሔር በአንተም ውስጥ እንደሚሰራ በእምነት ተቀበል።

ሶስተኛው ሁኔታ ንጹህ ካልሆነ ነገር ሁሉ ራስህን ለማራቅ ፈቃደኛ ሁን። በኃጢአት ምክንያት በተፈጥሮአችን እና በዓለም ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ረክሷል። ከረከሰ ነገር ሁሉ

የመለየት ውስጣዊ ፍላጎት እስከሌለ ድረስ መንፃት ሊኖር አይችልም። ለመንፃት እርኩስ ነገርን መተውና ከእርሱም መለየት ሊቀድም ይገባዋል። እግዚአብሔር ለምርጦቹ የሰጠው ትዕዛዝ "እርኩስንም አትንኩ" የሚል ነው። ዙሪያዬን የከበበኝ ነገር ሁሉ የረከሰ ነገር እንደሆነ መገንዘብ አለብኝ።

ወዳጄ ሁለንተናዬ ለእግዚአብሔር ክብር ከተማረከ ከጌታ ጋር ባለኝ በእያንዳንዷ ኅብረት በክርስቶስ ክቡር ደም እነፃለሁ በዚህን ጊዜ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዬ በጠቅላላ ነፍሴና ሁለንተና ተፈጥሮዬ በማያቋርጥ የመንፃት ልምምድ ውስጥ ይገባል።

ነገሮችን ከመመርመር ይልቅ የሚያጣጥልና የሚንቅ በረከቱን በሙላት መለማመድ አይችልም። ነገር ግን ሁለንተናው በክርስቶስ ደም እንዲጠመቅ ሙሉ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ "የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል" የሚለውን ቃል በሙላት በሚረዳበት መንገድ ላይ ነው።

የመጨረሻው ነገር በደሙ ኃይል እምነትን መለማመድ ነው። አለማመናችን የደሙ መስዋዕትነት ውጤት እንዳያመጣ ይከለክላል ደሙ ኃይሉንና የመስዋዕትነት ፍሬውን እንደያዘ ይኖራል አለማመናችን ግን ልባችንን በመዝጋት ደሙ እንዳይሰራ እንቅፋት ይሆናል። እምነት ደግሞ እንቅፋቱን በማስወገድ ሕያው ጌታ ደሙን መስዋዕት አድርጎ ላቀረበበት መለኮታዊ ኃይል ልባችንን ይከፍታል።

በደሙ መንፃት እንዳለ እንመን፤ በአረንጓዴ ተክሎች የተሞላ በመንገድ ዳር የሚገኝ የአትክልት ሥፍራን ተመልክታችኋል? በሰምለሙ የአትክልት ሥፍራ አካባቢ ከተነጠፈው መንገድ በአላፊ አግዳሚው እግረኛና መኪና የሚነሣው አቧራ በመንገዱ ዳር ያሉትን አትክልቶችና ሣሮች ያለብሣቸዋል ነገር ግን አትክልትን እየረጨ ውኃ የሚያጠጣው መሣሪያ ሥራውን ሲጀምር በአንድም አትክልት ላይ የአቧራ መልክ አታዩም በዚያ ፈንታ ግን ሁሉም አረንጓዴ ተክሎች ደማቅ አረንጓዴ እና አዲስ ሆነው ስሜትን በሚስብ መልክ ይታያሉ በተመሣሣይ ሁኔታ የክርስቶስ ክቡርደም በአማኝ ልብ ውስጥ ያለማቋረጥ በእምነት ይሰራል ራሱን በእምነት ለጌታ የሚሰጥ እና ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች የክርስቶስ ደም በእርሱም ሕይወት ሊያደርግ እንደሚችል ለሚያምን ለእርሱም ደግሞ ይሰጠዋል። የደሙን ሰማያዊ መንፈሳዊ ፍሬ በየቅጽበቱ መለማመድ ይቻላል። የደሙ ኃይል ሁልግዜ በጌታ የደሙ ምንጭ በቁስሉ ውስጥ እንድኖር ያደርገኛል።



ውድ አማኝ ሆይ ! ወደ ክቡር የክርስቶስ ደም በእምነት እንድትቀርብና ደሙም ልብህን ከኃጢአት ሁሉ እንዴት እንደሚያነፃ በእምነት እንድታይ ጥሪ አቀርብልሃለሁ።

በመንገዱ የዛለና የደከመ ተጓዥ ንጹሕ ቀዝቃዛ ምንጭ ሲያገኝ ጠጥቶ በመርካት ታጥቦ በመንጻት ከድካሙ እንደሚያርፍ በቅዝቃዜውም እንደሚደሰት ኃይሉም እንደሚታደስ ታውቃለህ። ዓይኖችህን በእምነት ወደ ላይ አንስተህ ብትመለከት ከላይ ከሰማይ የማያቋርጥ ምንጭ ወደ ምድር ሲንዶለዶል ትመለከታለህ። በክርስቶስ የደሙ ኃይል ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ በምድር በሚኖሩ ነፍሶች ላይ ለመፈወስና ለማንፃት ይፈሳል "የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል" በሚለው ቃል መሠረት ራስህን ከዚህ ፏፏቴ ስር አስቀምጥ። ይህ ቃል አንተ ከምትገምተውና ከምትረዳው የበለጠ መለኮታዊ ጥልቀት እና ሰፊ ትርጉም አለው። በደሙ የሚያነፃህ ቃል ኪዳኑንም በአንተ ውስጥ በኃይል የሚፈጽመው ራሱ ጌታ እንደሆነ እመን። በክርስቶስ ደም ከኃጢአት እንደምትነፃ በሙሉ መታመን በየዕለቱ በባርኮቱ ኑር።

# ምዕራፍ አምስት

## በደም አማካይነት መቀደስ

**"ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ"**

**ዕብ.13፡12**

በደም ውስጥ መንፃት ያለፈው ምዕራፍ ርዕሳችን ነበር፡፡ አሁን ደግሞ በደም ውስጥ መቀደስ ትኩረታችንን የምናሳርፍበት ርዕስ ጉዳይ ይሆናል፡፡ ላይ ላዩን ተመልካች ለሆነ ሰው በመንፃትና በመቀደስ መካከል ትንሽ ልዩነት ያለ ይመስላል ሁለቱም ቃሎች ተመሣሣይ ነገርን የሚገልጡ ቢመስልም ልዩነታቸው ግን የሰፋና በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ መንፃት አብዛኛውን ጊዜ ከአሮጌው ሕይወት ጋር ይያያዛል፡፡ በመንፃት የኃጢአት ቆሻሻ ይወገዳል ይህ እርምጃ የዝግጅት ጊዜን ይወክላል፡፡ ቅድስና ግን አዲሱን ሕይወት የሚመለከት ነው የእግዚአብሔርን ባህሪ ለመምሰል በእግዚአብሔር የተሰጠ ነው፡፡ ቅድስና ማለት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን ማለት ነው፡፡ በደሙ አማካይነት ለእኛ የተሰጠ የበረከቱ ልዩ ሙላት ነው፡፡

በሁለቱም ቃሎች መካከል ያለውን ልዩነት በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሃሳብ አስመልክቶ "ክርስቶስ ... ቤተክርስትያንን እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ" በማለት ይገልፃል (ኤፌ. 5፡25-26)፡፡ በመጀመሪያ አነፃት ከዚያም በኋላ ቀደሳት ቀጥሎም ለጢሞቲዎስ በጻፈው መልዕክቱ "እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ቢያነፃ ለክብር የሚሆን የተቀደሰም ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ ይሆናል" ብሏል (2ኛ ጢሞ.2፡21)፡፡ ቅድስና ከመንፃት በኋላ የሚመጣ እና መንፃትን የሚያልፍ በረከት ነው፡፡

ቅድስና ጠንከር ባለ ቃል በምሣሌ የተገለጸው የካህናትንና የሌዋውያንን ሹመት በማስተያየት ነው፡፡ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ከካህናት ሹመት ባነሰ ያገለግሉ ለነበሩ ቅድስና የሚለው ቃል ሲገለጽ እናይም በእርሱ ፈንታ አምስት ጊዜ መንፃት የሚለው ቃል ተጠቅሶ እናነባለን (ዘኁ.13)፡፡ ካህናት ለአገልግሎት ሲሾሙ ቅድስና የሚለው ብዙ ጊዜ ለእነርሱ ሲነገር እናያለን ይህም ከሌዋውያን ይልቅ የክህነት አገልግሎት ወደ እግዚአብሔር እጅግ የሚያስጠጋ እንደሆነ ያሳያል (ዘፀ.29 እና ዘሌ.8)

ከላይ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመስዋዕቱ ደም እና በቅድስና መካከል የቀረበ ትስስር እንዳለ በአጽንኦት ይገልጻሉ፡፡ የሌዋውያንን ሹመት በተመለከተ በመጀመሪያ



ከኃጢአት መንጻት መፈጸም አለበት፡፡ ስለዚህ ለመንፃት በሚያነፃው ውኃ ይረጫሉ እንጂ እንደ ካህናት በደም አይረጩም የካህናት ሹመት ሲካሄድ ግን ደም በእነሱ ላይ ይረጫል በዚህ ምክንያት ከደሙ ጋር የግልና የቀረበ ግንኙነት ይኖራቸዋል፡፡

እነዚህ ሥርዓቶች ሁሉ በክርስቶስ ደም የመቀደስ ምሣሌዎች ናቸው፡፡ እኛም አብዝተን ለማወቅ የምንጓጓው ይህንኑ ነው፡፡ እንዲሁም ከቅድስናው ተካፋይነትን እናገኛለን፡፡ እስኪ በቅድሚያ የሚከተሉትን እንገንዘብ፡-

- *ቅድስና ማለት ምን ማለት ነው ?*
- *ቅድስና የክርስቶስ መከራ ትልቁ ዓላማ ነው፡፡*
- *ቅድስና በደም አማካይነት ሊገኝ ይችላል፡፡*

## ቅድስና ምንድን ነው ?

ቅድስና ምን እንደሆነ ከማየታችን በፊት በቅድሚያ የእግዚአብሔር ቅድስና ምን እንደሆነ መረዳት አለብን፡፡ እግዚአብሔር ወደር የሌለው ቅዱስ ነው ፡፡ ፍጥረት ቅድስናን መቀበል ያለበት ከእግዚአብሔር ነው፡፡

የእግዚአብሔር ቅድስና እግዚአብሔር ከሚጠላቸው እና በጠላትነት ከሚፈርጀው ከኃጢአት ጋር በማነጻጸር መናገር ቢቻልም እነዚህ ነገሮች ቅድስና ምን እንደሆነ በቂ ገለጻ አይሰጡንም፡፡ እነዚህ ሃሳቦች አንፃራዊ ናቸው የእግዚአብሔር ቅድስና በውስጡ ኃጢአት እንደሌለበት ያሳያሉ፡፡ ቅድስና የእግዚአብሔር የባህሪ መግለጫ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ሁልግዜ ቅዱስ ስለሆነ ነው በከፍተኛ ደረጃ ለቅዱስ ነገር ፈቃድ አለው ያንንም ያደርጋል፡፡ በዚህም ሳቢያ በፍጥረቱ ውስጥ በላቀ ደረጃ ቅድስናን ማየት ይፈልጋል ለፍጥረቱም መስዋዕት አድርጐ ሰጥቷል፡፡

እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅዱስ ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ይህም የሆነው ኃጢአትን በመቅጣቱ ብቻ ሳይሆን የራሱን ህዝብ የሚቤዥም ስለሆነ ነው፡፡ መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ የሚፈልገው ቅድስናው ኃጢአተኞችን እንዲቤዥ ያንቀሣቅሰዋል፡፡ ኃጢአትን የሚቀጣው የእግዚአብሔር ቁጣ እና ኃጢአተኞችን የሚቤዠው የእግዚአብሔር ፍቅር የሚመነጩት ከአንድ ምንጭ ይኸውም ከቅድስናው ስለሆነ ነው፡፡ ቅድስና የእግዚአብሔር ፍጹም ባህርይ ነው፡፡

የሰው ቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ውስጣዊ ስምምነት ነው፡፡ "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" (1ኛጴጥ.1፡15) ተብሎ በተጻፈው ቃል መሠረት የእግዚአብሔርን ፈቃድ

ሁሉ የራስ ፈቃድ አድርጎ መምረጥ ነው። ቅድስና በውስጣችን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ከመሆን የተለየ ነገር አይደለም። የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኘት ውጤት ነው። በቅዱሱ እግዚአብሔር ከመንጻትና የእርሱ ብቻ የሆነውን ቅድስና ከመቀበል በቀር ቅድስና የማግኛ ሌላ መንገድ የለም። እግዚአብሔር ብቻውን ቅዱስና የሚቀድስ ጌታ ስለሆነ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ቅድስና እና ቅዱስ ለሚሉት ቃላት የተለያዩ ትርጉሞች ይሰጣል። ቅድስና ወደ እግዚአብሔር ያቀረበን የግንኙነት መንገድ እንደሆነ ይገልጣል። ቅድስና ለሚለው ቃል የመጀመሪያውና ቀለል ያለው ትርጉም መለየት ማለት ነው። ወይም የእግዚአብሔር ርስት ለመሆንና ለቅዱስ አገልግሎት ተለይቶ መውጣት ማለት ነው። መለየት ስንል ከኃጢአት መለየት ብቻ ሳይሆን በዓለም ካለው ነገር ሁሉ ከተፈቀደው ነገር እንኳ መለየት ማለት ነው። እግዚአብሔር ፍጥረቱን ፈጥሮ ከፈጸመ በኋላ ሰባተኛውን ቀን ቀደሰው። ይህም ማለት የቀሩት ስድስት ቀናት የረከሱ ናቸው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በየቀኑ የፈጠረውን ተመለከተ "እነሆም እጅግ መልካም ነበረ" ይላል ያ ቀን እግዚአብሔር በግሉ ልዩ ሥራ የተጠመደበት ቅዱስ ቀን ነበር። በተመሣሣይ ሁኔታ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ ለየ። ከእስራኤላውያን መካከል ደግሞ ካህናት ለልዩ አገልግሎት ተለይተው ወጡ ለቅድስና የሚደረገው የመለየት ሥራ በእግዚአብሔር የሚሰራ የግል ሥራው ነው። የእግዚአብሔር የምርጫ ጸጋም አብዛኛውን ጊዜ ከቅድስና ጋር የቅርብ ትስስር አለው። "እኔ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና ለእኔም ትሆኑ ዘንድ ከአሕዛብ ለይቻችኋለሁና ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ" (ዘሌ. 20:26)። "እምላክህ እግዚአብሔር የሚመርጠው እርሱ ቅዱስ ይሆናል" (ዘኍ.16:6)። "ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና በምድር ፊት ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር መረጠህ" (ዘዳ.7:6)። እግዚአብሔር ከሌሎች ጌቶች ጋር ቅድስናውን እኩል አይካፈልም እኩል ድርሻም አይወስድም እርሱ ቅድስናውን ለገለጠላቸውና ለሰጣቸው መተኪያ የሌለው ብቸኛ ቅዱስ ገዢ እና ወራሽ ነው። ቅድስና በሚለው ሃሳብ ውስጥ መለየት የሚለው በሙሉ አልተካተተም ነገር ግን ልንከተላቸው የሚገቡ በጣም አስፈላጊ ሁኔታዎች ብቻ ተጠቅሰዋል።

ሰው ከተቀደሰ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ይችላል። ሕይወት አልባ የሆኑ ዕቃዎች እንኳ ለእግዚአብሔር በሆነው አገልግሎት ተለይተው በእግዚአብሔር ፊት ጥቅም ይሰጣሉ። መለየቱ ዋጋ ያለው ይሆን ዘንድ አንድ ነገር መደረግ አለበት፤ሰው ለእግዚአብሔር ከተለየ



በፈቃዱና ከልቡ ምርኮኛ በመሆን ለተለየለት ነገር ራሱን መስጠት አለበት። የጌታ ለመሆን በቅድስና ራስን መስጠትን ይጨምራል።

ቅድስና የእኛ የሚሆነው በፈቃዳችን፣ በፍቅራችን እና በሕይወታችን ውስጥ ስሩን ሰድዶ ሲተከል ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከፈቃዱ ጋር በሚፃረር መልኩ ማንንም ሰው አይቀድስም። የቅድስና ብቸኛ መንገድ ከልብ በግል ለእግዚአብሔር ምርኮኛ መሆን ብቻ ነው። እግዚአብሔር ብቻ እንደሚቀድሰን ቅዱሳት መጻሕፍት አይናገሩም አብዛኛውን ጊዜ ራሳችንን መቀደስ እንዳለብንም ይናገራሉ።

ነገር ግን እውነተኛ ቅድስና እራስን በመስጠት ብቻ የተሟላ ወይም ፍጹም አይሆንም። መለየትና ራስን መስጠት እግዚአብሔር በነፍስ ውስጥ የራሱን ቅድስና እዲሰራ የዝግጅት ተግባራት ናቸው። "የመለኮታዊ ባህሪ ተካፋይነት" ለአማኞች በቅድስና የተሰጠ በረከት ነው። "ከቅድስናው እንድንካፈል..." (ዕብ.12:10) ይህም እግዚአብሔር ለራሱ በለያቸው ውስጥ የሚሰራው የከበረ የዓላማ ሥራ ነው። የቅድስና ተካፋይነት ጉዳይ ከእግዚአብሔር ውጭ የሚሰጥ አንድ የስጦታ ዓይነት አይደለም። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር በግል ከሚደረግ ኅብረት የሚገኝ እና መለኮታዊ ሕይወቱን በመካፈል የሚመጣ ነው።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ለመቀደስ በሕዝቡ መካከል ያድራል (ዘፀ. 29:45-46)። ቅዱሱ እግዚአብሔር በእኛም ውስጥ ይኖራል። መቀደስ የሚችለው የእግዚአብሔር መገኘት ብቻ ነው። እግዚአብሔር በኃይሉ በመካከላችን ሲገኝ እኛ ደግሞ በእርሱ መገኘት ሙላት እንደምንሞላ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እውነተኛ ቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግና የእርሱም በእኛ ውስጥ መኖር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ መኖሪያውን በሥጋ ውስጥ ማድረግ አስፈለገው መንፈስ ቅዱስም በእኛ ውስጥ ለመኖር መጣ ቅድስና ማለት ይሄ ነው።

## ቅድስና የክርስቶስ መከራ ዓላማ ነው

"ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ" (ዕብ.13:12) በማለት በግልጽ ተጽፎአል። የእግዚአብሔር ጥበብ ይኸውም ከቅድስናው ተካፋይ መሆን የሰው መድረሻ ግብ ነው። በተጨማሪም ከመስቀል ሞቱና መከራው ባሻገር የክርስቶስ ኢየሱስ የጌታችን ወደዚህ ምድር የመምጣቱ ማዕከላዊ ዓላማ ነው። ሕዝቡን እንዲቀድስ እና በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን እንሆን ዘንድ (ኤፌ. 1:4) ጌታ ኢየሱስ መከራውን በመቀበል

ቅድስናን እንደፈጸመልን ወደ አብ በጸለየው ጸሎቱ ገልጾታል ቃሉም "እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ" የሚል ነው(ዮሐ. 17፡19)። ክርስቶስ ራሱን የቀደሰው በመከራውና በሞቱ ነው ለእኛም ደግሞ የቅድስና ምክንያት ሆኖልናል። የላይኛው ሃሳብ ምን ማለት ነው? ኢየሱስ "የእግዚአብሔር ቅዱሱ ፣እግዚአብሔር ቀድሶ ወደ ዓለም የላከው" ራሱን መቀደስ ነበረበት ማለት ነው? አዎን መቀደስ ነበረበት ምክንያቱም በጣም ወሳኝ ነገር ስለሆነ ነው።

ክርስቶስ የተሞላው ቅድስና ፈተና ከሚደርስበት በላይ አልነበረም። በፈተናው ውስጥ የእርሱ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ እንዴት ለእግዚአብሔር ቅድስና ምርኮኛ እንደሆነ ማሳየት ነበረበት። የሰው እውነተኛ ቅድስና መለኪያው የእርሱ ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ፍጹም አንድ መሆኑ ነው። ጌታ ኢየሱስ በምድረበዳ ከዲያብሎስ ከተፈተነበት ጊዜ ጀምሮ መላ ሕይወቱን ስንመለከት ፈቃዱን ለአባቱ ፈቃድ ማስገዛቱንና እራሱን መስዋዕት አድርጐ ለእግዚአብሔር መስጠቱን እንመለከታለን። ይህንን በከፍተኛ ደረጃ ተግባራዊ ያደረገው በጌቴሴማኒ ነበር። ያ ጊዜ ሰዓቲቱ የጨለማው ሥልጣንነበር በዚያን ጊዜ የመከራውን ጽዋ ከአፉ መልሶ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ የራሱን ፈቃድ እንዲያደርግ በብርቱ ኃይል ከፊቱ ፈተና የተደቀነበት ጊዜ ነበር። ይሁን እንጂ ፈተናውን እምቢ ብሎ ገፍቶ በመጣል ራሱንና ፈቃዱን ለአባቱ ፈቃድና ቅድስና አሳልፎ ሰጠ። ከአብ ፈቃድ ጋር ፈቃዱን ፍጹም አንድ በማድረግ ራሱን ቀደሰ እኛም ደግሞ በእውነት የተቀደስን እንሆን ዘንድ የእርሱ ቅድስና ኃይላችን ሆነ። ጌታ ኢየሱስ ይህን ያደረገው ያለ ምንም ግፊት በገዛ ፈቃዱ ነው። ስለዚህ ጉዳይ የዕብራውያን መልዕክት እንዲህ በማለት ይገልጸዋል "እነሆ፣ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ" ብሏል። ሁለተኛውን ሊያቆም ፊተኛውን ይሽራል በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል" (ዕብ.10፡9-10)። የገዛ ሥጋውን መስዋዕት አድርጎ በማቅረቡ ምክንያት ለእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ምርኮኛ ሆነ እኛም የተቀደስነው በዚህ ፈቃድ ነው። እኛ በእውነት የተቀደስን እንሆን ዘንድ እርሱ ራሱን ስለ እኛ ቀደሰ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ በእርሱ ይፈጸም ዘንድ በፍፁም ታዛዥነት ራሱን ምርኮኛ አድርጎ ሰጠ። ይህም የሆነው ድነታችንን በመከራው ለመፈጸም ብቻ ሣይሆን በተመሣሣይ ሁኔታ ኃጢአትን ለዘለዓለም ድል ለማድረግ እኛን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና የቅድስናን መሠረት በልባችን ውስጥ ለመጣል ነው። ጌታ ኢየሱስ ህዝቡን የቀደሰው መከራን ከተቀበለ በኂላ ነው (ዕብ.2፡11)። "የሚቀድሰውና የሚቀደሱት ሁሉ ከአንድ



ናቸውና" ይላል። በጌታ ኢየሱስና በሕዝቡ መካከል ያለው አንድነት ምስጢር ሁለቱም ሕይወታቸውን የተቀበሉት ከአብ ነው ሕይወትን በጋራ ይካፈላሉ አንዱን ቅድስናም ይጋራሉ ኢየሱስ የሚቀድሰው ሲሆን ሕዝቡ ደግሞ የሚቀደሱት ናቸው። ስለዚህ ቅድስና ማሰሪያ ሆኖ ሁለቱን አንድ አድርጓቸዋል። ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ" በደም መቀደስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅና ለመለማመድ ፈቃደኞች ከሆንን በቅድሚያ ቅድስና የክርስቶስ መከራ ባህሪይና ዓላማ እንደሆነ መረዳት አለብን ደሙ የበረከት ምክንያትና ፍሬ ነው። ክርስቶስ ራሱን መቀደሱ የእነዚያ መከራዎች ልዩ ባህሪ ሲሆን በውስጡ ዋጋው እና ኃይሉ በአንድነት ተጣምረው ይገኛሉ። የእኛም ቅድስና የእነዚያ መከራዎች ዓላማ ነው ዓላማው ግቡን የሚመታው ፍጹም በረከቱን ሲፈጽም ብቻ ነው በተጓዳኝ ይህ እውነት ለእኛ ግልጽ ሲሆንልን ወደ እርሱ ትክክለኛ የመከራ ትርጉምና ባርኮት እንቀርባለን ወደ ክርስቶስ ትክክለኛ የመከራ ትርጉም በረከት መሄድ እንዳለብን ያሣየናል።

ቅዱሱ እግዚአብሔር መዋጀትን አስቀድሞ ወስኗል። በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው መቀደስ በኃጢአት ላይ በድል አድራጊነት ክብሩን መግለጥ እና ቅድስናውን ከፍ አድርጎ ማሳየት ፈቃዱ ነው። በተመሣሣይ ሁኔታ እኛም ለእግዚአብሔር የተለየን እንሆን ዘንድ ኢየሱስ በትዕግሥት መከራውን ፈጸመ። የክርስቶስ ዓላማ በመከራው ቅድስናን ማምጣት ብቻ አይደለም መንፈስ ቅዱስ ወደ እኛ መጥቶ በክርስቶስ መዋጀታችንን በእኛ ውስጥ በመግለጥ ከእኛ ጋር መኖሩ ሌላው ዓላማው ነው መንፈስ ቅዱስ የቅድስናም መንፈስ ነው።

እርቅ ፣ ይቅርታ እና ከኃጢአት መንፃት በቃላት ሊገለጹ የማይችሉ ከአእምሮ በላይ የሆነ ዋጋ ያላቸው ሆኖም በቀጥታ ወደ ቅድስና ያመለክታሉ። በክቡር የክርስቶስ ደም የታተመ ሁሉ ማህተሙ መለኮታዊ መሆኑን፤ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የመለየቱ ምልክት መሆኑንና በሙሉ ልብ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር እንዲቀድስ ደሙ ጥሪ እንደሚያደርግለት ሊገነዘብ ይገባል። ይህ ደም በእግዚአብሔር ቅድስና ውስጥ የቃልኪዳንና የኃይል ማዕከል እንደሆነና እግዚአብሔርም መገኛውን በእርሱ ውስጥ በማድረግ ለታተመው ሰው አምላኩ እንደሆነ እንዲያውቅ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

## ቅድስናን እንዴት በደም እናገኛለን

በአጠቃላይ ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነን ከደሙ በረከት ተካፋይ የሆነ ማንኛውም ሰው ከቅድስናውም ደግሞ ተካፋይ ይሆናል። ስለዚህ ይህ ሰው በእግዚአብሔር እይታ የተቀደሰ ሰው ነው። በተጓዳኝ ከደሙ ጋር ቅርብ ጥብቅ ግንኙነት አድርጐ የሚኖር ሰው የቅድስና ውጤቶች እንዴት እንደሚከሰቱ አናሳ መረዳት ቢኖረውም እንኳ በሚኖረው ቅርበትና ትስስር ምክንያት በደሙ የመቀደስ ልምምዱ ከዕለት ወደ እለት እየጨመረ ይሄዳል። ነገር ግን ሁሉን ነገር አጠናቆ አውቆ መገኘት እንዳለበት ልንጠብቅበት አይገባም በእምነት ፀሎት ደሙ በውስጡ ታላቅ የመቀደስ ኃይሉን ሊገልጥ ይችላል። በገዛ ደሙ ህዝቡን መቀደስ የሚችለው ጌታ ኢየሱስ ራሱ ነው። በደሙ ወደ ራሱ ላቀረበው የእግዚአብሔር በግ በእምነት አምልኮ እና መቀራረብ ከልቡ ራሱን የጠለ አማኝ ከመረዳቱ በላይ የሆነውን በደም መቀደስን ይለማመዳል ለዚህ አማኝ ይህንን ነገር የሚያደርግለት ጌታ ኢየሱስ ራሱ ነው።

ነገር ግን አማኝ በእውቀትም ደግሞ ማደግ አለበት ወደ ተዘጋጀለት የበረከት ሙላት መግባት የሚችለው በዚህ መንገድ ነው። ቅድስና የተፈቀደልን ነገር ብቻ አይደለም ነገር ግን በደሙ በረከትና በቅድስናችን መካከል ያለውን አስፈላጊ ትስስር ወይም ግንኙነት የማወቅም ኃላፊነት አለብን። ጌታ ኢየሱስ ቅድስናውን በምን ዓይነት መንገድ በውስጣችን እንደሚሰራና በደሙ ቅድስና ያገኘንባቸውን ነገሮች ዓይነተኛ መለያ ማወቅ አለብን።

የቅድስና ሁሉ መጀመሪያ የእግዚአብሔር ለመሆን ለእግዚአብሔር መለየት እንደሆነ ተመልክተናል። የኃጢአት ኃይል መሰበሩን ከኃጢአት እስራት መፈታታችንን ከእንግዲህ ወዲህ የኃጢአት ባሪያ አለመሆናችንን ነገር ግን በደሙ ነፃ ላወጣን ለእርሱ የተለየን መሆናችንን ደሙ አውጆልናል። "በዋጋ ተገዝታችኋል የራሳችሁ አይደላችሁም" ይላል። እኛ የእግዚአብሔር መሆናችንን የሚናገረው የደሙ ቋንቋ ይሄ ነው ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ የእርሱ እንድንሆን ይፈልጋል መርጦናል ገዝቶናልም በዙሪያቸው ካለው ነገር ተለይተው ለጌታ አገልግሎት እንደሚኖሩ ካህናት ደሙን በእኛ ላይ አይነተኛ መለያ አድርጎታል። ይህ የመለየት ሃሳብ ብዙ ጊዜ ደጋግመን በጠቀስነው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ውስጥ በሚከተለው ሁኔታ በግልጽ ተቀምጧል። "ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ እንግዲህ ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና" (ዕብ.13፡ 12-13) ከዚህ ዓለም ከሆነው ነገር



ሁሉ "መውጣት" ቅዱስ የሆነ፣ የነፃ ፣ ከኃጢአተኞች የተለየ የኢየሱስ ዓይነተኛ ዓላማ ነው የተከታዮቹም መለያ መሆን አለበት።

ውድ አማኝ ሆይ ጌታ ኢየሱስ በገዛ ደሙ ቀድሶሃል የቅድስናውን ሙሉ ኃይል እንድትለማመድ ይፈልጋል። በደሙ በመረጨትህ ምክንያት በአንተ ውስጥ የሆነውን ነገር ለማወቅ ትጋ ቅዱሱ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የእርሱ እንድትሆን ይፈልጋል አንዳች ነገር ከእንግዲህ ወዲህ በአንተ ላይ አይሰለጥንም አንተም እንኳ በራስህ ላይ መብት የለህም እግዚአብሔር ለራሱ ለይቶሃል ምክንያቱም በአንተ ላይ ድንቅ ምልክት አድርጓል ያም ምልክት ከቡርና ድንቅ የሆነው በምድር እና በሰማይ የሚገኘው እርሱም የክርስቶስ ደም ነው። የዘለዓለማዊው እግዚአብሔር ልጅ ሕይወት ያለበት በእግዚአብሔር የፀጋ ዙፋን ፊት የሚኖረው ነው። ከኃጢአት ኃይል የመዋጀት ሙሉ ዋስትና የስጠህ የእግዚአብሔር ለመሆንህ ምልክት ይሆን ዘንድ በአንተ ላይ ተረጨ።

ውድ አማኝ ሆይ ስለ ደሙ የቀረበው ትምህርት ሁሉ ለከበረው ለዚህ ኑዛዜ እንዲያበቃህ ጸሎቴ ነው "ጌታ ኢየሱስ በገዛ ደሙ ቀደሰኝ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ነኝ" ለማለት ያብቃህ/ሽ። ቅድስና ከመለየት በጣም የሚበልጥ እንደሆነ ተመልክተናል መለየት የቅድስና ጅማሬ ነው። በተጨማሪም ደግሞ ግላዊ መስጠት ከልብ እና በፍጹም ፈቃደኝነት ለጌታ ቅዱስ ፈቃዱ ለመኖር ምርኮኛ መሆን የቅድስና አንድ ክፍል መሆኑንም አይተናል። የክርስቶስ ደም እኛን ምርኮኛ ለማድረግና ለመቀደስ በውስጣችን የሚሰራው በምን መንገድ ነው? መልሱ ከባድ አይደለም በሚቤዠንና ከኃጢአት ኃይል ነፃ በሚያወጣን በደሙ ኃይል መታመን ብቻ በቂ አይደለም ከሁሉም በላይ የዚህን ኃይል ምንጭ ማወቅና መጠቀም አለብን።

ደሙ ኃይል እንዳለው እናውቃለን ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ ራሱን በፈቃዱ ምርኮኛ አድርጎ በመስጠቱ ነው። በፈሰሰው ደሙ ራሱን ቀደሰ ለእግዚአብሔር እና ለቅድስናው ሙሉ በሙሉ ራሱን አሳልፎ ሰጠ። በዚህ ምክንያት ደሙ ቅዱስ ነው የመቀደስም ኃይል አለው በደሙ ውስጥ የክርስቶስን ሙሉ ምርኮኝነት እናይበታለን። ደሙ ሁልግዜ ክርስቶስ መንገድ ከፋች ሆኖ ለአብ መስጠቱን እና የኃይል ምንጭ እና በኃጢአት ላይ ድል አድራጊ ሆኖ መገለጡን ይናገራል። ወደ ደሙ በቀረብን ቁጥር እና በመርጨት ደም ጥልቅ ሃሳብ ውስጥ ከኖርንና ከተመላለስን "ለእግዚአብሔር ፍጹም ምርኮኛ በመሆን ከኃጢአት ሙሉ በሙሉ የመቤዠት መንገድ ነው" የሚለውን የደሙን ድምጽ በጠራ ሁኔታ እንሰማዋለን።

የደሙ ድምጽ እኛን ለማንቃት ወይም ለማስተማር እንጂ በከንቱ አይናገርም ደሙ የሚናገረው በመለኮታዊና ሕይወት ሰጪ ኃይል ነው። መስዋዕት ሆኖ መሰጠትን ይጠይቃል። በእኛም ውስጥ የሚሰራው በኢየሱስ ውስጥ በሰራበት ትእዛዝ ነው። በገዛ ደሙ ኢየሱስ ስለቀደሰን ለእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ከሙሉ ልባችን ምርኮኛ ከመሆን በቀር ወደ ኋላ የሚያሳስበን ምንም ነገር ሊኖር አይገባም። ነገር ግን ከመሰጠት በኋላ መለየት ቢከተልም እስከ አሁን ያየናቸው እነዚህ ነገሮች ዝግጅቶች ብቻ ናቸው። ሙሉ በሙሉ መቀደስ የሚከሰተው እግዚአብሔር ለእርሱ የተለየውን የራሱ አድርጐ ክብሩን በሙላት ሲገልጥበት ብቻ ነው። "ከእስራኤልም ልጆች ጋር በዚያ እገኛለሁ ድንኳኑም በክብሬ ይቀደሳል" (ዘፀ.29:43) እውነተኛና ፍጹም ቅድስና የእግዚአብሔርን ቅድስና መካፈል ነው።

ደሙ በአጽንኦት ሰማያት እንደተከፈቱ የሰማይ የሕይወት ኃይል ወደ ምድር እንደወረደ ይነግረናል ማንኛውም እንቅፋት እንደተወገደም ይገልጽልናል እግዚአብሔር ማደሪያውን በሰው ውስጥ ማድረግ ችሏል።

ወደ እግዚአብሔር መቅረብና ከእርሱም ጋር የጠበቀ ኅብረት ማድረግ የተቻለው በደም ነው። ሳይቆጥብ ራሱን ለደሙ ምርኮኛ የሚያደርግ አማኝ የእግዚአብሔር መስዋዕትነትና ቅድስና በሕይወቱ  በሙላት የመገለጥን ዋስትና ያገኛል።

ነፍስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የመቅረቧና ከእግዚአብሔር ጋር የመኖሯ ልምምድ፤ በኃጢአት ላይ መንቃትና ኃጢአትን መቃወም እንዲሁም እግዚአብሔርን የመፍራት ዝንባሌ እንዴት የከበረ ቅድስና ነው።

በኃጢአት ላይ ጠንቃቃ ሆኖ መኖር ብቻ ነፍስን አያረካትም መቅደሱ መንጻት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርም ክብር መሞላት አለበት። በክርስቶስ ውስጥ የተገለጠውን መለኮታዊ ቅድስና ውበት መፈለግና ማግኘት የሚቻለው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ ነው ቅድስና ማለት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን፣ ከፈቃዱ ጋር ኅብረት ማድረግ፣ ሕይወቱን መካፈል ፣የእርሱን መልክ መምሰል ነው።

ውድ አንባቢያን "ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ እንግዲህ ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ እምን ሕዝቡን የሚቀድሰው እርሱ ነው ስለዚህ "ወደ እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ" የደሙ ኃይል በእኛ እንዲገለጥ በእርሱ እንታመን ለተባረከው የደሙ ፍሬ ራሣችንን አሳልፈን እንስጥ



ራሱን የቀደሰበት ያ ደም ሰማያትን ለእኛ ለመክፈት ቀዳሚ ሆኖ የገባው ነው ልባችንን ደግሞ የእግዚአብሔር ፀጋ እና ክብር መቀመጫ ዙፋን ሊያደርገው ይችላል። አዎን "ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ" የራሱን ነገር ትቶ ኢየሱስ እንዲቀድሰው ፈቃደኛ የሆነ ሁሉ የእርሱን በረከት ከማግኘት አይጐድልም የክቡር ደሙን ሙሉ ኃይል ለመለማመድ ፍቃደኛ የሆነ ሁሉ ያለ ጥርጥር በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እንደተቀደሰ ግንዛቤ ያገኛል።

"የሰላም አምላክ እርሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ"አሜን።

# ምዕራፍ ስድስት

## ሕያው እግዚአብሔርን ለማገልገል በደም መንፃት

**"አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል"**
**ኤፌ. 2:13**

**"ነውር የሌለው ሆኖ በዘለዓለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያው እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?"**
**ዕብ. 9:14**

በደም አማካይነት ከተቀደስን በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ኅብረት እንድናደርግ ምክንያት የሆነንን ቅድስና መገንዘብ ይኖርብናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅድስናና መቅረብ እጅግ በጣም የሚመሳሰሉ እውነቶች ናቸው። ያለ ቅድስና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖር አይችልም። ቅዱስ ያልሆነ ሰው ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር እንዴት ኅብረት ሊያደርግ ይችላል? በሌላ በኩል ስንመለከት ደግሞ ያለዚህ ኅብረት በቅድስና ማደግ አይቻልም። ቅድስና ሊገኝ የሚችለው ሁልግዜ ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር በሚደረግ ኅብረት ብቻ ነው።

በቅድስና እና በመቅረብ መካከል ያለው ጥብቅ ግንኙነት ግልጽ ሆኖ የሚታየው በናዳብና በአቢዩድ የአመጽ ታሪክ ውስጥ ነው "ሙሴም አሮንን፦ እግዚአብሔር ወደ እኔ በሚቀርቡ እቀድሣለሁ በሕዝቡም ሁሉ ፊት እከብራለሁ ብሎ የተናገረው ይህ ነው አለው..." (ዘሌ.10:3)። እነ ቆሬ በሙሴ እና በአሮን ላይ በአድማ በተነሱ ግዜ ሙሴ የተናገረው እንዲህ በማለት ነበር "ነገ እግዚአብሔር ለእርሱ የሚሆነውን ፣ ቅዱስም የሚሆነውን ያስታውቃል የመረጠውንም ሰው ወደ እርሱ ያቀርበዋል" (ዘሁ.16:5)።

እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን ሲመርጥና ሲለይ ከቅድስና ጋር የጠበቀ ኅብረት እንደሚያደርግ ተመልክተናል። በቅድስና ምርጫ የተጠበቁት ክብር እና ባርኮት እውንነታቸው የሚረጋገጠው ከእግዚአብሔር ጋር ከሚደረግ ቅርበት ውጭ አይደለም። በእግዚአብሔር ክብር እና በእርሱም ፍቅር እንዲደሰት ለተፈጠረው ሰው እውነተኛው እና ከፍተኛው ፍጹም ባርኮት ይሄ ነው። መዝሙረኛው "አንተ የመረጥከው በአደባባዮችህም ለማደር የተቀበልከው ምስጉን



ነው ከቤትህ በረከት እንጠግባለን" ይላል። (መዝ.(65):4)። ለእግዚአብሔር መስጠት እና ወደ እርሱ መቅረብ በባህሪያቸው ተመሣሣይ ነገሮች ናቸው።

ሰውን ለእግዚአብሔር በመቀደስ ወደ እግዚአብሔር መገኛ የሚያስገባው የመርጨት ደም በተመሣሣይ ሁኔታ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ያደርገዋል።

በእስራኤል መካከል ካህናት ለቅዱስ አገልግሎት ሲለዩ ለአገልግሎት የመለየታቸውን ሕግ እንደሚከተለው እናነባለን "የአሮንንም ልጆች አቀረበ ሙሴም የቀኝ ጆሮአቸውን ጫፍ፣የቀኝ እጃቸውንም አውራጣት ፣ የቀኝ እግራቸውንም አውራጣት ከደሙ አስነካ ሙሴም ደሙን በመሰዊያው ዙሪያ ረጨ" (ዘሌ.8:24) ከእግዚአብሔር ጋር የሆኑ ሁሉ ወደ እርሱ በመቅረብ ከእርሱ ጋር የመኖር ኃላፊነት አለባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ናቸውና ይህ እውነት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በታላቁ ሊቀ ካህናችን ሕይወት ተረጋግጧል። ይኸውም "በገዛ ደሙ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት ገባ" (ዕብ.9:12) በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥም ይህ እውነት ይሰራል ቃሉም እንዲህ ይላል "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን ከክፉ ሕሊና ለመንፃት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን" (ዕብ. 10:19-22)። በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ የተጠቀሰው "መግባት" የሚለው ቃል ካህናት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡበት ዓምድ ሆኖ ያገለግላል። በተመሣሣይ ሁኔታ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ በክህነት አገልግሎታችን ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ የታወጀልን በደሙ ኃይል ነው ስለዚህ "ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን" ይልና "ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገን" ይላል። (ራዕይ 1:6) "አለኝም፦ እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፣ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ። ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አለ፣ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል" (ራዕ.7:14:15)። በደሙ ኃይል ለእኛ ከተደረጉልን የከበሩ በረከቶች አንዱ ወደ እግዚአብሔር መገኛ ወደ ዙፋኑ መቅረባችን ነው። ይህ የተባረከ በረከት ምን እንደሆነ መረዳት እንችል ዘንድ እስቲ ይህ የክቡር ደሙ ባርኮት በውስጡ የያዛቸውን ነገሮች በቅድሚያ እንገንዘብ።

- *በመጀመሪያ፡ ዘእግዚአብሔር መገኛ የመኖር መብት ሰጠን*
- *ሁለተኛ፡ መንፈሳዊ መስዋዕት እንድናቀርብ አደረገን*
- *ሶስተኛ፡ የደሙ ኃይል ለሌሎች ባርኮት አመጣ*

## በእግዚአብሔር መገኛ ውስጥ በትክክል መኖር

ይህ እድል በተለይ በእስራኤል ለሚኖሩ ካህናት የተለጠ ሆኖ በእግዚአብሔር መገኛ የመኖር ነፃ እድል እንደነበራቸው እናውቃለን፡፡ ካህናት ሳያሰልሱ በእግዚአብሔር መገኛ በመገናኛው ድንኳን ይኖራሉ እንደ እግዚአብሔር ቤት አባልነታቸው የገበታውን ሕብስት ይበላሉ ከመስዋዕቱ ደግሞ ይካፈላሉ፡፡ እውነተኛ እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ ከዚህ የተሻለ እድል እንደሌለው ያስባል፡፡ መዝሙረኛው ይህንን ሐሳብ ሲገልጽ "አንተ የመረጥከው በአደባባዮችህም ለማደር የተቀበልከው ምስጉን ነው ከቤትህ ከቅዱስ መቅደስህ በረከት እንጠግባለን" (መዝ. (65)፡4)፡፡ በጥንት ዘመን የእግዚአብሔር መገኘት ይገለጥ ስለነበር አማኞች በታላቅ ጉጉት ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች መቼ እደርሳለሁ? የአምላክን ፊት መቼ አያለሁ? በማለት በናፍቆት ይጠብቁ ነበር፡፡ "ወደ እግዚአብሔር መቅረብ" የሚለውን መንፈሳዊ ትርጉም ጥቅም በሚገባ ተረድተውታል፡፡ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ መንፈሳዊ ትርጉም በእግዚአብሔር ፍቅር መታደስ፣ ኅብረት ማድረግ፣ በጥበቃና በበረከቱ ውስጥ መኖርን ይወክላል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ "በአንተ ለሚያምኑ በሰው ልጆች ፊት ያዘጋጀሃት፣ ለሚፈሩህም የሰውርሃት፣ቸርነትህ እንደምን በዛች! በፊትህ መጋረጃ ከሰው ክርክር ትጋርዳቸዋለህ፣ በድንኳንህም ከአንደበት ክርክር ትሸፍናቸዋለህ" በማለት ይዘምራሉ (መዝ. (31)፡19-20)፡፡

ክቡር የሆነው የክርስቶስ ደም አማኞች ወደ እግዚአብሔር መገኛ ይገቡ ዘንድ ከእርሱም ጋር የጠበቀ ኅብረት ያደርጉ ዘንድ የከፈተው መንገድ ጥልቅ መንፈሳዊ እውነታ ነው፡፡ የደሙን ሙሉ ኃይል የተረዳ አማኝ በእግዚአብሔር መገኛ በቅርበት ይኖራል ከዚህ ጋር ከተያያዙት ቃላት በማይገልጣቸው በረከቶች ይደሰታል በዚያ የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር ዋስትና አለው፡፡ ይህን ፍቅር ይለማመዳል በእርሱም ይደሰታል፡፡ ይህን ደስታ የሚሰጠው እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ ዕለት ዕለት የእግዚአብሔር ወዳጅ ሆኖ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እያደረገ ይኖራል፡፡ በፍጹም ነጻነት በሃሳቡና በምኞቱ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ለአብ የታወቀ ሆኖ ይገለጣል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው ቅርበት የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ያገኛል፡፡ መልካም ነገር ሁሉ በእርሱ ዘንድ ስለሚገኝ መልካም ነገርን አይለምንም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለሆነ ነፍሱ በፍጹም እረፍትና ሰላም ትሞላለች ለነፍሱ የሚያስፈልገውን ምሪትና ትምህርት ይቀበላል፡፡ እግዚአብሔር ሁልግዜ



ዓይኖቹን በእርሱ ላይ በማጥናት ይመራዋል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው መቀራረብ ምክንያት ለስላሳውን የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ይሰማል፡፡ ግልጽ የሆነውን የአብን ፈቃድ ለማወቅና ለመከተል ይማራል፡፡ እግዚአብሔር ሁልግዜ ከእርሱ ጋር ስለሆነና ብርታቱም ስለሚሆን ኃይሉ ያለ ማቋረጥ ይታደሳል፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረው የኅብረት ልምምድ በሕይወቱ እና በባህርዩ ላይ አስደናቂ ለውጥ ያደርጋል፡፡ የእግዚአብሔር ህልውና በትህትና በፍርሃትና በተቀደሰ ጥንቃቄ ማስተዋል ይሞላዋል፡፡ በነገሥታቱ ንጉሥ መገኛ ይኖራል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረገው ኅብረት በሕይወቱ እግዚአብሔርን መምሰልን እንዲቀረጽበት ያደርጋል፡፡ የእግዚአብሔርንም መልክ እንደሚመስል መመልከት ይጀምራል፡፡ ከቅዱሱ ጋር በመኖሩ እርሱም ቅዱስ ይሆናል ስለዚህ "ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል መታመኛዬ እግዚአብሔር ነው" ማለት ይችላል (መዝ.(73)፡28)፡፡

የአዲሱ ቃል ኪዳን ልጆች የሆናችሁ ሁሉ መጋረጃው ለሁለት እንደተቀደደ ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ መኖሪያ የሚወስደው ሕያው መንገድ እንደተከፈተ ደጋግማችሁ አልሰማችሁምን? ምናልባት ይህ ታላቅ እድል ፍላጎታችንን ይቀሰቅሰው ይሆናል ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር መኖርና እርሱም ከእኛ ጋር ከመኖሩ የበለጠ ሊያረካን የሚችል ነገር የለም፡፡ እውነተኛ የክርስትያን ሕይወት ይሄ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት የምንባረከው ድነታችን ደስታ ብቻ አይደለም፡፡ ወደ እግዚአብሔር ቀርበን በምናበረክተው አገልግሎትም ጭምር ነው እስቲ በጥንቃቄ እንገንዘብ፡፡

## መንፈሳዊ መስዋዕት ለእግዚአብሔር የማቅረብ አገልግሎት

ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ መስዋእት እንድናቀርብ የተሰጠን እድል ከሁሉ የላቀ ነው፡፡ ካህናት በእግዚአብሔር ማደሪያ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ እና ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን በመስጠት ይደሰታሉ፡፡ የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ የቅዱሱ ስፍራ አገልጋዮች በመሆን ሁልግዜ በተቀደሰው ስፍራ ይኖራሉ፡፡ ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ ብቻ እውነተኛውን ደስታ ያገኛሉ አገልግሎቱም እውነተኛ የበረከት አገልግሎት ይሆንላቸዋል፡፡

አገልግሎቱም ከሚያካትታቸው ነገሮች ዋና ዋናዎቹ የሚረጨው ደም መቅረብና በመልካም መዓዛው ማደሪያውን የሚያውደው ዕጣን መዘጋጀት አለባቸው፡፡ ለማደሪያው ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ በቃሉ መሠረት ይሰናዳሉ፡፡ ካህናቱም ከፍ ባለው ልዑል ማደሪያ ተገኝተው ማደሪያውን መጠበቅ፣ማገልገልና ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን ነገር ማዘጋጀት አለባቸው እነዚህ ነገሮች ለእግዚአብሔር እና ለክብሩ ስለሚገቡ መከናወን ይኖርባቸዋል መልካም ፈቃዱም በእነርሱ ውስጥ ይፈጸማል፡፡

የክርስቶስ ደም ወደ እግዚአብሔር ካቀረበን በፊቱ አገልጋዮች ሆነን እንድንኖር ደግሞ ያደርገናል፡፡ በአይኖቹ ፊት ደስ የሚያሰኘውን መንፈሳዊ መስዋዕት እናቀርባለን፡፡ ካህናት የመስዋዕቱን ደም በቅድስት ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ያቀርባሉ፡፡ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት የበጉን ደም ከማመንና ከማክበር የበለጠ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መስዋዕት ማቅረብ አንችልም፡፡ ማንኛውም ትህትና የሞላበት መታመን እና ልባዊ ምሥጋና ማቅረብ እግዚአብሔር በደሙ ላይ ያለውን የከበረ ሃሳብ ማጉላት ነው፡፡ ምሥጋናውንም መናገር በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት አለው በእግዚአብሔር ዘንድ መኖራችን እና ወደ እርሱም መቅረባችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ደሙን በእግዚአብሔር ፊት የሚያከብር መሆን አለበት፡፡

ካህናት የመስዋዕቱን ዕጣን ወደ ቅድስት ስፍራ ይዘው ሲመጡ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነው የመገናኛው ድንኳን በእጣኑ መልካም መዓዛ ይሞላል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጸሎት መልካም መዐዛ ያለው እጣን ሆኖ ማደሪያውን እንዲከብብ ያስፈልጋል፡፡ የፀሎት ዋጋ የምንፈልገውን ነገር ማግኛ ብቻ ተደርጐ መታሰብ የለበትም ጸሎት ከዚያም ያለፈ ዓላማ አለው ይኸውም እግዚአብሔርን የሚያስደስት አገልግሎት መሆኑ ነው፡፡

ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ በደሙ እውነተኛ ደስታን የሚለማመድ የአማኝ ሕይወት የማያቋርጥ የጸሎት ሕይወት ያለው ነው፡፡ በእያንዳንዱ እርምጃና ሁኔታ ውስጥ በእግዚአብሔር ላይ በጽኑ ለመደገፍ ጸጋ ያስፈልጋል፡፡ በተባረከው በእግዚአብሔር ቅርበትና የማይለወጥ መልካምነት ምክንያት ነፍስ በእውነተኛ እምነት ራሷን ስታፈስስ ማናቸውም ቃልኪዳኖች ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡ የእግዚአብሔር የፊቱ ብርሃን ሲያበራ በተመሣሣይ ሁኔታ ከጸሎት ከምሥጋና እና ከአድናቆት ጋር የነፍስ ደስታ መስዋዕት ሆነው ይቀርባሉ፡፡ የእግዚአብሔር ካህናት ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የከንፈር ፍሬ መንፈሳዊ መስዋዕቶች ናቸው፡፡ በደሙ አንድ ግዜ ተቀድሰውና ወደ እርሱ ቀርበው በፊቱ ይመላለሳሉ ይኖራሉም፡፡



እዚህ ላይ መታሰብ ያለበት አንድ ዋና ነገር አለ ይኸውም ለእግዚአብሔር ቤት በሆነው አገልግሎት መንፃትም ሆነ የሚያስፈልገውን ነገር ማዘጋጀት የካህናት ሥራ ነው ዛሬ በአዲስ ኪዳን ያለው አገልግሎት ምንድን ነው? ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁንና ለመንፈሳዊ አምልኮ የተለየ ውጫዊ ሥርዓት አያስፈልገውም በፊቱ እንዲመላለስ አብ የጠራው ሁሉ ከውጫዊ ሥርዓት ይልቅ መንፈሳዊ ሥርዓት እንዲፈጽም ታዟል ይህም አገልግሎት መንፈሳዊ መሥዋዕት ተብሎ ተጠርቷል፡፡ አማኝ የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር በእግዚአብሔር ፊት ለእርሱ በሆነው አገልግሎት የሚቀርብ ከሆነ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ የክህነት አገልግሎት ማለት ነው፡፡ "እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት" (1ቆሮ. 10፡31)፡፡ "እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሠገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት" (ቆላ.3፡17)፡፡ በዚህ መንገድ መደረግ የሚገባውን የምናደርግ ከሆነ ድርጊታችን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የምሥጋና መስዋዕት ይሆናል ሆኖም ግን ሙሉ በሙሉ ራሣቸውን በመስጠት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብን ክብር የተገነዘቡ ክርስትያኖች በቁጥር በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡

መንጻት፣ መቀደስ እና በደሙ ኃይል ወደ ጸጋው ዙፋን መቅረብ ምድራዊ ጥሪዬ እና የሕይወቴ ማዕከል ነው፡፡ መብላቴና መጠጣቴ እንኳ መንፈሳዊ አገልግሎት ነው፡፡ ሥራዬ፣ንግዴ፣ገንዘቤ፣ቤቴ፣የማደርገው ማንኛውም ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር መገኘት የተቀደሰ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም እኔ ራሴ በእግዚአብሔር ፊት በእምነት እመላለሳለሁ፡፡ ከምድር ሥራዎች ዝቅታው የክህነት አገልግሎት ነው ምክንያቱም የሚሰራው የእግዚአብሔር መቅደስ በካህኑ ስለሆነ ነው፡፡ ይህም እንኳ ቢሆን ወደ እግዚአብሔር የመቅረብን በረከት ክብር አይገልጥም፡፡ የክህነት አገልግሎት ከፍተኛው ክብርና በረከት ሌሎችን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት መቅረቡ ነው፡፡

## የደሙ ኃይል ለሌሎች በረከት ለማምጣት

ወደ እግዚአብሔር ሙሉ ክብር መቅረብን የሚሰጠን የደሙ ኃይል ነው፡፡ በእስራኤል ውስጥ ካህናት በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ መካከል የሚቆሙ መካከለኞች ናቸው፡፡ እነርሱ የሕዝቡን ኃጢአትና መስዋዕቱን ይዘው በእግዚአብሔር ፊት ይቀርባሉ የሕዝቡንም ጥያቄ ያቀርባሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ የኃጢአት ይቅርታ የመንገር እና ሕዝቡን የመባረክ ኃይል ተቀብለው ያውጃሉ፡፡ ይህ የአዲስ ኪዳን ክህነት የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለሆነ አማኝ

ሁሉ የተሰጠው መብት ነው በአዲስ ኪዳን እያንዳንዱ አማኝ ካህን ነው። እግዚአብሔር የተዋጃችሁን በደሙ በኩል ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ሲፈቅድ እነርሱ ተባርከው ለሌሎች የበረከት ምክንያት እንዲሆኑ ነው። ካህን በመካከለኝነቱ ለደካሞች የሚራራ ልብ ሊኖረው ይገባል። በመቅደሱ ውስጥ የእግዚአብሔርን በረከት ተቀብሎ ከዚያ ሲወጣ ለሌሎች ያስተላልፋል። በተጨማሪም በደሙ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር በመቅረብና በመጠጋት ታላቁ የክህነት ኃይልና ክብር ይገለጥበታል።

የክህነት አገልግሎት በሁለት መንገድ መለማመድ እንችላለን የመጀመሪያው በምልጃ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአገናኝ መሣሪያነት ነው።

## በምልጃ

የእግዚአብሔር ልጅ ለሆነ ሁሉ ከተሰጡት ከፍተኛ አገልግሎቶች  አንዱ የምልጃ አገልግሎት ነው። ምልጃ ማለት በዓለም ውስጥ ለተፈጠረ ችግር ወይም ለአንድ ግለሰብ ወደ እግዚአብሔር ልመናን በማፍሰስ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ከእግዚአብሔር እንዲያገኝ መማፀን ማለት ነው። ሆኖም ይህ ብቻ በቂ አይደለም። በዚህ መንገድ ረጅም ርቀት መሄድና በረከትን ማምጣት ከተቻለ መልካም ነው ነገር ግን የምልጃ አገልግሎት ዓላማ ከዚህ የላቀ እና ኃይሉ ያለው በእምነት ጸሎት ውስጥ ነው ይህ የእምነት ጸሎት ፍላጎታችንን በእግዚአብሔር ፊት አፍስሰን ለእርሱ ከምንተወው በጣም የተለየ ጸሎት  ነው።

በእውነተኛ የእምነት ጸሎት ውስጥ ማላጁ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች የራሱ በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፍ አለበት። የተስፋ ቃሉ ከሚማልድበት ነገር ጋር ይስማማ እንደሆነ ከመንፈስ ቅዱስ ለመስማት ራሱን መስጠት አለበት። የምልጃው ዐብይ ርዕስ የሆኑትን ኃጢአትንና ችግርን የራሱ አድርጎ በመሸከም በተስፋው ቃል ፊት መቅረብ አለበት። ጸሎቱ መልስ እንዳገኘ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል የማላጁን እምነት እስከሚያነቃ ድረስ በእግዚአብሔር ፊት መቆየት አለበት። ምናልባት በዚህ መንገድ ወላጆች ለልጆቻቸው፣አገልጋዮች ለጉባኤው፣ በእግዚአብሔር የወይን እርሻ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ለሕዝቡ ይጸልያሉ ጸሎታቸው መልስ ማግኘቱን የሚያውቁት እግዚአብሔር በመንፈሱ እምነታቸውን ሲያነቃ ነው። በኃይሉ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበን የጸሎታችንን መልስ እስክንቀበል ድረስ  አስደናቂውን ትጋት የሚሰጠን ደሙ ነው።



በእግዚአብሔር ፊት መኖር ምን ማለት እንደሆነ በትክክል ከተረዳን በተቀደሰ የክህነት አገልግሎታችን ውስጥ ብዙ ኃይል ይገለጣል።

## እንደንዋየ ህልየት /የሙዚቃ መሣሪያ

የክህነታችን ተጨማሪ ማረጋገጫ ለሌሎች በመማለድ በረከት ማምጣት ብቻ ሳይሆን በአገልግሎት እንደ ንዋየ ህልየት በመሆንም ጭምር ነው። እያንዳንዱ አማኝ በፍቅር ተገፋፍቶ ሌሎችን እንዲያገለግል ተጠርቷል ለሌሎች በረከት እንዲሆንና እግዚአብሔር እርሱንም እንዲባርከው ነው። እርካታ በሌላቸው አማኞች ለሌሎች በረከቱን የሚያመጣው ኃይል በእነርሱ ውስጥ አይሰራም። በቃላቸው በሌሎች ላይ ተጽዕኖ የሚያመጣ ኑሮ እንዳላቸው ቢናገሩም ነገር ግን እንደሚናገሩት አይደሉም በመቅደሱ ውስጥ የማይኖሩ ከሆነ የሚያስደንቅ ነገር በሕይወታቸው አይታይም (ዘዳ.10:8) "በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቃልኪዳን ታቦት ይሸከም ዘንድ እርሱንም ለማገልገል በእግዚአብሔር ፊት ይቆም ዘንድ በስሙም ይባርክ ዘንድ እግዚአብሔር እስከ ዛሬ ድረስ የሌዊን ነገድ ለየ።" የክህነት ባርኮት ኃይል መሠረቱ በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ የክህነት ሕይወት ነው። የደሙን ኃይልና ጥበቃ በግሉ የሚለማመድ ካህን ተስፋቢሶችንና ደካሞችን ደሙ እንደሚያድን በማመን እንዲበረታቱ ምክንያት ይሆናቸዋል። ቅዱሱ ሕይወት ሰጪ የደሙ ኃይል ክርስቶስ ደሙን በማፍሰስ ሌሎችን ለመቤዠት ራሱን መስዋዕት እንዳደረገ በካህኑም ሕይወት ተመሣሣይ ነገር ያደርጋል።

ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ቅርበት ፍቅራችን በእግዚአብሔር የፍቅር እሳት ይፈተናል። እግዚአብሔር በእርግጠኝነት የሚሰራበት እምነታችንም ይጠነክራል። የክርስቶስ መንፈስ በውስጣችን ሆኖ በትህትና በጥበብ እና በኃይል እንድንሰራ ያደርገናል ድካማችንን እና አለመብቃታችንን የእግዚአብሔር የሥራ መሣሪያ አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል። ከልምድና ተሞክሮአችን እንደምንማረው በረከት የሚፈስልን እውነተኛ በረከት በሆነው በእርሱ ዘንድ ስንኖር ነው በተጨማሪም በእግዚአብሔር በረከት ሳይሞላ ማንም ሰው ወደ እርሱ ሊቀርብ አይችልም። የተዘጋጀልን ሕይወት የተወደደ የከበረና የተባረከ ፣ ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ በበረከቱ የምንደሰትበት የቤቱን አገልግሎት የምንፈጽምበት በረከቱን ለሌሎች የምናስተላልፍበት አይደለምን?

ማንም ሰው ይህ ሙሉ በረከት የእርሱ እንዳልሆነና እንዲህ አይነቱ ሕይወት ከእርሱ እጅግ የራቀ እንደሆነ አድርጐ ሊያስብ አይገባውም። የኢየሱስ ክርስቶስ የደሙ ኃይል ለእኛም ደግሞ ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ ዋስትናችን ነው። ይህ የሚሆነው ራሣችንን በሙሉ ለጌታ የሰጠን እንደሆነ ብቻ ነው።

እነዚህን በረከቶች በትክክል ለሚፈልግ ሁሉ የሚከተሉትን ምክሮች እለግሣለሁ ከበረከቶቹ ከአንዱም እንድትጎድል እንዳልተደረግህ አስብ የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን ሁላችን በደሙ ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ ተደርገናል። ሁላችንም የደሙን ሙሉ ኃይል የመለማመድ ፍላጎት ሊኖረን ይችላል። ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ሕይወት ለእኔ የተተወ ውሣኔ ነው የሚለውን እያንዳንዳችን በግላችን እንያዝ ከልጆቹ አንዱ ከዚህ በረከት እንዲጐድል የአብ ፈቃድ አይደለም። ከዚህ በረከት ርቆ በመኖር እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አንችልም። እኛ ካህናት ነን በክህነት እንድንኖር የሚያስችለን ፀጋ ተዘጋጅቶልናል መኖሪያችን ወደ ሆነው ወደ መቅደሱ በነፃ መግባት ተሰጥቶናል። ለዚህ እርግጠኛ መሆን እንችላለን ልጆቹ እንደመሆናችን እግዚአብሔር ቅዱስ መኖሪያውን እንድንኖርበት ሰጥቶናል ሳንጠራጠር ይህንን እውነት በልባችን እንቀበል።

ከነ ባርኮቱ የደሙ ሙሉ ኃይል የአንተ እንዲሆን ፈልግ ይህ ባርኮት እውን የሚሆነው በደሙ ኃይል ነው በደሙ የማስታረቅ ኃይል እምነት ልብህ የተሞላ ይሁን። መጋረጃው ሙሉ በሙሉ ተቀድዷል ወደ እግዚአብሔር እንዳንቀርብ ከልክሎን የነበረው የኃጢአት ኃይል ለዘለዓለም ተወግዷል። ኃጢአት አንተን ከእግዚአብሔር ፊት ለቅጽበት መለየት የሚያስችለው ኃይል ስለሌለው በደስታና በሐሴት ኑር። ጽድቅ በሙላት የተሰጠህ በደሙ እንደሆነ እመን ከዚያም በኋላ እንደ ጻድቅ በመቅደሱ ውስጥ ስፍራ ይኖርሃል ደሙ እንዲያነፃህ ፍቀድ በውስጥህ ሆኖ ከሚያረክስህ ኃጢአት ነፃ የሚያወጣው ኀብረት እንደሚከተል ታመን። "የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያው እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነፃ ይሆን" የሚለውን ቃል ደጋግመህ ተናገረው። ደሙ ይቀድሳችሁ፤ ለእግዚአብሔር በመስጠት ተለይታችሁ በእርሱ እንድትሞሉ ያድርጋችሁ የኃጢአት ይቅርታ፣ መንጻት እና በደሙ የመቀደስ ኃይል በውስጣችሁ በነፃነት ይንቀሳቀስ ከዚያም በኋላ እነዚህ ነገሮች እንዴት እናንተን ወደ እግዚአብሔር እንዳቀረባችሁና እንደጠበቃችሁ መገንዘብ ትጀምራላችሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እናንተን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ የደሙን ኃይል በውስጣችሁ እንደሚገልጠው ያለ ፍርሃት ተጠባበቁ ደሙ የፈሰሰው እኛን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ



ለማድረግ ነው ደሙ በአንተ ውስጥ ሥራውን በመፈጸም ሙሉ ይሆናል። ደሙ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት በሰው ቋንቋ የማይነገር ብቃትና ክብር አለው።

በደም የሚረጨው የሥርየት መክደኛ የእግዚአብሔር የጸጋ ዙፋን መቀመጫ እና እግዚአብሔር ለመኖሪያነት የመረጠው ስፍራ ነው። ለደሙ ሙሉ በሙሉ ምርኮኛ ወደ ሆነ ልብ በሙሉ ደስታና ሐሴት ይቀርባል። ደሙ ማንም ሊቋቋመው የማይችለው ኃይል አለው። በደሙ ኃይል ኢየሱስ ከመቃብር ተነስቶ ወደ ሰማየ ሰማያት ገባ። ደሙ በራሱ ሕይወት የመስጠት መለኮታዊ ኃይሉ አንተን/ አንቺን እለት በእለት በእግዚአብሔር መኖሪያ እንደሚጠብቃችሁ እርግጠኛ ሁኑ።

ደሙ ክቡር እና ኃያል እንደሆነ ሁሉ የአንተም እምነት ጽኑ ከሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለህ መኖሪያ እውነተኛና የተረጋገጠ ይሆናል። "ልብሳቸውን አጥበው በበጉ ደም አነጹ ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፣ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል" የሚለው ቃል ስለ ዘለዓለማዊው ክብር ይናገራል ለምድራዊ ሕይወታችንም ደግሞ ይሆናል። የእምነታችን ሙላትና የደሙ ኃይል ልምምዳችን ሲጨምር ወደ እግዚአብሔር መቅረባችንም እየጨመረ ይሄዳል ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የመቅረባችንም ጉዳይ የተረጋገጠ ይሆናል። በዚህ ምድር እግዚአብሔርን በመቅደሱ ያለማቋረጥ ለማገልገል በሩ በስፋት ይከፈታል ሕያው እግዚአብሔርን የማገልገል ኃይል በጨመረ ቁጥር የክህነት ባርኮት ባለጠግነት በዙሪያህ ባሉት ላይ እየበዛ ይሄዳል። አ! ጌታ ሆይ ይህ ቃል በሙሉ ኃይሉ አሁንና ለዘለዓለም በእኛ ላይ ይሰራል አሜን!

# ምዕራፍ ሰባት

## በደሙ አማካይነት "በቅድስት" ውስጥ መኖር

**"እንግዲህ፣ወንድሞች ሆይ፣ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፣ በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፣ ከክፉ ሕሊና ሰመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንን በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ።"**

**ዕብ. 10:19-22**

እነዚህ ቁጥሮች የዕብራውያን መልዕክት ዋና ሐሳብ ማጠቃለያ እና የእግዚአብሔር ጸጋ የምሥራች ናቸው። መንፈስ ቅዱስ መልዕክቱ ለተጻፈላቸው ለዕብራውያን ሰዎች የበረከት ምክንያት እንዳደረገላቸው ለእኛም ደግሞ አድርጎልናል። በኃጢአት ምክንያት ሰው ከእግዚአብሔር መገኛ እና ኅብረት ከኤድን ገነት ተገፍቶ ከወጣ ጀምሮ እግዚአብሔር ከሰው ውድቀት መጀመሪያ አንስቶ የተበላሸውን ኅብረት ለመመለስ ሲፈልግ ኖሯል።

እስከ ዘመኑ ፍጻሜ እግዚአብሔር ለእስራኤል የአካሉ ጥላ ወይም ምሣሌ በሆነው በመገናኛው ድንኳን ሕዝቡን ከልሎ የነበረው መጋረጃ ተወግዶ የእግዚአብሔር ሕዝብ በእግዚአብሔር መገኛ የሚኖሩበትን ቀን በናፍቆት እንዲጠብቁ ሰጥቷቸው ነበር። "መቼ እደርሳለሁ የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?" የሚለው ጥያቄ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ናፍቆት ነበር። ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ እንደተከፈተ ያላወቁ የብዙዎቹ የአዲስ ኪዳን አማኞች የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆችም መቃተት ሆኗል። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ እውነተኛ መኖሪያውን እንዳገኘ ማወቅ አለበት።

አ! ወንድሞቼና እህቶቼ ኢየሱስ የፈጸመላችሁን የመዋጀት ሙሉ ኃይል ምን ያህል ጊዜ ትለማመዳላችሁ? እስቲ ከእኔ ጋር ኑና በአምላካችን ስለተከፈተው ቅዱስ ስፍራ የሚናገረውን እና በደሙም በኩል መግባት እንድንችል የሰጠንን ነፃነት እንመልከት።

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ አንቀጽ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረን ያደረገው ነገር ምን እንደሆነ በአራት ተከታታይ ሐሳቦች ያሣየናል። በሚቀጥሉት አራት ተከታታይ ሐሳቦች ወደዚያ ኅብረት ለመግባት እንዴት እንደምንዘጋጅ እና በእርሱም እንደምንኖር ያስተምሩናል።

ከላይ የተሰጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በጥንቃቄ ካነበብነው "እንቅረብ" የሚለውን ቃል እናገኛለን ይህ ቃል የምንባቡ ማዕከል ነው እስኪ የሚከተለውን እንገንዘብ



- *በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለእኛ ምን አዘጋጀ?*
- *ሁለተኛ እግዚአብሔር ለእኛ ላዘጋጀው ነገር እኛን እንዴት አዘጋጀን*
- *በመጨረሻም "እንቅረብ" የሚሉት ናቸው።*

**"እንግዲህ፣ወንድሞች ሆይ፣ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን፣ በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን፣ ከክፉ ሕሊና ሰመንፃት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ"**

ዕብ. 10:19-22

## እግዚአብሔር ለእኛ ምን አዘጋጀ ?

**ሀ. ቅድስትን**

"እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት... እንድንገባ... እንቅረብ" የኢየሱስ የመዋጀት ሥራ እኛን ወደ ቅድስት በማምጣት ያበቃል። ቅድስት ምን እንደሆነች የማያውቅ የመዋጀትን ሙሉ ደስታ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም። ቅድስት ምንድን ነው? ቅድስት ከፍ ያለ የልዑል እግዚአብሔር መኖሪያ ስፍራ ነው። ይህ መጠሪያ ስም ለማያትን ብቻ አያመለክትም ነገር ግን የእግዚአብሔር መገኛ የሆነው መንፈሳዊ ቅዱስ ስፍራ ጭምር ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ከምድራዊ ነገር የተሰራ መቅደስ ነበር (ዕብ. 8:2፣9:1) እርሱም የእግዚአብሔር መኖሪያ ሲሆን ካህናት በዚያ እየተገኙ እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር። በአዲስ ኪዳን ዘመን ግን እውነተኛ መንፈሳዊ ድንኳን አለ ይህም ድንኳን የትኛውንም የተለየ ስፍራ አያመለክትም። "ቅድስት" የሚባለው እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥበት ስፍራ ሁሉ ማለት ነው (ዮሐ. 4:23-25)።

ወደ ቅድስት ውስጥ መግባት በዚያ መኖርና በእግዚአብሔር ፊት ቀኑን ሁሉ መመላለስ ምን ያህል የከበረ እድል ነው። በዚያ ምን ያህል የብልጽግና በረከት ይፈስ ነበር! በቅድስት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ኅብረትና የእርሱ ውስታ ያስደስታል በዚያ ሕይወትንና የእግዚአብሔርን ባርኮት መለማመድ ይቻላል። የእግዚአብሔር ኃይልና ደስታ በዚያ አለ። በቅድስት ውስጥ ሕይወት የሚያልፈው በክህነት ንጽህና እና መለየት ነው በቅድስት ውስጥ ጣፋጭ ሽታ ያለው እጣን ይቃጠላል ተቀባይነት ያለው መስዋዕት

ለእግዚአብሔር ይቀርባል በቅድስት ውስጥ ያለው ሕይወት የተቀደሰ የጸሎት ሕይወትና ባርኮት ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የምናገኘው ነገር ሁሉ ምድራዊ ነበር። መቅደሱ ራሱ ከምድራዊ ነገር የተሰራ እና በአካባቢ የተወሰነ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ነገር ግን መንፈሳዊ ነው። እውነተኛ መቅደስ ሕልውናውን የሚያገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እውነተኛ ሕይወት በቅድስት ውስጥ እውን ይሆናል። የብሉይ ኪዳን ካህናት እግዚአብሔር በመካከላቸው ሲመላለስ ያውቁ እንደነበር ማወቅ ይቻላል ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸመውን ሥራ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ እውን ያደርገዋል።

በኢየሱስ ክርስቶስ ያላችሁ አማኞች ሆይ! ወደ ቅድስት ለመግባት እና በዚያ ለመኖር ድፍረቱ ወይም ነፃነቱ አላችሁን? መኖሪያችሁን የትም ቦታ ሳይሆን እንደ ተዋጀ ሰው በቅድስት ውስጥ ማድረግ ተገቢ ነው። ክርስቶስ ሙሉ የመዋጀት ኃይሉን ባልሆነ ቦታ አይገልጥም። ነገርግን በቅድስት ውስጥ በብልጽግና ሊባርካችሁ ይችላል። በትክክል ከተገነዘባችሁ የእግዚአብሔር አብ እና የኢየሱስ ክርስቶስ ዓላማ የእናንተም ደግሞ ይሆናል። በዚህን ጊዜ ወደ ቅድስት ውስጥ የመግባት ምኞታችሁ፣ በእርሷ ውስጥ የመኖር ፍላጎታችሁ እና በውስጥዋ የማገልገል መሻታችሁ ፍፃሜ ያገኛሉ። ወደ ቅድስት በክብር ገብተን የምንኖርበትን ትክክለኛ ግንዛቤ መንፈስ ቅዱስ ሲሰጠን እንደሚችል በመተማመን መጠበቅ እንችላለን።

## ለ. በደሙ አማካይነት ነፃነት

ቅድስት በእግዚአብሔር ዘንድ እንዳለች ሁሉ ወደ ቅድስት የመግባት ፍቃድም ያለው በእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ወደ ቅድስት መግባትንም ሆነ ዝግጅቱን ያደረገው እግዚአብሔር ራሱ ነው። እኛ ደግሞ በክርስቶስ ደም አማካይነት ወደ ቅድስት የመግባት መብት ነፃነት እና ድፍረት አለን። የክርስቶስ ደም ይህን የመሰለ አስደናቂ ኃይሉን ስለገለጠ በእርሱ በኩል ኃጢአተኛ ሰው ወደ ቅድስት ማለትም ወደ መለኮታዊ ቅድስት በሙላት የመግባት ነፃነት ያገኛል "አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል" ይላልና ። (ኤፌ. 2:13)

ደሙ ይህን የመሰለ አስደናቂ ኃይል የሚያደርገው እንዴት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "የሥጋ ሕይወት በደም ውስጥ ነውና" (ዘሌ. 17:11) የደሙ ኃይል ያለው



በሕይወት ዋጋ ውስጥ ነው በክርስቶስ ደም ውስጥ የመለኮታዊ ሕይወት ኃይል ይኖርበታል፣ ይሰራበታል። ደሙ ሁሉን ቻይነትንና የማይገሰስ ኃይሉን ይዞ በእርሱ ውስጥ ይኖራል።

ነገርግን ያ ደም መጀመሪያ እስካልፈሰሰ ድረስ የማስታረቅ ኃይሉን መግለጥ አልቻለም ነበር። ጌታ ኢየሱስ የኃጢአትን ቅጣት ሞትን በመሸከም የኃጢአትን ኃይል አሸንፎ ዋጋ ቢስ አደረገው። ይኸውም "የኃጢአት ኃይል ሕግ ነው" ኢየሱስ ከሕግ እርግማን በታች ሆኖ ደሙን በማፍሰስ ሕግን ያለ ነቀፌታ ፈጸመ። ደሙ ኃጢአትን ሙሉ በሙሉ ኃይል አልባ አደረገው ስለዚህ ደሙ አስደናቂ ኃይሉን የተቀዳጀው የእግዚአብሔር ልጅ ሕይወት በውስጡ ስላለበት ብቻ ሳይሆን የኃጢአት ማስተሰሪያ ተደርጎ ስለተሰጠም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደሙ የሚሰጠው ጥልቅ ትርጉም በዘለዓለም ኪዳን ደም እግዚአብሔር ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን አወጣው የሚል ነው። (ዕብ. 13:20)

በገዛ ደሙ ወደ ቅድስት ገባ (ዕብ. 9:12)። የደሙ ኃይል የኃጢአትን ኃይል፣ ሞትን ፣ መቃብርን፣ ሲኦልን፣ ሙሉ በሙሉ ኃይላቸውን አወደመ ድል ነሣቸው። ስለዚህ እኛም ደግሞ ከተጽእኖአቸው መውጣታችንም ተረጋገጠ። ይህም ብቻ አይደለም የደሙ ኃይል ለማያትን ከፈተ ስለዚህ እኛም በነፃነት የመግባታችን ጉዳይ ተረጋገጠ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

ስለዚህ አሁን በደሙ ወደ ቅድስት የመግባትን ነፃነት አግኝተናል አስቀድሞ ኃጢአት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ነፃነታችንን ነጥቆን ነበር። ሆኖም ደሙ ያሰ እንክን ወደዚህ ነፃነት መለሰን። ጊዜ ወስዶ የደሙን ኃይል የሚያሰላስልና የግሉ አድርጎ በመውሰድ የሚያምነው አስደናቂውን ነፃነቱን የሚያይበት ዓይኖቹ ይከፈታሉ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለው ቅርበት ምሪት ሊያገኝ ይችላል።

ኦ! በመለኮታዊ አስደናቂ የደሙ ኃይል ወደ ቅድስት መግባት መቻላችን እንዴት ድንቅ ነው ደሙ ለማይለወጠው ዘለዓለማዊ ፍሬ ለእኛ እና በእኛ ይማልዳል። ኃጢአትን ከእግዚአብሔር እይታና ከእኛ ሕሊና ውስጥ አስወገደው በደሙ በኩል በእያንዳንዷ ቅጽበት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ እና በሙላት የመግባት ነፃነት አለን። መንፈስ ቅዱስ የደሙን ሙሉ ኃይል ሊገልጥልን ይችላል። መንፈስ ቅዱስ በሚያስተምረን ወደ እግዚአብሔር አብ መቅረብ እና በሙላት መግባት እንደሰታለን፤ ሕይወታችን በደሙ በኩል በቅድስት ውስጥ ነውና።

## አዲስና ሕያው መንገድ

"እንግዲህ፣ ወንድሞች ሆይ፣ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደ ቅድስት በኢየሱስ ደም በመጋረጃው ማለት በሥጋው በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን" የሚለው በደሙ ወደ ቅድስት የመግባት መብት እንደተሰጠን ያሳያል። ሕያውና ሕይወት ሰጪው መንገድ ኃይል ሰጠን ይህንን መንገድ የመረቀልን ወይም የከፈተው በሥጋው ነው። በደሙ በኩል ከሚለው ሐሳብ ጋር በምንም መንገድ ልናመሳስለው አይገባም። ትርጉሙ እንደዚያ ማለት አይደለም አንዳንድ ሰዎች በሥጋው በኩል ማለት በደሙ በኩል ማለት ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ፣ ሆኖም ግን ትርጉሙ ከዚህ ይሰያል።

ኢየሱስ የገዛ ደሙን ለእኛ አፈሰሰ በሚለው ልዩ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ደሙን አፍስሶ በሄደበት የሥጋ መጋረጃ በተቀደደበት መንገድ ልንከተለው ያስፈልጋል። ያንን መንገድ ሲከፍት እኛን ወደ ቅድስት የሚያስጠጋንና የሚያስገባንን ሕያው ኃይል ሰጥቶናል፤እዚህ ላይ የምንማረው ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ የተከፈተው በተቀደደው የሥጋ መጋረጃ በኩል እንደሆነ ነው።

መጋረጃው የተቀደደው በኢየሱስ ነው እኛንና እግዚአብሔርን ለያይቶ የነበረው መጋረጃ ሥጋ ነው። የሃጢአት ኃይል ያለው በሥጋ ውስጥ ነው። ኃጢአት ሲወገድ ብቻ የዚያን ጊዜ መጋረጃው ይወገዳል። ኢየሱስ በሥጋ በመምጣትና በመስቀል ላይ በመሞት የሥጋን መጋረጃ መቅደድ የቻለው በሞቱ ብቻ ነው ከዚያም በኋላ የኃጢአትን እና የሥጋን ኃይል ባዶ አደረገ። "ሥጋን በመቅረብ ከሞት አዳነን" ለፈሰሰው ደሙ ዋጋ እና ኃይል የሰጠው ይሄ ነው።

በደሙ በኩል ወደ ቅድስት ለመግባት ለወሰኑ ሁሉ ይህ ሕግ ቀርቶላቸዋል። በተቀደደው የሥጋ መጋረጃ በኩል መግባት ይችላሉ። የሥጋን መቀደድ የጠየቀው ደሙ ነው የፈጸመውም ደሙ ነው። የኢየሱስ ደም በኃይል በሚሰራበት ቦታ ሁልግዜ የሥጋ ሞት ይከተላል። በሌላ አነጋገር ሥጋ ሊሰራ አይችልም ይሞታል ማለት ነው። በሥጋው ለመጠቀም የሚያስብ ሰው ወደ ቅድስት መግባት አይችልም ሥጋ መስዋዕት ሆኖ ለሞት መሰጠት አለበት፤በተዛማጅ አማኝ የሥጋን ኃጢአተኝነት ሲገነዘብና በሥጋ ያለውን ሁሉ ለሞት አሳልፎ ሲሰጥ ያንጊዜ የደሙን ኃይል በሚገባ መገንዘብ ይችላል። አማኝ ይህን ማድረግ የሚችለው በራሱ ብርታት ወይም ጥንካሬ አይደለም ነገር ግን ኢየሱስ በመረቀለት



ሕያው መንገድ ሲመጣ ብቻ ነው። የኢየሱስ ሕይወት ሰጪ ኃይል የሚሰራው በዚህ መንገድ ነው።

እውነተኛ አማኝ ከኢየሱስ ጋር ተሰቅሏል ሞቷልም ሥጋንም ሰቅሏል ስለዚህ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ለማድረግ በመጋረጃው በኩል ይገባል።

ኦ! አዲሱና ሕያው መንገድ የከበረ መንገድ ነው በሕይወት ሰጪ ኃይል የተሞላ ነው ኢየሱስ ለእኛ መርቆ ከፍቶልናል። በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በአዲሱ መንገድ ወደ ቅድስት የመግባት ነፃነት አግኝተናል። ጌታ እግዚአብሔር በተቀደደው መጋረጃ በሥጋ ሞት በኩል ወደ መንፈስ ቅዱስ የሙላት ሕይወት ይመራናል ከዚያን በኋላ በመጋረጃው አልፈን ከእግዚአብሔር ጋር በቅድስት ውስጥ ለመኖር የምንችልበትን የመኖሪያ ስፍራችንን እናገኛለን። እያንዳንዷ የሥጋ መስዋዕትነት በደሙ በኩል ወደ ቅድስት ጠልቀን እንድንገባ ትመራናለች።

- ❖ *<u>የደራሲው ማስታወሻ</u> እነዚህን ጥቅሶች በጥንቃቄ አስተያዩዋቸው 1ጴጥሮስ 3:18 "ክርስቶስ በሥጋው ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" 4:1፣ "ክርስቶስ ሥለ እኛ በሥጋ መከራን ተቀበለ" 4:6፣ "ኃጢአትን በሥጋ ኮነነ" ።*

## ታላቁ ሊቀ ካህን

**"በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን እንቅረብ"**

ወደ ቅድስት ስንገባ የምናገኘው የክርስቶስን ሥራ ፤ ደሙን እና ሕያው መንገድን ብቻ ሳይሆን ሰው የሆነውን ክርስቶስንም ነው። ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቤት ላይ ታላቅ ሊቀካህን ሆኖ ስለምናገኘው እግዚአብሔር ይመስገን።

ካህናት ወደ ምድራዊው መቅደስ እየገቡ ማገልገል የቻሉበት ምክንያት ከታላቁ ሊቀ ካህን ጋር ግንኙነት ስለነበራቸው ነው። ከአሮን ልጆች በቀር ካህናት አልነበሩም። ከጌታ ከኢየሱስ ጋር ካለን ግንኙነት የተነሣ ለእኛም ወደ ቅድስት መግባት ተሰጥቶናል። ስለዚህ ኢየሱስ ወደ አብ እንዲህ በማለት ፀለየ "እነሆኝ እኔም እግዚአብሔር የሰጠኝንም ልጆች" (ዕብ. 2:13)

ኢየሱስ ታላቅ ካህን ነው የዕብራውያን መልእክት ኢየሱስ እውነተኛ መልከጸዴቅ እንደሆነ ያሳየናል ይህም ብቻ አይደለም ዘለዓለማዊ ልጅ ዘለዓለማዊና የማይለወጥ ክህነት ያለው ታላቅ ካህን ሆኖ በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠ ይነግረናል። በዚያ ለማማለድ ዘወትር

በሕይወት ይኖራል በተጨማሪም በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሁሉ ሊያድናቸው ይችላል። ኢየሱስ ታላቅና ኃያል ካህን ነው።

“በእግዚአብሔር ቤት ላይ ታላቅ ካህን የሆነ” ኢየሱስ በቅድስት አገልግሎት ሁሉ ላይ የተሾመ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ በእርሱ ጥበቃ ስር ይሆኑ ዘንድ ተሰጥተውታል። ወደ ቅድስት ለመግባት የልብ መሻት ካለን እርሱ እኛን ለመቀበል በዚያ በሕይወት አለ በተጨማሪም ወደ አብ ያቀርበናል። የመርጨትን ደም በእኛ ውስጥ የሚፈጽመው እርሱ ነው እርሱ በደሙ በኩል ገባ እኛንም በደሙ በኩል ወደ ቅድስት አስገባን በቅድስት ውስጥ ያለውን አገልግሎት እና እኛም ያለብንን ኃላፊነት ያስተምረናል ምንም እንኳ ደካሞች ቢሆኑ ጸሎቶቻችን መስዋዕቶቻችን እና አገልግሎቶቻችን ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሚያደርገው እርሱ ነው ከዚህም በተጨማሪ በቅድስት ውስጥ ለሚኖረን አገልግሎትና ሕይወት ሰማያዊ ብርሃንና ኃይልን የሚሰጠን እርሱ ነው ሕይወትንና የቅድስናን መንፈስም የሚሰጠን እርሱ ነው። ደሙ ወደ ቅድስት መግባትን እንደሰጠን ሁሉ መስዋዕትነቱ ይኸውም ሥጋው ደግሞ ሕያው መንገድን አስገኝቶልናል በቅድስት ውስጥ ከገባን በኋላ ጸንተን እንድንኖር ሁልግዜ እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን እንድንመላለስ ሊያደርገን የሚችለው እርሱ ነው ርህራሄን የተሞላ ታላቅ ሊቀካህን እንደመሆኑ እያንዳንዱን አማኝ እንዴት እንደሚያስተካክል ደካሞችንም እንዴት እንደሚረዳ ያውቃል በቅድስት ውስጥ ወደ እግዚአብሔር መቅረብን ውብ የሚያደርገው ይሄው ነው። በዚያ ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቤት ላይ ታላቅ ካህን ሆኖ እናየዋለን።

ቅድስት በጣም ከፍ ያለ እና ሊደረስበት የማይቻል መስሎ ሲሰማን የደሙ ኃይል ምን እንደሆነ መረዳት ያዳግተናል በተጨማሪም በአዲስና በሕያው መንገድ እንዴት እንደምንራመድ ማወቅ አንችልም በዚህን ጊዜ ወደ ቅድስት እንዲያመጣንና እንዲያስተምረን ወደ ሕያው አዳኝ እንመለከታለን እርሱ በእግዚአብሔር ቤት ላይ ታላቅ ካህን ነውና በእርሱ ከታመንክ ብቻ በቅድስት ውስጥ ትሆናለህ።

“እንቅረብ” እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀልንን ቅድስትን ፣ ነፃነትን የሰጠንን ደሙን፣ ወደ ቅድስት የሚወስደውን ሕያው መንገድ እና እኛን የሚረዳንን ታላቁን ካህን ተመልክተን “እንቅረብ” አዎን “እንቅረብ” እግዚአብሔር ለእኛ ካዘጋጃቸው ከነዚህ አስደናቂ በረከቶች ምንም ነገር አይከልክለን። ወደ ቅድስት መግባትን አግኝተናል። ይህንንም መብት ያገኘነው በክርስቶስ ኢየሱስ ደም አማካይነት ነው። መንገዱን መርቆ በከፈተልን በእርሱ እርምጃ መግባትን



አግኝተናል። እኛን በቅድስት ውስጥ ለመቀበል፣ ለመቀደስ፣ ለመጠበቅ፣ ለመባረክ በዘለዓለማዊ ክህነቱ ይኖራል። ከእንግዲህ ወዲህ አንጠራጠር ወይም ወደ ኋላ ለመመለስ ልባችን አያስብ። እግዚአብሔር ላዘጋጀልን ነገር ያለንን ነገር ሁሉ እንሰዋ በሰማዩ በአባታችን ፊት ለመቅረብና በእርሱ ዘለዓለማዊ ሕልውና ውስጥ ሕይወታችንን እንድናገኛት በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ እንቅረብ።

ለመግባት እንዴት እንደምንዘጋጅ ለማወቅ ወስነናል ? የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባችን ለዚህ ጥያቄ የከበረ መልስ ይሰጠናል።

## እንዴት እንዘጋጅ?

### በቅን ልብ እንቅረብ

መግባት ለሚፈልጉ አማኞች ከተጠየቁት አራት ነገሮች የመጀመሪያው “መቅረብ” ነው። በቅን ልብ ከሚለው ከሁለተኛው ጥያቄ ጋር የተያያዘው “በተረዳንበት እምነት” የሚለው ቃል ነው። በቅን ልብ የሚለው ምን እንደሆነ በትክክል መረዳት እንችል ዘንድ በተረዳንበት እምነት በዋነኝነት ከዚህ ቃል ጋር በአንድነት ተያይዟል።

የወንጌል ስብከት ሁልግዜ የሚጀምረው በኃጢአት ኑዛዜና ከእምነት ነው። ሰው ወዲያውኑ የኃጢአትን ይቅርታ ካላገኘ በቀር በእምነት የእግዚአብሔርን ፀጋ መቀበል አይችልም በእምነት የሕይወት እርምጃ ውስጥ ይህ ሕግ ሁልግዜ ይሰራል ያለ ቅን ልብ የእምነት መረዳት ላይ መድረስ ያዳግታል ያም ልብ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ታማኝ ምርኮኛ የሆነ ልብ ነው። ቅድስት ያለ ቅን ልብ ሊገባባት አይቻልም። ይህ ቅን ልብ እንዲፈልግ የተነገረውን ነገር በእውነት የሚፈልግ ልብ ማለት ነው።

“በቅን ልብ እንቅረብ” ይህ ልብ ምን ዓይነት ልብ ነው? በቅድስት ውስጥ ለመኖር በእውነት ሁሉን ነገር ለመተው የወሰነ፣ ሁሉን ነገር በመተው ላይ ያለ፣ እግዚአብሔርን የያዘ፣ ለደሙ ሥልጣንና ኃይል ምርኮኛ ለመሆን እራሱን የካደ ልብ ነው። በአዲስና በሕያው መንገድ በተቀደደው የሥጋ መጋረጃ በኩል ከክርስቶስ ጋር ለመሄድ የመረጠ ልብ ነው በእውነትና ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ጌትነትና መኖሪያነት ራሱን የሰጠ ልብ ነው።

“በቅን ልብ እንቅረብ” ያለ ቅን ልብ ወደ ቅድስት መግቢያ በር አይገኝም። ታዲያ ቅን ልብ ያለው ማነው? እግዚአብሔር የሰጠው አዲስ ልብ ቅን እንደሆነ መገንዘብ አለብን። በአዲሱ ልብ ውስጥ በሚኖረው በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ፈቃድህን ከእግዚአብሔር ጋር

በሚስማማ መንገድ እና በሥጋህ ውስጥ ከሚኖረው ኃጢአት ጋር በሚቃረን ሁኔታ ራስህን ስጥ ለጌታ ኢየሱስ ለታላቁ ካህን ማንኛውንም ኃጢአት እንደሰጠኸውና በፊቱ እንደ ጣልክ ሕይወትህን በሞላ እንዳስረከብከውና ሁሉን ትተህ እርሱን ለመከተል እንደወሰንክ ንገረው በሥጋህ ውስጥ ጠልቆ የተሰወረውን ኃጢአት እና የልብህን ክፋት ላታስተውለው ትችላለህ ለዚህ ችግርህ እግዚአብሔርን "አቤቱ መርምረኝ ልቤንም እወቅ ፈትነኝ መንገዴንም እወቅ" በማለት ልትጠይቀው ትችላለህ (መዝ(139)፡23)፡፡ ልብን መመርመር ለሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን ራስህን ያለማቋረጥ አስገዛ እርሱ ከአንተ የተሰወረውን ይገልጥልሃል ይህን የሚያደርግ ወደ ቅድስት መግባት የሚችል ቅን ልብ ያለው ነው፡፡

"በቅን ልብ በፊትህ እንቀርባለን" ብለን ለእግዚአብሔር መናገር እንፍራ እግዚአብሔር በሥራችን ፍጹምነት መሠረት እንደማይፈርድ እርግጠኞች ልንሆን ያስፈልጋል የሚፈርደው በተገለጠው ኃጢአት በታማኝነት ራሣችንን ለእግዚአብሔር ባለመስጠታችን እና በተሰወረው ኃጢአታችን ላይ የመንፈስ ቅዱስን ወቀሳ ባለመቀበላችን ነው በእግዚአብሔር ፊት በታማኝነት እንዲህ የሚያደርግ ልብ ቅን ልብ ነው፡፡ በደሙ በኩል በቅን ልብ ወደ ቅድስት እንቀርባለን በመንፈስ ቅዱስ በኩል ቅን ልብ የሰጠን እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

## ሙሉ የእምነት መረዳት

እግዚአብሔር ከሰው ጋር በሚያደርገው ግንኙነት እምነት ምን ዓይነት ቦታ እንዳለው እናውቃለን "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም" ወደ ቅድስት መግባት የተመሠረተው በሙሉ የእምነት ዋስትና ላይ ነው፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖርበትና የምንመላለስበት የተቀደሰ ስፍራ እንዳለ መቀበል የሚያስችል ሙሉ የእምነት መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ክቡር የደሙ ኃይል ኃጢአትን ፈጽሞ እንዳሸነፈ ከእግዚአብሔርም ጋር ያለንን ሕብረት ሊከለክል የሚችል ምንም ነገር እንደሌለ፤ ኢየሱስ እኛን በሥጋው የቀደሰበት ህያው መንገድ ከእርሱ ጋር ለሚራመዱ ሁሉ ዘላለማዊ የሕይወት ኃይል መያዙ፤ በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሆነው ታላቁ ሊቀካህን በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሊያድናቸው እንደሚችል፤ በቅድስት ውስጥ ለሕይወት የሚያስፈልገንን ሁሉ በመስጠት በውስጣችን በመንፈሱ እንደሚሠራ ልናምን እና በሙሉ የእምነት መረዳት አጥብቀን ልንይዝ ይገባል፡፡



ታዲያ ወደዚህ እምነት እንዴት መድረስ እችላለሁ? እምነቴ ወደ ሙሉ መረዳት እንዴት ሊያድግ ይችላል? የሚል ጥያቄ ካለን ይህ ሊሆን የሚችለው "የእምነታችን ራስና ፈጻሚ" ከሆነው ከኢየሱስ ጋር ሕብረት በማድረግ ነው (ዕብ. 12፡2)፡፡ በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን እንደመሆኑ ተገቢ እምነት እንዲኖረን ይረዳናል፡፡ ኢየሱስን በመገንዘብ፣ አስደናቂ ፍቅሩን በመረዳት፣ ፍጹም ሥራውን በማወቅ ክቡር እና ኃያል ደሙን በማመን እምነት ይጸናል ይጠነከራልም እምነታችንን እንዲያነቃ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ ዓይኖቻችንን በእርሱ ላይ በማጽናት እምነትና የእምነት መረዳት የእኛ ይሆናል፡፡

"እምነት ከመስማት ነው መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው" (ሮሜ 10፡17) የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል መያዝና ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ እምነት በቃሉ ይመጣል በቃሉም ያድጋል፡፡ ቃል ስንል ፊደል ማለታችን አይደለም፡፡ ነገር ግን መንፈስና ሕይወት የሆነው የኢየሱስ ድምጽ ነው "እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው" ብሏልና (ዮሐ. 6፡63)፡፡ አምና አሜን በእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል ነው፡፡ ቃሉን ለማሰላሰል እና በልብህ ውስጥ ለመያዝ ጊዜ ውሰድ ነገር ግን ሁልግዜ በልብህ በኢየሱስ ላይ ማረፍ አለብህ የሚያድነው እምነት በኢየሱስ ላይ ያረፈ እምነት ነው በጸሎት ወደ ኢየሱስ የሚወስደን እና ከእርሱ ጋር እንድንነጋገር የሚያደርገን ቃል የጊዜው ቃል ነው፡፡

"ላለው ይሰጠዋልና" የሚለውን ቃል አስታውስ ያለህን እምነት ተጠቀምበት፣ተለማመደው፣ግለጸው፣በእግዚአብሔር ላይ ያለህ መታመን የሕይወትህ ተቀዳሚ ዓላማ እንዲሆን አድርግ እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑ ልጆችን ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ከእምነት የበለጠ የሚፈልገው ነገር የለውም፡፡ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ለማንበብ ስትቀርብ "አቤቱ የተስፋ ቃልህን ዛሬም እንደምትሰጠኝ አምንሃለሁ በማለት ጸልይ እያንዳንዱን የተስፋ ቃል ከቃሉ ስታነብብ "ጌታ ሆይ ይህን የተስፋ ቃል በሕይወቴ እንደምትፈጽመው አምንሃለሁ" በማለት ተናገር ቀኑን ሙሉ በሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ምሪትና ባርኮት መታመንን ቅዱስ ልማድህ አድርግ፡፡

ወደ ቅድስት ለመግባት "ሙሉ የእምነት መረዳት" በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተረዳንበት እምነት እንቅረብ ይላልና፡፡ በደም መዋጀት ፍፁምና ኃያል ነው፡፡ የኢየሱስ ፍቅርና ጸጋ በውስጡ ይፈስሳል በቅድስት ውስጥ የመኖር ባርኮት ያለ ጥርጥር የእኛ ነው ከፍታውም ከምንደርስበት በላይ ነው ስለዚህ በሙሉ የእምነት መረዳት እንቅረብ፡፡

## ልባችንን ተረጭተን እንቅረብ

**"ከክፉ ህሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን (ነጽተን) ... እንቅረብ።"**

ልብ የሰው ሕይወት ማዕከላዊ ክፍል ነው። ህሊናም ደግሞ የልብ ማዕከላዊ ክፍል ነው። በዚህ ሕሊና ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ይገነዘባል። ክፉ ህሊና በእግዚአብሔር እና በግለሰብ መካከል ያለው ነገር ሁሉ የተበላሸ እንደሆነ ይነግረዋል። ኃጢአትን እንደሚሰራ ብቻ ሳይሆን ኃጢአተኛም እንደሆነ ከእግዚአብሔር እንደተለየ ይነግረዋል። ጥሩ ወይም ንጹህ ህሊና ግን ሰውየው እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኝ ምስክርነት ይሰጣል (ዕብ.11:5) ንጹህ ሕሊና ኃጢአተኛው የኃጢአቱን ሥርየት እንዳገኘ ብቻ ሳይሆን ልቡ በእግዚአብሔር ፊት እውነተኛ እንደሆነም ሽንገላም እንደሌለበት ይመሰክርለታል። ወደ ቅድስት ለመግባት ያመነ ሁሉ ከክፉ ሕሊና የነፃ ልብ ሊኖረው ያስፈልጋል። የልብ መንፃት የሚለው ቃል "ከክፉ ሕሊና ለመንፃት ልባችንን ተረጭተን" በማለት ተተርጉሟል። በደም መረጨት አስፈላጊ ነው። የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድታገለግል ሕሊናህን ከክፉ ሁሉ ያነፃዋል።

ኢየሱስ ወደ አብ በገባበት በደሙ ወደ ቅድስት እንደምንገባ ተመልክተናል። ይሁን እንጂ ይህ በቂ አይደለም ሁለት ዓይነት መረጨቶች አሉ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ካህናት በመሰዊያው ላይ በእግዚአብሔር ፊት በሚረጭ ደም ብቻ አይታረቁም ነገር ግን ሰዎች ራሣቸው በደሙ መረጨት አለባቸው የክርስቶስ ደም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በቀጥታ ከልባችን ጋር መገናኘት አለበት ከዚያ ልባችን ከክፉ ሕሊና ይነፃል ከዚያም በኋላ ሕሊና የኃጢአት ዕዳ ፈጽሞ እንደተከፈለ ምስክርነት ይሰጣል በእኛ እና በእግዚአብሔር መካከል የምትለያይ ትንሽ ነገር እንኳ መቅረት አትችልም። የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ደስ እንደምናሰኝ ሕሊናችን ምስክር ይሆናል ምክንያቱም ልባችን ነጽቷል በመርጨት ደም በኩል ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ሕያው ሕብረት አድርገናል አዎን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል ከኃጢአት ዕዳ ብቻ ሳይሆን ከኃጢአትም ቆሻሻ ያነፃል።



በደሙ ኃይል ምክንያት የወደቀው አሮጌ ተፈጥሮአችን የራሱን ኃይል እንዳይገልጥ ይከለከላል ሣሩንና ልምላሜውን ሽፍኖት የነበረው አቧራ በዝግታ የሚፈሰው ምንጭ አንጽቶ አዲስና መንፈስ ማራኪ እንደሚያደርገው ሁሉ ደሙም ያለ ማቋረጥ ልብን ለማንጻት ይሰራል። ከደሙ ሙሉ ኃይል ሥር የሚኖር ልብ ከክፉ ሕሊና የነፃ ወደ ፍጹም ነፃነት ለመቅረብ የተዘጋጀ ልብ ነው ሁለንተና ልብ ሁለንተና ውስጣዊ ተፈጥሮ በመለኮታዊ ሥራ ነጽቷል።

ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን የምንቀርበው በተረዳንበት እምነት ነው። ልባችን እንደነፃ እንመን ደሙ እንደሚያነፃን በመታመን በእግዚአብሔር ፊት ከፍ ከፍ አድርገን እናክብረው። ታላቁ ሊቀካህን በቅዱስ መንፈሱ አማካይነት በደሙ ነጽተን ወደ ቅድስት ለመግባት ሊያዘጋጀንና የቃሉን ትርጉምና ኃይል በመግለጥ ሊያስገነዝበን ይችላል። ከዚህም በላይ ወደ ልባችን ለመግባት ያዘጋጃል ወደ ቅድስት ለመግባትና በዚያ ለመኖር የሚያስችል ልብ ማግኘት ምንኛ መታደል ነው።

## ሰውነታችንንም ታጥበን

"ሰውነታችንን በጥሩ ውኃ ታጥበን... እንቅረብ" በሁለት ዓለሞች ውስጥ እንኖራለን እነርሱም የሚታየው እና የማይታየው ዓለም ናቸው። ከሰው ጋር ግንኙነት የምናደርግበት ውጫዊ ወይም ቁሣዊ ሕይወት እንዳለን ሁሉ ከእግዚአብሔርም ጋር የሚያገናኝ ውስጣዊ ድብቅ ወይም ስውር መንፈሳዊ ሕይወት አለን። ቁሳዊው አካል ሰውነትን የሚወክል ከሆነ ሰውነት ውስጥ ያለውን ሙሉ ሕይወት ከተግባሮቹ ሁሉ ጋር ይወክላል።

ልብ በደም መረጨት አለበት ሰውነት ደግሞ በጥሩ ውሃ መታጠብ አለበት። ካህናት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ራሣቸውን ሲሰጡ ሰውነታቸውን በንጹህ ውሃ ይታጠባሉ በተጨማሪም በደም ይረጫሉ (ዘጸ. 29:4፣20፣21) ወደ ቅድስት ውስጥ ሲገቡ በዚያ የሚያገኙት በመሰዊያው ላይ ያለውን የሚረጭ ደም ብቻ ሳይሆን በገበታው ውስጥም ለመታጠቢያ የሚያገለግል ውሃ ተሞልቶ ያገኛሉ እንደዚሁም ደግሞ ክርስቶስ የመጣው በደምና በውሃ ነው (1ዮሐ. 5:6) ስለዚህ በመጀመሪያ በውሃ ተጠመቀ በኋላ በደሙ ተጠመቀ (ሉቃ. 12:50)።

እኛ ደግሞ በውሃና በደም የምንነፃበት እጥፍ መንጻት አለን የውሃ ጥምቀት በንስሐ ከኃጢአት የመለየት ምሣሌ ነው "ተጠመቁ እና ከኃጢአታችሁ ታጠቡ" ደሙ ልብን

ውስጣዊውን ሰው ሲያነፃ የውሃ ጥምቀት ግን ከኃጢአት መለየትን ለመመስከር ከሚታየው ሕይወቱ ጋር ሰውነትን መስጠት ነው፡፡

ስለዚህ "ከክፉ ህሊና ለመንፃት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውሃ ታጥበን እንቅረብ" ሥጋን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ካልነፃን የደሙን ውስጣዊ የማንፃት ኃይል መለማመድ አንችልም፡፡ በመርጨት ደም የመንፃት መለኮታዊ ሥራ እና ከኃጢአት የመለየት ምሣሌ የሆነው የውሃ ጥምቀት የሚነጣጠሉ አይደሉም፡፡

ወደ ቅድስት ለመግባት መንፃት አለብን ሳትታጠብ የንጉሱ መገኛ ወደሆነው ወደ ቅድስት መግባትን በፍጹም አታስብ ከኃጢአት ሁሉ ሳትነፃ ወደ እግዚአብሔር መኖሪያ ወደ ቅድስት መምጣት እንደምትችል ማሰብ ሞኝነት ነው የክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል እግዚአብሔር የሚያነፃህን ኃይል ሰጥቶሃልና በቅድስት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር የመኖር ፍላጎት ካለህ በእያንዳንዱ እርምጃህ ኃጢአትን የማስወገድ ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ ያልተቀደሰ ሕይወት ወደ ቅድስት መግባት አይችልምና፡፡

በቅድስት ውስጥ እንድንሆን የፈለገ እግዚአብሔር ይመስገን የእርሱ ካህናት እንደመሆናችን በቅድስት ውስጥ እርሱን ማገልገል አለብን በቅድስት በረከት ይኸውም በቅዱሱ ሕብረት እንድንደሰት የልባችንን ንጽህና ይፈልገዋል፡፡ በደሙና በመንፈሱ እንድንነፃ በተጠንቀቀልናል፡፡ ስለዚህ "ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንን በጥሩ ውሃ ታጥበን እንቅረብ"፡፡

## እንቅረብ

በጉባኤያችን ውስጥ ከልባቸው ወደ ጌታ ላልተመለሱት ሰዎች እንኳ የቅድስት ስፍራ ተዘጋጅቶላቸዋል መቅደሱም ደግሞ ተከፍቶላቸዋል ክቡር ደሙ ሕያው መንገዱ እና ታላቁ ካህን የእነርሱ ናቸው በታላቅ ትምክህት "ኑ እንቅረብ" ብለን ልንጋብዛቸው ያስፈልጋል ከእግዚአብሔር የራቃችሁ ወዳጆቼ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ፀጋ አታክፋፉ አስቸኳይ ጥሪውን ወደ እናንተ ወደ ላከው በልጁ ደም ዋጋ ወደ ቅድስት የሚወስደውን መንገድ መርቆ ወደ ከፈተው በቅዱስ መኖሪያው የእርሱ ልጆች አድርጎ በፍቅር እንደገና ለመቀበል ወደሚጠብቃችሁ ቅዱስ አባት ቅረቡ ወዳጆቼ እኔም "ሁላችንም ወደ እርሱ እንቅረብ" በማለት ልመናዬን አቀርባለሁ በእግዚአብሔር ቤት ላይ የሆነው ታላቁ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የሆነ አዳኝ ነው፡፡



"እንቅረብ" ጥሪው የቀረበው ለሁሉም አማኞች ነው በመቅደሱ ደጅ ላይ በመቆም አትርኩ የኃጢአትን ይቅርታ በልባችን ብቻ ተስፋ ማድረግ በቂ አይደለም ስለዚህ በመጋረጃው በኩል እንግባ ወደ እግዚአብሔር መንፈስ በእውነተኛ አቀራረብ እንቅረብ በእርሱ ቅዱስ መገኛ ውስጥ መኖሪያችንን እናድርግ ሰውነታችን የእግዚአብሔር ውስጣዊ መቅደስ ነውና፡፡

"በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ" በእውነት ፈጽሞ ራሱን ለእግዚአብሔር የሰጠ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት "ሙሉ የእምነት መረዳትን ይለማመዳል" በቃሉም ውስጥ የተሰጡትን ተስፋዎች ሁሉ በደስታና በነፃ የራሱ አድርጎ ይወስዳቸዋል የእምነታችን ድካም መነሻው የራሳችን ልብ ጥመት ነው "በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ" የዚያን ጊዜ በረከቱ የእኛ ይሆናል ደሙ ፈጽሞ የኃጢአትን ይቅርታ ስላመጣና ኃጢአትን ስላሸነፈ አማኞች በነፃነት ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርቡ ወደ ኋላ ሊያደርጋቸው የሚችል ነገር የለም፡፡

"ከክፉ ህሊና ለመንፃት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንም በጥሩ ውሃ ታጥበን እንቅረብ" በደሙ ፍጹም ኃይል እምነትን በልባችን እንቀበል ከቅዱስ ስፍራ ጋር የማይስማማውን ማንኛውንም ነገር አውጥተን እንጣል ከዚያም በኋላ በየቀኑ በቅድስት ውስጥ እንዳለን ይሰማናል ሕይወታችን በሆነው በክርስቶስ ውስጥ እኛም ደግሞ በዚያ እንሆናለን ከዚያን በኋላ በቅድስት ውስጥ ተግባራችንን ሁሉ ማከናወን እንጀምራለን የምናከናውናቸው እነዚህ ተግባራት ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ መንፈሳዊ መስዋዕቶች ናቸው ወንድሞች ሆይ፣ እግዚአብሔር በቅድስት ውስጥ እኛን እንደሚጠብቀን አውቀን "ወደ እርሱ እንቅረብ"

"እቅረብ" የሚለው ቃል ከጸሎት ጋር የሚገናኝ ልዩ ጥሪም ነው እንደ ካህናት በመቅደሱ ውስጥ ሁልግዜ የማንኖርበት ጊዜ አለ ነገር ግን ነፍስ ፈጽሞ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ከእርሱ ጋር ብቻ በቃልኪዳን መተሳሰር ህብረት የምታደርግበት ጊዜ አለ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ጸሎታችን በደካማ ኃይል ከርቀት እግዚአብሔርን የሚጠራ መሆኑ የሚያሳዝን ነው እስቲ እያንዳንዱን ጸሎታችን እንመርምር በእውነት በቅድስት ውስጥ ስለመሆናችን ይመሰክራል? ከክፉ ሕሊና ፈጽሞ በተረጨ ልብ ውስጥ እንሁን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ለያይቶን የነበረው የኃጢአት ግድግዳ በደሙ ኃይል ፍጹም እንደተወገደ እናስብ በደሙ አማካይነት በቅድስት ውስጥ እንደሆንን ለማወቅና ለመጸለይ ጊዜ እንውሰድ ከዚያን በኋላ ፍላጎታችን እና ምኞታችን መልካም መዓዛ እንዳለው የዕጣን

መስዋዕት በእግዚአብሔር አብ ፊት እናኑር ያን ጊዜ ጸሎት እውነተኛ ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያና ከእግዚአብሔር ጋር ውስጣዊ ኅብረት ማድረጊያ መንገድ ይሆናል። ይህ እንዲህ ከሆነ የክህነት ሥራ የሆነው ምልጃ እና ለሌሎች በረከት የመጸለይ አገልግሎት ያለ ምንም እንቅፋት በብርታትና በኃይል ማከናወን እንችላለን። በደሙ ኃይል አማካይነት በተቀደሰ ስፍራ የሚኖር እርሱ ከእግዚአብሔር እውነተኛ ቅዱሳን መካከል አንዱ ነው ስለዚህ የእግዚአብሔር ቅዱስና የተባረከ ሕልውና ከእርሱ ውስጥ መንጭቶ በዙሪያው ላሉት ሁሉ ይደርሳል።

ወንድሞች ሆይ ፣ "እንቅረብ" ለራሣችን ለእርስ በእርሳችን ለሁሉም እንጸልይ የእግዚአብሔር የአምላካችንን ሕልውና በየስፍራው ከእኛ ጋር ይዘን የምንዞርበት ቅድስተ ቋሚ መኖሪያችን ትሁን። በውስጣችን ከኃይል ወደ ኃይል ከክብር ወደ ክብር የሚያድግ የሕይወት ምንጭ ይሁንልን ዘወትር በደሙ ኃይል በቅድስት ውስጥ ያኑረን አሜን!



# ምዕራፍ ስምንት

## ሕይወት በደም ውስጥ

"ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፤የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሣችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ" (ዮሐ. 6፡53-56)።

"የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?" (1ቆሮ. 10፡16)

በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ደም መጠጣት ርዕስ ሆኖ ቀርቦልናል። ውኃ ሁለት ተግባራት እንዳለው ቅዱስ ደሙም ደግሞ ሁለት ተግባር አለው።

ውሃ ለማጠብ ተግባር ስንጠቀምበት ያነፃል ነገር ግን ለመጠጣት ስንጠቀምበት ያድሳል ያረካል። የኢየሱስ ክርስቶስን ሙሉ የደም ኃይል ማወቅ የፈለገ የኢየሱስ ደም የመጠጣት ትርጉም ምን እንደሆነ ከእግዚአብሔር ቃል መማር አለበት። በመታጠብና በመጠጣት መካከል ያለውን ልዩነት ማንም ያውቀዋል ውሃን ለንጽህና ተግባር መጠቀም ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው መጠጣት ግን ከዚያ የበለጠ አስፈላጊና አርኪ ነው። ያለ ንጽህና እንደሚገባን መኖር እንደማንችል ባንጠጣ ደግሞ ፈጽሞ በሕይወት አንኖርም። መጠጣት በሕይወት መኖርን ሙሉ ደስታና እርካታን ይሰጣል የእግዚአብሔርን ልጅ (የኢየሱስን) ደም ካልጠጣን ወይም የግላችን ካላደረግነው የዘለዓለም ሕይወት ሊኖረን አይችልም።

### "ደሙን የመጠጣት በረከት"

ውኃ ከማጽዳቱ ይልቅ የበለጠ ቅርበት ያለው መጠጣቱ እንደሆነ ግልጽ ነው በተጨማሪም ጉልበት ያለው ውጤት ያስከትላል። ከክርስቶስ ደም ጋር በሚደረገው ኅብረት የሚገኘው በረከት ከመንጻትና ከመቀደስ በጣም የላቀ ነው በእርሱ ላይ የተጠቀሰው በረከት በጣም የላቀ ወይም የጠለቀ እንደሆነ መገመት እንችላለን።

ደሙ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት ለእኛ አንድ ነገር በማድረግ ብቻ የተገደበ አይደለም ነገር ግን ሙሉ ውስጣዊ መታደስን በማምጣት ታላቅ ነገር በውስጣችን ያደርጋል። "የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሣችሁ ሕይወት የላችሁም።" የሚለው የጌታ ኢየሱስ ቃል ሐሳባችንን ሊገዛ ይገባል። ጌታችን ኢየሱስ ሁለት ዓይነት ሕይወት ለይቶ አሣይቶናል በጌታ ኢየሱስ ፊት ቆመው  የነበሩት አይሁዶች ፍጥረታዊ ሥጋና ነፍስ ነበራቸው ከእነርሱም መካከል አብዛኞቹ ለኢየሱስ ጥሩ አመለካከት የነበራቸው ነበሩ ነገር ግን ኢየሱስ ሥጋውን ካልበሉ ደሙንም ካልጠጡ በራሣቸው ሕይወት እንደሌላቸው ነገራቸው ስለዚህ ኢየሱስ ይዞት የመጣውና ለሚፈልጉ ሰዎች ሊሰጥ ያለው አዲስና ሰማያዊ ሕይወት እንደሚያስፈልጋቸው ተናገረ። ሕይወት ያለው ማንኛውም ፍጥረት በሕይወት ለመኖር ምግብ ያስፈልገዋል። ሥጋዊ (ምድራዊ) ሕይወት ምድራዊ እንጀራና ውኃ መመገብ እንዳለበት ሰማያዊ ሕይወት ደግሞ ኢየሱስ በሚሰጠው ሰማያዊ ምግብና መጠጥ ይኖራል "የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሣችሁ ሕይወት የላችሁም" ሲል ኢየሱስ የሰው ልጅ ሆኖ በምድር በመመላለስ ራሱን በመስቀል ላይ ከሰጠን ከእርሱ ሕይወት የሚበልጥ እንጀራ ሊኖር አይችልም።

ጌታ ኢየሱስ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ" በማለት ጠበቅ አድርጐ ከመግለጹም በተጨማሪ የዚህን ሕይወት ባህሪ በግልጽ አብራርቶታል። ዘለዓለማዊ ሕይወት ማለት የእግዚአብሔር ሕይወት ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ በመጀመሪያ ደረጃ ወደ ምድር የመጣበት ዓላማ ይህን ዘለዓለማዊ ሕይወት በሰውነት ለመግለጽና በሥጋ ካለነው ከእኛ ጋር ለማገናኘት ነው። ዘለዓለማዊ ሕይወት በመለኮታዊ ኃይሉ ወደ ሰማይ ባረገው የሥጋ ሰውነት ውስጥ እንዳለ እንመለከታለን። ሥጋውን በመብላትና ደሙን በመጠጣት የክርስቶስን ሕይወት ተካፋይ የሚሆኑ ሁሉ በራሣቸው ሰውነት የዘለዓለምን ሕይወት ይለማመዳሉ። "እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ" ይላል የሚያስደንቀው በክርስቶስ ውስጥ ያለው ዘለዓለማዊ ሕይወት በሰው ሰውነት ውስጥ መገለጡ ነው። መንፈስ ቅዱስን ከምንካፈለው ባልተናነሰ የሥጋውም ተካፋይ መሆን አለብን የዚያን ጊዜ ሰውነታችን በእርሱ ሕይወት የተሞላ ይሆናል አንድ ቀንም የትንሣኤው ተካፋይ ይሆናል።

ጌታ ኢየሱስ "ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው" ሲል "እውነተኛ" የሚለው ቃል ስለ ራሱ በወይኑ ግንድ ምሣሌ ከተናገረው ጋር የሚመሳሰል ነው



እንዲህ አለ፡- "እኔ እውነተኛ የወይን ግንድ ነኝ" የሚለው ቃል በምሣሌው እና በእውነተኛው ሕይወት መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል ምድራዊ ምግብ እውነተኛ ምግብ ስላልሆነ እውነተኛ ሕይወትን አይሰጥም።  እውነተኛው ምግብና መጠጥ ሕይወት መስጠትና በሕይወት ማኖር የሚችለው የክርስቶስ ሥጋ እና ደም ብቻ ነው ይህ አባባል የሚያመለክተው በውስጣችን ላለው የዘለዓለም ሕይወት ምግብ የሆነው የክርስቶስ ኢየሱስ ሥጋ እና ደም መሆኑን ነው። ስለዚህ ኢየሱስ "ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው" ብሏል።

ጌታ ኢየሱስ ስለዚህ ምግብ እውነተኛነትና ኃይል ሲናገር "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ" ብሏል።

የኢየሱስን ደም መጠጣት በረከትና ከእርሱም ጋር አንድ መሆን ነው። በእርሱ ውስጥ ያለውን መለኮታዊ ባህሪ ተካፋይ መሆንም ነው ይህ አንድነት ምን ያህል እውነት እንደሆነ ኢየሱስ ሲገልጽ "እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው፣ እንደምሆን እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል" ብሏል። በአብና በወልድ መካከል ያለውን አንድነት ምንም ነገር ሊገታው አይችልም ይህ አንድነት እኛም ከወልድ ጋር ላለን አንድነት ምክንያት ነው። በማይነጣጠል መለኮታዊ ባህሪ አብና ወልድ ፍጹም አንድ እንደሆኑ ከዚህ የተነሣ ኢየሱስን የሚበላ ሰው ከኢየሱስ ጋር አንድ ይሆናል ይህ አንድነት በመለኮት ውስጥ እንዳለው አንድነት እውነተኛ አንድነት ነው።

ጌታ ኢየሱስ የሰውን ሥጋ በመውሰድ ለራሱ ሥጋን አዘጋጀ ይህ ሰውነት በክርስቶስ ሥጋና ደም ሕይወት ውስጥ የዘለዓለምን ሕይወት ተካፋይ ሆነ። በረከቱን በሙላት ለመቀበል የተዘጋጁ እና ይህን በረከት በሙላት ለመለማመድ የወሰኑ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስን ደም ስለመጠጣት የሚናገረውን ቅዱስ ምስጢር በማመን መቀበል አለባቸው።

## ይህ በረከት በእኛ ውስጥ እንዴት ይሰራል ?

የክርስቶስን ደም መጠጣት ምን እንደሆነ ለመረዳት መሞከር አለብን። በዚህ ርዕስ ስር የምንመለከተው የመጀመሪያው ሃሳብ "መጠጣት" የሚለውን ነው። ይህ ቃል በጥልቀት፣ በእምነት እና በውስጥ በመንፈሳችን የደሙን ኃይል የመቀበላችንን ምስጢር የሚያመለክት ነው።

አንዳንድ ጊዜ ሰባኪዎች የክርስቶስን ደም ስለ መጠጣት ሲናገሩ በተመስጦ ክልባችን አዳምጠን በመቀበል መልሰን እናስተጋባለን የአንድ ሰው ልብ በክርስቶስ ክቡር የደሙ ኃይል ሐሳብ ሲሞላ፣ ከደስታው ታላቅነት የተነሣ የራሱን ሐሳብ ሲተው፣ በሙሉ እምነት ክልቡ የራሱ አድርጎ ሲቀበል እና በዚያ ሕይወት ሰጪ የደም ኃይል በውስጣዊ ሕይወቱ መሰወጥን ሲፈልግ በዚያን ግዜ በእርግጠኝነት "የክርስቶስን ደም ጠጥቷል" ብሎ መናገር ይቻላል። በጠቅላላ በደም መዋጀቱን፣መንፃቱን፣ መቀደሱን እና ወደ ነፍሱ ውስጥ በጥልቀት ዘልቆ መግባቱን በእምነት እንዲመለከት ያስችለዋል።

በዚህ አገላለጽ ውስጥ አንድ ጥልቅ ምስጢር አለ ይኸውም በደሙ አማካይነት የተገኘውን ሙሉ በረከት ጉላ ባለ መንገድ በምሣሌ ማሣየቱ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሥጋውን እንድንበላና ደሙን እንድንጠጣ በተደጋጋሚ በተጠቀመበት ገለፃ ውስጥ የበለጠ ነገር እንዳቀደልን ያረጋግጣል። ይህ እውነት በግልጽ የተንፀባረቀው በጌታ እራት ነው። ጌታ ኢየሱስ በቅፍርናሆም ሲያስተምር ስለ እራቱ በግልጥ ባይናገርም ኋላ በፋሲካው እራት በትዕይንት ማረጋገጫ በግልጽ ተናግሯል።

የጌታ እራት ወይም ቅዱስ ቁርባንን በተመለከተ ሁለት አይነት አመለካከቶች ይንፀባረቃሉ አንደኛው የተሐድሶ አራማጅ የሆነው የዝዊንግሊ አመለካከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የካልቪን አመለካከት ነው።

የዘለዓለምን ሕይወት ለመውረስ በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ቅዱስ ቁርባንን ወይም የጌታን እራት ተካፋይ መሆን የተገባ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ለኤፌሶን ቤተክርስትያን ሲጽፍ እንዲህ ብሏል። "ቤተ ክርስቲያን ... አካሉ ናት" (ኤፌ. 1:23) እንዲሁም "አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ እራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል" (ኤፌ. 4:15-16)። ሰውነታችን ከክርስቶስ ሥጋ ጋር በአካልና በመንፈስ ካልተያያዘ እነዚህ ነገሮች ገቢራዊ ሊሆኑ እንደማይችሉ እንመለከታለን። ቀጥሎ ሐዋርያው ድንቅ በሆነ አገላለጽ እኛ አካሉ ነንና ካለ በኋላ "ይህ ምስጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው" ይላል። በክርስቶስ ሥጋና ደሙ ውስጥ የአማኞችን አንድነት አለመገንዘብ ሞኝነት ነው። ሐዋርያው በከፍተኛ ሁኔታ ስለተረዳው የጌታ እራት ወይም ቅዱስ ቁርባን ከመግለጽ ይልቅ በሁኔታው ይደነቃል።

አማኝ የክርስቶስን የመቤዠት ሥራ ቀለል አድርጎ ከሚመለከት ይልቅ በቅዱስ ቁርባን ወይም በጌታ ራት ውስጥ ላቅ አድርጎ እንዲመለከተው የሚያደርግ ነገር አለ። የተሰዋውን



የክርስቶስን ሥጋ መብላት የፈሰሰውን ደሙን መጠጣት ምንድን ነው? ለዚህ ጥያቄ መልሱ የክርስቶስን ስቃይና ሞት በሚያምን ልብ መቀበል ብቻ ሣይሆን በዚህ ምክንያት የኃጢአትን ይቅርታና የዘለዓለምን ሕይወት መቀበል ነው ከዚህ በተጓዳኝ በክርስቶስና በእኛ ውስጥ በአንድ ጊዜ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ከተቀደሰ አካሉ ጋር የበለጠ አንድ መሆን ነው። ምንም እንኳ ክርስቶስ በሰማይ እኛ ደግሞ በምድር ብንሆንም ሥጋችን ከቅዱስ ሥጋው ጋር አንድ እንዳይሆን አያግደውም በአንድ መንፈስ እንኖራለን ለዘለዓለም በአንዱ መንፈስ እንገዛለን። በዚህ ትምህርት ውስጥ የቀረቡት ሐሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ሃሳብ ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ።

እግዚአብሔር ቀደም ብሎ ከፈጠራቸው መንፈሳዊ ፍጥረታት ይልቅ በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ግልጽ የሆነ ልዩነት አስቀምጧል ከምድር አፈር ያበጀውን ሰው የሕይወትን መንፈስና የእግዚአብሔርን ክብር ይገልጥ ዘንድ የጥበቡና የኃይል ሥራው መገለጫ አደረገው በሥጋ በኩል ምኞትና ኃጢአት ወደ ዓለም ገቡ ሥጋን ለማዳንና የእግዚአብሔር መኖሪያ ለማድረግ ሙሉ መቤዠት ተዘጋጀ። መቤዠት ፍጹም የሚሆነውና የእግዚአብሔር ዓላማ የሚፈጸመው እንዲህ ሲሆን ብቻ ነው። ጌታ ኢየሱስ በሥጋ የመጣበትና በእርሱም የኖረበት ዓላማው "የመለኮት ሙላት በሰውነት ተገልጦ እንዲኖር" ነበር። ስለዚህ ኃጢአታችንን በሥጋው በእንጨት ላይ ተሸከመ በሞቱና በትንሣኤው ሰውነት ሥጋንና መንፈስን ከሃጢአትና ከሞት ኃይል አዳነ።

የዚህ መቤዠት የመጀመሪያ ፍሬ እኛን ከክርስቶስ ጋር አንድ አካልና መንፈስ አድርጉናልናል እኛ የእርሱ አካል ወይም ቤቱ ነን። ኢየሱስ በራሱ መንፈስ በመንፈሳችን ውስጥ የሚሠራው ሰውነታችን በትንሣኤ ጊዜ የመቤዠት ተካፋይ እንዲሆን ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ገና በምድር እያለ አስቀድሞ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተመቅደስ በመሆኑ የነፍስና የመንፈስ ቅድስና በበለጠ ክብር እንደገና እየተለወጠ እንዲሄድ ነው በዚያው ልክ ባለመነጠል ሥጋም የቅድስናው ተካፋይ እንዲሆን ነው።

የጌታን ራት ወይም ቅዱስ ቁርባንን በምንወስድበት ጊዜ ሕብስቱ እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋ ወይኑ ደግሞ እውነተኛው የክርስቶስ ደም በመሆን ይለወጣል የሚል ተቀባይነት የሌለው የስህተት ትምህርት አለ። ሐቁ ግን ቅዱስ ቁርባንን የክርስቶስ ሥጋ ለኃጢአታችን መቆረሱ ደሙም በመስቀል ላይ መፍሰሱን በማሰብ የምንወስደው በጌታ የተደነገገ ሥርዓት ነው።

ህብስቱን ስለመካፈል የተነገረው ሁሉ የክርስቶስን ደም በመጠጣት ሙሉ ገቢራዊነት ሊኖረው ይገባል። ውጤቱ ከክርስቶስ ጋር ፍጹም የልብ ወዳጅነትና ፍጹም አንድነት የሚያመጣ ጥልቅ መንፈሳዊ ምስጢር ነው ነፍስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የክርስቶስን ደም ሙሉ ተካፋይ በምትሆንበት እና በፈሰሰው ደሙ የተገለጠውን ወዳጅነት በምትጋራበት ስፍራ ተግባራዊ ይሆናል። ደም የሥጋ ሁሉ ሕይወት ነው ሕይወት ያለው በደም ውስጥ ስለሆነ (ዘሌ.17፡11) አማኞች ከክርስቶስ ጋር አንድ አካል በሆኑበት ስፍራ ፍጹም በክርስቶስ ውስጥ የመኖር ከፍተኛ ፍላጐት አለ። ደሙ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለሰማያዊው ሕይወት ከሰው ችሎታ በላይ የሆነ ኀይልና ብርታትን ይሰጣል። በደሙ ውስጥ በፈሰሰው የክርስቶስ ሕይወት የዳነው ኃጢአተኛ ሕይወት ነው። የአሮጌው ሰው "እኔነት" ሞቶ ለአዲሱ ሰው ለክርስቶስ ስፍራ ይከፈትለታል። ደሙን መጠጣት በክርስቶስ ሰማያዊ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ተሳትፎ ማድረግ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል ለዚህም "እምነት" ትልቁን እና በጣም የከበረውን ስፍራ ይይዛል።

## ለሚጠጣው ደሙ የእኛ አመለካከት

የተወደዳችሁ ወገኖች ሆይ፣ ጥልቅ ከሆኑት የእግዚአብሔር የሕይወት ምስጢሮች አንዱ በእኛ ውስጥ እንዳለ ተረድተናል። ደሙን መጠጣት ማለት ምን እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን ስንጠይቀው እና መረዳቱን በእኛ ውስጥ እንዲያፈሰው ስንጸልይ ጥልቅ በሆነ አክብሮት ወደ እርሱ በመቅረብ መሆን አለበት።

ከክርስቶስ ጋር የተሟላ ኅብረት ማድረግ የሚፈልግ ብቻ የክርስቶስን ደም መጠጣት ምን እንደሆነ መማር ይችላል። ጌታ ኢየሱስ "ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ" ብሏል (ዮሐ. 6፡56) ። በኃጢአቱ ይቅርታ ብቻ ረክቶ የተቀመጠ ነገር ግን የክርስቶስን ፍቅር እስከሚረካ ድረስ ለመጠጣት የማይጠማና በሙሉ ኃይሉ የሥጋን እና የነፍስን መዋጀት ለመለማመድ ያልወሰነ በክርስቶስ ውስጥ ያለው ስፍራ እንደተጠበቀ ቢሆንም ደሙን በመጠጣት ረገድ የሚኖረው ተካፋይነት ግን አነስተኛ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ "በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ" ያለውን የክርስቶስን ዓላማ የራሱ ዓላማ ያደረገ እና የዘለዓለም ሕይወት ኃይል በእርሱ ሰውነት እንዲሰራ የወሰነ በነዚህ ቃሎች ከባድነት ወይም ምስጢራዊነት በመፍራት አይጨነቅም እርሱ ከሰማይ እንደሆነና ወደሰማይ እንደሚሄድ የሚረዳ ሰማያዊ አስተሳሰብ እንዲኖረው ይናፍቃል። በከፍተኛ ጉጉት የሚናፍቀው ሥጋና ደሙ ከሰማይ እንደሆነ ይገነዘባል። መጠጣት ከሌለ የሚጠጣ ነገር አስፈላጊ አይደለም። ክርስቶስን እና



ከእርሱ ጋር ያለውን ፍጹም ኅብረት በጉጉት መጠበቅ ደሙን ለመጠጣት የተሻለ ዝግጅት ማድረግ ወይም መጠማት ነው።

የተጠማች ነፍስ ከሰማያዊ ሕይወት ሰጪ ውኃ ጠጥታ እንድትረካ የምትደረገው በመንፈስ ቅዱስ ነው። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የክርስቶስን ደም መጠጣት ሰማያዊ ምስጢር ነው። የሁሉም ዳኛ የሆነው እግዚአብሔር እና የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ክርስቶስ ባለበት "የመርጨት ደም" አለ (ዕብ. 12፡23-24) ከእኛ መረዳት በላይ የሆነው በእርሱ ዘንድ ያለውን እውነት መንፈስ ቅዱስ ወስዶ ያስተምረናል። የአካሉ ክፍል እንደመሆናችን ደሙን እና ሕይወቱን መካፈላችንን እና የደሙ ሕያው ኃይል በእኛ ውስጥ እንደተላለፈ ከክርስቶስ ጋር ባለን አንድነት በኩል መንፈስ ቅዱስ የሚገልጥልን የክብር መረዳት ነፀብራቅ ነው።

በምንጸልይበት ጊዜ ደሙን በእምነት እንደተቀበልንና እንደጠጣነው በማሰብ ሊሆን ይገባል። እያንዳንዱ የሰውነታችን ብልት የተጣራውን ደም ቬይን ወይም "የደም ቅዳ" ተብለው በሚጠሩ የደም ስሮች አማካይነት በልብ ግፊት ስለሚቀበል እያንዳንዱ የአካል ክፍል ወይም ብልት ያለማቋረጥና በቂ ደም ይደርሰዋል ስለዚህ እኛን ከክርስቶስ ጋር አንድ ያደረገን በክርስቶስ ውስጥ ያለ የሕይወት መንፈስ የክርስቶስን ደም በውስጣዊ ሕይወታችን ተለምዶአዊ ክንውን ያደርግልናል። ጌታ ኢየሱስ ሥጋውን ስለ መብላት እና ደሙን ስለመጠጣት ሲናገር የሰሙ አይሁድ "ይህስ የሚያሳጨንቅ ንግግር ነው" በማለት ቅሬታቸውን ገለጡ ኢየሱስም መልሶ "ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው ሥጋ ምንም አይጠቅምም" አላቸው እኛ በክርስቶስ፣ ክርስቶስ ደግሞ በእኛ ሲኖር ይህን መለኮታዊ ምስጢር በእኛ ውስጥ ሕይወትና ኃይል በማድረግ እንድንለማመደው ሊረዳን የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ይህን በረከት በእኛ ላይ እንዲያፈስሰው በእኛ በኩል እርግጠኛ እና ጠንካራ እምነት ሊኖር ይገባል። ክቡር ደሙ ያደረገውና የሰጠን በረከቶች ሁሉ ለእኛ እንደሆኑ ማመን አለብን። ጌታ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ደሙን ጠጥተን ሕያው እንድንሆን እንዳዳረገን፤በተሻለ ሁኔታ የተረዳናቸውን የደሙን ውጤቶች ይኸውም እርቅን፣ መንጻትን እና መቀደስን እንመን ከልባችንም የራሣችን አድርገን በመቀበል እንጠቀምባቸው።

ከዚያም በኋላ በታላቅ ደስታና ሐሴት ጌታን አ ! ጌታ ሆይ ደምህ ለእኔ የሕይወት ውሃ ነው በክቡር ደምህ አጥበህ አነፃኸኝ በየቀኑ "ክቡር ሥጋህን እንድበላና ደምህንም እንድጠጣ ታስተምረኛለህ ስለዚህ እኔ በአንተ እኖራለሁ አንተም በእኔ ትኖራለህ" በማለት ደፍረን መጸለይ እንችላለን ያለ ጥርጥር እርሱ ደግሞ ይህንን በሕይወታችን ያደርግልናል።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ድል በደሙ አማካይነት

**"እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሳ ድል ነሱት ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም" (ራዕይ 12፡11)**

የሰውን ሥፍራ ለመውሰድ ሰውን ወደ ስህተት በመራው በቀደመው እባብ እና በሴቲቱ ዘር መካከል በሺህ ለሚቆጠሩ ዓመታት ብርቱ ጦርነት ሲካሄድ ኖሯል አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ስትገለጥ በሌላ ጊዜ ደግሞ የክፋት ኃይላት ጊዜያዊ የበላይነት ሲያገኙ ጦርነቱ ወደ ተስፋቢስነት የሚያዘነብል ይመስል ነበር።

በጌታችን በኢየሱስ ሕይወትም ውስጥ እንዲሁ ሆኗል። በክርስቶስ መምጣት በአስደናቂው ቃሉ እና ሥራው መገለጡ ሲጠበቅ የነበረው የከበረው መቤዠት በከፍተኛ ፍጥነት ብዙዎችን ሲያነቃ የኢየሱስ ሞት በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ምን ያህል የሚያስፈራና ተስፋ የሚያስቆርጥ ሆኖ ነበር! እንደ እውነቱ ከሆነ የጨለማው መንግሥት አሸንፎ መንግሥቱን ለዘለዓለም የመሰረተ ይመስል ነበር።

ነገር ግን ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን ስንመለከት በጨለማው መንግሥት አስፈሪ መንኮታኮት አንጻራዊ ድል ተረጋገጠ። ጌታ ኢየሱስ ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት እርሱ ብቻ የሞትን መውጊያ በመስበር ወደ መንግሥቱ ገባ "በሞት ላይ ሥልጣን የነበረውን ዲያብሎስን በሞቱ ሻረ" በዚያች ቅዱስ ቅጽበት ጌታ ኢየሱስ ደሙን በማፍሰስ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሲሰጥ ሰይጣን ድል በድል የተንበሸበሸ ይመስል ነበር ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ጠላት የያዘ የመሰለውን ድል እስከ ዘለዓለም ከእጁ ተራገፈ።

መጽሐፍ ቅዱሳችን ለዚህ ሕያው ክንውን ታላቅ ምሣሌ ይሰጠናል። ጌታ ኢየሱስ ከሞት በመነሣት ወደ ላይ በማረጉ ምክንያት ሰይጣን ቁልቁል የተወረወረበትን ራዕይ እንደሚከተለው ያሳየናል። (ራዕይ 12፡5-9)

**"አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች ልጅዋም ወደ እግዚአብሔር ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ... ። በሰማይ ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውም፣ ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም**



**ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው፣ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ <u>ተጣለ</u> ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።"**

ቀጥሎም ምንባቡ በሰይጣን መጣል ምክንያት ስለተገኘው ድል የደስታ ዝማሬን ያቀርባል።

**"ታላቅም ድምጽ ከሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፦ አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና። እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሳ ድል ነሱት፣ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም" (ራዕይ 12፡10-11)**

ለሰይጣን መሸነፍ እና ለተከታዮቹ ከሰማይ መጣል ምክንያቱ የክርስቶስ ወደ ሰማይ ማረግ እና በሰማይ የተካሄደው ጦርነት ውጤት ሲሆን በሰማይ የተሰማው የድል ዝማሬ ደግሞ በዋነኝነት በበጉ ደም ላይ ያተኮረ የድል ዝማሬ ነው ድሉ የተገኘበት ኃይል መሠረቱ ደግሞ ደሙ ነው። በራዕይ መጽሐፍ በሙሉ በጉን በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ እንመለከተዋለን እንደ ታረደ በግ በመሆኑም በሰይጣን እና በሥልጣኑ ሁሉ ላይ በደሙ ድልን ተቀዳጀ። ደሙን ከብዙ ውጤቶቹ ጋር አይተነዋል ድል ሁልግዜ ከበጉ ደም ጋር የተያያዘ እንደሆነ መገንዘብ ይገባናል ስለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት።

*♦ በመጀመሪያ ድል አንድ ግዜ ለሁሉም ተገኝቷል ♦ ሁለተኛ የተገኘው ድል ለዘለዓለም ነው። ♦ ሶስተኛ እኛም የድሉ ተካፋይ ሆነናል።*

## አንድ ጊዜ ለሁሉም የተገኘው ድል

በምንባባችን ውስጥ የተመለከትነው ትልቅ ቁምነገር የሰው ታላቅ ጠላት በሆነው በሰይጣን በአንድ ወቅት ተይዞ ስለነበረው ሥልጣን ነው ይኸውም ሰይጣን ወደ ሰማይ በመግባት በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ወንድሞችን መክሰስና በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚደረገውን መልካም ነገር ሁሉ በጠላትነት የመቃወም ችሎታ ነበረው።

ይህ ሁኔታ በብሉይ ኪዳን እንዴት ይገለጥ እንደነበር እናውቃለን በመጽሐፈ ኢዮብ ላይ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር በእግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ኢዮብን የመፈተን ፈቃድ ሲያገኝ እንመለከታለን (ኢዮ. 2)። በትንቢተ ዘካርያስ ላይ ደግሞ የሚከተለውን እናነባለን "ታላቁን ካህን ኢያሱን በእግዚአብሔር መልአክ ፊት ቆሞ አሳየኝ ሰይጣንም ይከሰው ዘንድ በስተቀኙ ቆሞ ነበር" ይላል (ዘካ. 3፡1-2)፣ (ሉቃ. 10፡18) ጌታችን ኢየሱስ ስለ

ዲያብሎስ ውድቀት ሲናገር "ሰይጣንን ከሰማይ እንደመብረቅ ሲወድቅ አየሁ" ብሏል ኋላ ደግሞ በሕማማቱ ጊዜ ወደ መስቀል መከራ እንደቀረበ አውቆ እንዲህ አለ "አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጪ ይጣላል" (ዮሐ.12:31)።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን በሰማይ ውስጥ ያለ ፍጥረት አድርጎ እንዳቀረበው ስንመለከት እንግዳ ይሆንብናል ነገር ግን ይህንን ሐሳብ በቀጥታ ለመረዳት ሰማይ ጠባብ የመኖሪያ ሥፍራ እንዳልሆነ እግዚአብሔር እና ሰይጣን ተጎራብተው እንደማይኖሩ መገንዘብ አስፈላጊ ነው ሰማይ ከብዙ የተለያዩ ክፍሎቹ ጋር ዳር ድንበር የሌለው ስፍራ ነው ይህ መጠነ ሰፊ ስፍራ የእግዚብሔርን ፈቃድ በሚያገለግሉ በማይቆጠሩና በማይመጠኑ የመላእክት ሰራዊት የተሞላ ነው ሰይጣን ከመላእክቱ ጋር የሚኖርበት ስፍራ አለው መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን ጥቁር አስፈሪና አስቀያሚ አካል አድርጎ አይስልልንም ነገር ግን በአጠቃላይ ውጫዊ ሁኔታውን በመለወጥ "የብርሃን መልአክ" በመምሰል እንደሚገለጥ ይናገራል። ሰይጣን ሲሶ የመላዕክት አገልጋዮች ያሉት ገዥ ነው።

ሰይጣን በማሳትና በማደናገር የሰውን ውድቀት ሲያመጣ ዓለምን የራሱ ሲያደርግና የዓለም ገዥ ሲሆን በዓለም ውስጥ ባለው ነገር ሁሉ ላይ በአመጽ ሲሰለጥን ምኞት ነበረው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር "ሁሉንም ግዙዋቸው" በማለት ሰውን የዓለም ገዢ እንዲሆን አድርጎት ነበር። ሰይጣን የመጀመሪያውን የዓለም ንጉሥ ሰውን ካሸነፈ በኋላ በመንግሥቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ በራሱ ሥልጣን ስር አደረገ። ስለዚህ የሰይጣን ስልጣን እስከጊዜው ድረስ እውቅና ያገኘ ነበር ሰው ለሰይጣን ፈቃድ ተገዢ ከሆነ የጨካኝ አገዛዙ ሰለባ መሆኑ አይቀሬ በመሆኑ ሰው ለዘመናት የሰይጣን ጥቃት ሰለባ ሆኖ ኖሯል። በሞት ላይ ሥልጣንን ይዞ የአዳምን ዘር በሞት ፍርሃት በስልጣኑ ሲገዛ የነበረውን ጠላት እግዚአብሔር ፍጹም ሥልጣኑን በመጠቀም አልሻረውም ነገር ግን የሕግንና የእውነትን መንገድ መረጠ ሰይጣንም በመለኮት የአሠራር ፕላን ከሥልጣኑ እስከተሻረ ድረስ በአገዛዙ ላይ መቀጠል ተችሎት ነበር።

ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጅ ሰይጣንን በግዛቱ ለመዋጋትና ለማሸነፍ በሥጋ መጣ። ጌታ ኢየሱስ ከተቀባ በኋላ በይፋ አገልግሎቱን ሲጀምር የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በግልጥ ይታወቅ ዘንድ "ከዲያብሎስ ሲፈተን በመንፈስ ወደ ምድረበዳ ሄደ" በሰይጣን ላይ ድል መቀዳጀት ያስቻለው በግሉ ፈተናን ስለታገሰ እና ስለተቋቋመ ነው።

ቢሆንም ይህ ድል በቂ አልነበረም። "በሞት ላይ ሥልጣን የነበረውን ዲያብሎስን በሞቱ እንዲሽር ክርስቶስ በሥጋ መጣ" በእግዚአብሔር ሕግ ምክንያት ዲያቢሎስ በሞት ላይ



ሥልጣን ነበረው። ሕጉ እስረኞችን አሳሪ እንዲሆን ሥልጣን ሰጠው መጽሐፍ ቅዱስ "የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው" ስለሚል ሕጉ የጠየቀው የጽድቅ ጥያቄ ሳይሟላ ሰይጣንን መሻር በእርሱም ላይ ድል መቀዳጀት ፈጽሞ አልተቻለም። ኃጢአተኛ ከሰይጣን ሥልጣን ከመዳኑ በፊት በቅድሚያ ከሕግ ኃይል መዳን አለበት።

በፈሰሰው ደሙ እና በሞቱ በኩል ጌታ ኢየሱስ የሕግን ጥያቄ አሟላ። ሕጉም ያለ ማቋረጥ "የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው" በማለትና "ኃጢአትን የምትሰራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች" እያለ በይፋ ሲያውጅ በመቅደሱ ምሣሌያዊ አገልግሎት በደም መፍሰስና መርጨት መስዋዕት በኩል ሕጉ እርቅና መቤዠት ሊፈጸም የሚችለው በደም መፍሰስ ብቻ እንደሆነ አስቀድሞ መናገር ጀመረ። ዋስትናችን የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ከሕግ በታች ተወልዶ ያለ ምንም እንከን ሕግን ፈጸመ። ለሰይጣን ሥልጣን ራሱን ባለማስገዛት ፈተናውን ሁሉ ተቋቁሞ በፈቃዱ የኃጢአትን ቅጣት ለመክፈል ራሱን ሰጠ። የመከራውን ጽዋ ላለመጠጣት ከሰይጣን ለቀረበለት ምክር ጆሮውን አልሰጠም ሕጉን ለመፈጸም ሲል ደሙን ለማፍሰስ መላ ሕይወቱን እስከ ፍጻሜ ድረስ ለሞት አሳልፎ ሰጠ። ሕጉ ያለ ምንም እንከን ሲፈጸም የኃጢአትና የሰይጣን ሥልጣን ወደ ፍጻሜ መጡ ስለዚህ ሞት ሊይዘው አልቻለም "በዘለዓለም ኪዳን ደም" እግዚአብሔር "የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሳው" ስለዚህ ደግሞ እርሱ "በገዛ ደሙ ወደ ሰማያት ገባ" እና እርቁን እውን አደረገው።

የሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በሚያስደንቅ ሁኔታ ምስጢራዊ በሆነች ሴት የኢየሱስን በክብር ወደ ሰማያት መግባት ውጤት ይነግረናል።

**"አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች ልጅዋም ወደ እግዚአብሔር ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ… በሰማይም ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውምም፤ ከዚያም ወዲያ በሰማይ ሥፍራ አልተገኘላቸውም ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ። "**

**(ራዕ. 12:5፤7-9)**

ምንባቡ የሚገኝበት የመጽሐፍ ቅዱሳችን ክፍል "ከበጉ ደም የተነሣ … ድል ነሱት" የሚለውን የድል ዝማሬ ያስከትላል።

በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ከእስራኤል ወገን በሚቆመው በሚካኤልና በዓለም ተቃራኒ ኃይላት መካከል የተፈጠረውን የቆየ ግጭት እንመለከታለን።

ይሁን እንጂ ሰይጣን ከሰማይ ሊጣል የቻለው ከበጉ ደም የተነሣ ነው። ክርስቶስ በደሙ ባመጣው ከኃጢአት እርቅና የሕግ ፍጻሜ ሰይጣን የነበረውን ሥልጣን እና መብት ሙሉ በሙሉ አሳጣው ኃጢአትን በመደምሰስና ከመስመር በማስወጣት በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ነገር ሲያደርግ ያየነው ደሙ በሰይጣን ላይ ተመሣሣይ ኃይል አሰው ከዚህ የተነሣ ከእንግዲህ ወዲያ የከሳሽነት መብት የሰውም ምክንያቱም "አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሣቸው የወንድሞቻችን ከሣሽ ተጥሎአልና… ከበጉ ደም የተነሣ ድል ነሱት"

## ድሉ ለዘለዓለም ይቀጥላል

"ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ ደስ ይበላችሁ" በማለት ታላቅ የምሥራች በሰማይ ለሚኖሩት ሲያውጅ "ለምድርና ለባህር ወዮላቸው ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ ምድር ወርዷል" የሚለው ተስፋ አስቆራጭ የሚመስል አገላለጽ ለምድር ሲነገር ይስተዋላል ይሁን እንጂ ሰማያዊው ድል ወደ ምድር መተላለፉን በሚያበስረው አዋጅ ሲቀደድ ይታያል፡፡ በዚህም ምክንያት የመጀመሪያውን ድል ተከትሎ እድገት እያሳየ ወይም አድማሱን እያሰፋ የሚሄድ ድል እናያለን፡፡ ሰይጣን ከሰማይ ወደ ምድር መጣሉን ተከትሎ ሰማያዊው ድል ወደ ምድር ሽግግር ማድረግ ነበረበት ይህ ሁኔታ በድል ዝማሬ ውስጥ እንዲህ ሲል ተገልጧል "ከበጉ ደም የተነሣ ድል ነሱት" ይህ ድል በመጀመሪያ የተነገረው "ወንድሞች" የተባሉትን በሚመለከት ነበር ሆኖም የመላእክትንም ድል ደግሞ ይመለከታል፡፡ በሰማይና በምድር የተፈጸመው ድል በመከታተል በአንድ ጊዜ ለአንድ ዓላማ የተፈጸመ ድል ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ በማካሄድ ረገድ በሰማይ እና በምድር መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ ቀደም ሲል (ከትንቢተ ዳንኤል 10:12-13) ምንባብ ተመልክተናል ዳንኤል ጸሎቱን ሲጀምር ወዲያውኑ መልአኩ ብርቱ መሆን ጀመረ በሰማይ የተደረገው የሶስት ሳምንት ውጊያ ለሶስት ሳምንት በምድር የተደረገ የጾም ጸሎት ጊዜ ነበር፡፡ በምድር ላይ የሚደረገው ግጭት በማይታየው ሥፍራ በሰማይ የሚደረገው ግጭት ነጸብራቅ ነው፡፡ የሚካኤልና መላዕክቱ እንዲሁም በምድር ያሉት ወንድሞች በበጉ ደም ድል ተጎናጸፉ፡፡

በራእይ መጽሐፍ በአሥራ ሁለተኛው ምዕራፍ ግጭቱ እንዴት ከሰማይ ወደ ምድር እንደተሸጋገረ በግልጽ ተመልክተናል፡፡ "ስለዚህ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፣ ደስ ይበላችሁ ለምድርና ለባሕር ወዮላችሁ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እናንተ ወርዷልና… ዘንዶውም ወደ ምድር እንደተጣለ ባየ ግዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን



ሴት አሣደዳት" ሴቲቱ በኢየሱስ ደም ከተመሠረተችው ከእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሌላ ምሣሌ ልትሆን አትችልም ዲያብሎስ ኢየሱስን ከመስቀል ሞቱ የበለጠ መጉዳት ስለልቻለ የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ማሳደድ ቀጠለ የጌታ ኢየሱስ አሥራ ሁለት ደቀመዛሙርት እና በመጀመሪያው ሶስት ክፍለ ዘመናት የነበሩት አብያተቤተክርስቲያናት በዚያ ተላቅ መከራ ውስጥ አልፈዋል፡፡ በደም አፍሳሽ ስደት ውስጥ በመቶዎች እና በሺዎች የሚቆጠሩ ክርስትያኖች በአሰቃቂ ግድያ ሰማዕት ሆነዋል፡፡ ሰይጣን በከፍተኛ ደረጃ ይህንን ያደረገው ቤተክርስቲያንን ወደ ክህደት ለመምራት ወይም ከነ አካቴው ከሥሯ ነቅሎ ለመጣል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ "እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸው ቃል የተነሣ ድል ነሱት ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም" የሚለው ስለ ወንጌል ሰማዕት ከሆኑት ክርስቲያኖች ጋር የሚስማማ ነው፡፡

ከዘመናት ስደት በኋላ ለቤተክርስቲያን የጸጥታ እና የብልጽግና ዘመናት መጡ በዚህ አጋጣሚ ሰይጣን ከንቱን ነገር በኃይል ገፍቶ ወደ ቤተክርስቲያን ለማስገባት ሞከረ በዓለማዊነት አካሄድ ሕይወት የተሻለ ስኬት ሳያገኝ አልቀረም በቤተክርስቲያን ውስጥ ዓለም በመገለጧ ሁሉም ነገር ከብርሃን ወደ ጨለማ መሄድ ጀመረ በመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክ ክህደት በከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ በዚህ ፈታኝ ዘመን ውስጥ በመከራው መካከል የእምነት ገድል የተጋደሉ እና ሕይወታቸውን ለጌታ በመስጠት ምስክሮች የሆኑ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ስለዚህ "ከበጉ ደም የተነሳ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሱት ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም" የሚል ምስክርነትን አትርፈዋል፡፡

በተባረከው የተሐድሶ ኃይል አማካይነት ሰይጣን በቤተክርስቲያን ላይ አግኝቶ የነበረው ጊዜያዊ ድል ተንኮታኩቶበት ከበጉ ደም የተነሣ ድል ነሱት በእውነተኛ የወንጌል ስብከት "በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው አጸደቀን እርሱንም እግዚብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተሥሪያ አድርጎ አቆመው" (ሮሜ. 3:24-25)፡፡ ለተሐድሶ መሪዎች ይህ ቃል አስደናቂ ኃይል እና የከበረ ድል ሰጣቸው ከመታደስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ቤተክርስቲያን በስህተትና በሙትነት ላይ የአዲስ ሕይወትን ድል ለመቀዳጀት በክርስቶስ ክቡር ደም ስትታደስ ኖራለች በባእድ ሃይማኖቶች መካከል የሰይጣን ዙፋን ሳይነቃነቅ በሺህ ለሚቆጠሩ ዓመታት ኖሯል እስከ አሁን የሰይጣን ኃይል የሚፈርስበት መሣሪያ ደሙ ነው የመስቀሉ ደም ስብከት የዓለም ኃጢአት ተወግዶ እርቅ የመጣበት ነፃው የእግዚአብሔር ይቅርታ መሠረት የሆነው ፍቅር የሚገለጽበት ጽኑው ጨለማ የተገፈፈበት

የሰው ልብ የሚመለስበትና የሚከፈትበት የሰይጣን መኖሪያ ከመሆን ወደ እግዚአብሔር መቅደስነት የተለወጠበት ነው::

በቤተክርስቲያን የተደረገው ለእያንዳንዱ ግለሰብ ክርስቲያንም ጥቅም ነው:: ክርስቲያን ሁልግዜ "በበጉ ደም" ድል አለው ደሙ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ ኃጢአትን በማስወገድ ፍጹም እርቅን እንዳመጣ ሰይጣን በእኛ ላይ የነበረውን ሥልጣን ሙሉ በሙሉ እና ለዘለዓለም እንደአጣ የእግዚአብሔር ውለታ በሙሉ ዋስትና በልባችን ውስጥ እንደሚሰራ እና የኃጢአትን ኃይል እንዳወደመ ነፍስ ስትረዳ እና በደሙ ኃይል ውስጥ ስትኖር የሰይጣን ፈተና ወጥመድ ሰለባ ከመሆን ይቀርላታል። የበጉ ቅዱስ ደም በሚረጭበት ስፍራ እግዚአብሔር ሲኖር ሰይጣን ደግሞ በርሮ ይጠፋል። "በበጉ ደም ድል ነሱት" የሚለው ቃል በሰማይ ፣በምድር እና በልባችን ውስጥ ሁልግዜ የድል ነጋሪ ሆኖ ማወጁን ይቀጥላል።

## በዚህ ድል ውስጥ የእኛ ድርሻ ምንድን ነው?

በበጉ ደም ከነጹት መካከል እንዳለን ስንረዳ የድሉ ተካፋይ እንሆናለን የድሉ ሙሉ ደስታ እንዲኖረን ለሚከተሉት እውነቶች ትኩረታችንን መስጠት አለብን።

## መንፈሳዊ ውጊያ ማካሄድ
## ያለ ውጊያ ድል የለም

በጠላት ግዛት ውስጥ እንደምንኖር መገንዘብ አለብን። ለሐዋርያው ዮሐንስ የተገለጠለትን ሰማያዊ ራዕይ በዕለታዊ ሕይወታችን ማስታወስ አስፈላጊ ነው ሰይጣን ከሰማይ ወደ ምድር ሲጣል ጥቂት ጊዜ እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ተሞልቷል ወደ ከበረው ክርስቶስ መድረስ አይችልም ነገር ግን የእርሱን ቅዱስ ሕዝብ በመዋጋት ወደ እርሱ ለመድረስ ይፈልጋል። ሁልግዜ በመንቃት በቅዱስ ሕሊና መመላለስ አለብን ባልጠበቅነው ሁኔታ በጠላት ኃይል ተታልለን ሳይሰለች እኛን በከፊል ወይም ሙሉ በመሉ በሥልጣኑ ስር እንዳያደርገን ነቅተን ልንጠብቅ ይገባል። ዲያብሎስ በቀጥታ የዚህ ዓለም ገዥ ተብሎ ተጠርቷል በዓለም ያለው ሁሉ እርሱን ለማገልገል የተዘጋጀ ነው ስለዚህ ዓለምን ተጠቅሞ ቤተክርስቲያን ለጌታዋ ታማኝ እንዳትሆን እንዴት እንደሚሰራ ያውቃል ቢሳካለት በመንፈሱ ማለትም በዓለም መንፈስ ሲሞላት ይፈልጋል።

ሰይጣን ከፍተኛ ግምት የምንሰጠውን ኃጢአት ብቻ ለመፈተኛነት አይጠቀምም ነገር ግን በኑሮአችን፣ በሥራችን ፣በእለት እንጀራ ፍለጋችን፣ በሚያስፈልገን ገንዘብ፣



በፖለቲካችን፣ በንግድ ልውውጣችን፣ በሥነ-ጽሑፋችን፣በሣይንሣችን፣ በእውቀታችን እና በሁሉም ነገር እንዴት በር አስከፍቶ እንደሚገባና ለእርሱ አጋንንታዊ ማሣሣቻ የጥፋት መሣሪያ አድርጎ እንደሚጠቀምበት ያውቃል።

በበጉ ደም በሰይጣን ላይ ድል አድራጊነትን ለመቀዳጀት የወሰነ ክርስቲያን ሁሉ ተዋጊ መሆን አለበት። የጠላቱንም ባህርይ ለመረዳት ጥረት ማድረግ አለበት። የሰይጣን ድብቅ ተንኮል ሰዎችን የሚያሳውርበትና የሚያስትበት መጽሐፍ ቅዱስ "የሰይጣን ጥልቅ ነገር" እንደሚለው (ራዕይ 2:24) በቃሉ በኩል ከመንፈስ ቅዱስ ለመረዳት ራሱን መስጠት አለበት። ይህ ተጋድሎ "ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዥዎች ጋር በሰማያዊው ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር" መሆኑን መገንዘብ አለበት (ኤፌ. 6:12) ። አማኝ በሁሉም ነገር ራሱን ለእግዚአብሔር በመስጠት የተጠየቀውን ዋጋ ከፍሎ ጦርነቱን እስከ ሞት ድረስ መጋደል አለበት። "ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሱት ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም" የሚለውን የድል ዝማሬ መዘመር የሚችለው ይህ ሲሆን ብቻ ነው።

## ድል የምናደርግበትን እምነት መያዝ

"ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው?" (ዮሐ. 5:4-5)። ጌታ ኢየሱስ "ደስ ይበላችሁ" ብሏል "እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" (ዮሐ.16:33) ሰይጣን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሸነፈ ጠላት ነው በጌታ ኢየሱስ ውስጥ ባለው ሰው ላይ ሰይጣን አንድ ነገር የማድረግ ሥልጣን የለውም ባለማመን፣ ባለማወቅ ወይም የክርስቶስን ድል ተሳታፊነቴን ቸል በማለት ሰይጣን እኔን በተንኮሉ እንዲያስት እድል ልሰጠው እችላለሁ አለበለዚያ በእኔ ላይ እንዳች ስልጣን የለውም። ከጌታ ኢየሱስ ጋር አንድ እንደሆንኩ ኢየሱስ በእኔ ውስጥ እንደሚኖር እና ድሉን በእኔ ውስጥ እንዳስቀመጠና እንደሚጠብቀው በሕያው እምነት ስረዳ የዚያን ጊዜ ሰይጣን በእኔ ላይ ኃይል የለውም በበጉ ደም የተገኘው ድል ደግሞ የሕይወቴ መሠረት ነው።

በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ብርታት እና ታላቅ ደስታን በውስጣችን ሊያነሣሣ የሚችለው ይህ ዓይነቱ እምነት ብቻ ነው። በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች በመያዝ እኛን ለመፈታተን የሚያደርገውን እረፍት የለሽ ጥረት እና የጥፋት ኃይሉን በማሰብ ሁልግዜ

እንዲህ ባለ ውጥረት በነገሰበት ሁኔታ ውስጥ እንዴት መኖር ይቻላል ፈተናው በጣም የሚያስጨንቅ ነው አ! በፍጹም የማይቻል ነገር ነው በማለት ልናስብ እንችላለን፡፡ይህ ሃሳብ ያለ ጥርጥር እውነት የሚሆነው በደካማ ተፈጥሮአችን ጠላትን ለመግጠም ወይም በራሳችን ብርታት ድሉን ለማግኘት የተነሣሣን እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን እንድናደርግ አልተጠራንም ኢየሱስ ድል ነስቷል ሰይጣን በኢየሱስ ከሰማይ እንደተጣለ በሚናገረው ሰማያዊ ራዕይ ነፍሳችንን መሙላት አለብን ኢየሱስ በደሙ እንዳሸነፈ እንደዚሁም የደሙን ኃይልና ድል ሊሰጠን ሁልግዜ ከእኛ ጋር እንዳለ በእምነት መሞላት አለብን የዚያን ጊዜ እኛም ደግሞ "በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን" ማለት እንችላለን፡፡

## በበጉ ደም ኅብረት ውስጥ ድል አድርጊነት እንዳለ መረዳት

እምነት በአእምሮዬ የምይዘው ሃሳብ አይደለም አእምሮዬን የሞላ መረዳትም አይደለም እምነት ሕይወት ነው፡፡ እምነት ነፍስን ከእግዚአብሔር እና ከማይታየው ሰማያዊ ሥፍራ ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ መሣሪያ ነው፡፡ ከዚያም በላይ ከክርስቶስ ደም ጋር የሚያገናኝ ነው ራሴን ሙሉ በሙሉ ወደ ደሙ በማምጣት ከኃይሉ ስር ሳላስገዛ በሰይጣን ላይ ድል አገኛለሁ ብዬ ማመን የሚቻል ነገር አይደለም፡፡

በደሙ ኃይል ማመን ኃይሉን የመለማመድን ፍላጎት በውስጣችን ይቀሰቅሳል ኃይሉን በግል መለማመድና ድሉን በበለጠ ክብር ማመን ያመጣል፡፡

ያንተ ወደ ሆነው ፍጹም እርቅ ከእግዚአብሔር ጋር ጠልቀህ ለመግባት ፈልግ "ደሙ ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል" በሚለው ቃል እምነትን ተለማመድ ጸንተህም ኑር የሚቀድሰው እና ሕይወት ሰጪው ደሙ የነፍስህ ምግብና ኃይልህ ይሁን የዚያን ጊዜ በሰይጣንና በፈተናዎቹ ላይ ያልተሸራረፈ የድል አድራጊነት ልምምድ ይኖርሃል፡፡ ራሱን በመስጠት ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚራመድ ካህን እንደ አሸናፊ ንጉሥ በሰይጣን ላይ ድል ነሺ በመሆን ትመላለሳለህ፡፡

ውድ አማኞች ጌታችን ኢየሱስ በደሙ ካህናት ብቻ አላደረገንም ነገር ግን ለእግዚአብሔር ነገሥታት አድርጎናል፡፡ በክህነት ንጽህናና አገልግሎት ብቻ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የለብንም በተጨማሪም ደግሞ በንጉሣዊ ኃይል ለእግዚአብሔር እንገዛለን፡፡ የንግሥና መንፈስ ሲሞላን ያስፈልጋል የንጉሣዊነት ብርታት በጠላቶቻችን ላይ ይገዛል የበጉ ደም



ምልክትነትና ማህተም እየጨመረ መሄድ ያለበት ከኃጢአት እዳ ነፃ ወጥቶ ለመታረቅ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም በኃጢአት ኃይል ሁሉ ላይ ድልን ለመቀዳጀትና ለመግዛት ነው፡፡

የክርስቶስ ትንሣኤና እርገት እንዲሁም የሰይጣን መጣል የክርስቶስ ደም መፍሰስ ውጤቶች ናቸው፡፡ የመርጨት ደም በአንተም ውስጥ ከክርስቶስ ጋር ሙሉ የትንሣኤው ደስታ ተካፋይ እንድትሆን በር ከፍቶልሃል በተጨማሪም ከእርሱ ጋር በሰማያዊ ሥፍራ እንድትቀመጥ አድርጎሃል፡፡

በድጋሚ አንድ ግዜ የውስጣችሁን ሁለንተና ከፍታችሁ የክርስቶስን የደም ኃይል ወደ ውስጣችሁ እንድታስገቡ እጠይቃችኋለሁ፡፡ ሕይወት ባለማቋረጥ የክርስቶስን ትንሣኤና እርገት የሚያከብር እና በሲኦል ኃይላት ላይ ደግሞ ያለተቋረጠ ድልን የሚያበስር ይሆናል፡፡ ልብህ/ሽም ያለማቋረጥ ከሚከተለው ሰማያዊ ዝማሬ ጋር አንድ ይሆናል፡፡ ዝማሬውም እንዲህ ይላል፦ "አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ድል ነሱት" (ራእይ 12፡10-11)፡፡

# ምዕራፍ አሥር

## በደሙ አማካይነት ሰማያዊ ሐሴት

"ከዚህ በኋላ አየሁ፣ እነሆም አንድ ስንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ... በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ... በታላቅ ድምጽም እይጮሁ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ። እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ልብሣቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ" (ራዕይ 7:9-14)።

ይህ ቃል በሰማያዊ ክብር ውስጥ ስላሉት ማንም ሊቆጥራቸው ስለማይችል ታላቅ ሕዝብ የሚገለጽ ራዕይ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ እነዚህን ሰዎች በእግዚአብሔር እና በበጉ ዙፋን ፊት ቆመው በራዕይ አየ ወተት የመሰለ ረጅም ልብስ ለብሰው የዘንባባ ዝንጣፊዎች ደግሞ በእጆቻቸው ይዘው ነበር። በታላቅ ድምጽም እየጮሁ "በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው" እያሉ ይዘምሩ ነበር። ይህን የድልና የአክብሮት ዝማሬ መላዕክት ሁሉ ተቀብለው በዙፋኑ ፊት በግንባራቸው እየወደቁ እግዚአብሔርን በማምለክ ለእርሱ ዘዓለማዊ ምሥጋናንና ክብርን በማቅረብ ምላሽ ይሰጣሉ።

በዚህ መካከል ከሽማግሌዎች ውስጥ አንዱ ነጩን ልብስ ወደ ለበሱት ማንም ሊቆጥራቸው ወደማይችለው ሕዝብ በእጁ እያመለከተ ዮሐንስን እንዲህ ሲል ጠየቀው "እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ ?" ዮሐንስም መልሶ "ጌታ ሆይ አንተ ታውቃለህ" በማለት መልስ ሰጠ ሽማግሌውም መልሶ "እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል" አለው። ይህ ገለጻ የተሰጠው ዙፋኑን ከበው ከቆሙት ሽማግሌዎች ከአንዱ ነው በሰማያዊ ክብራቸው ውስጥ ያሉትን የተዋጁትን ሁኔታ የሚመለከተው ይህ ገለፃ ትልቅ ትርጉም አለው።

የክርስቶስ ኢየሱስ ደም የኃጢአተኞች ተስፋ የሆነው በዚህ ዓለም ኃጢአትና ጦርነት ላይ ብቻ ሳይሆን በሰማይም እንደሆነ ከላይ የተመለከትነው ምንባብ ያስረዳል ጠላት ሁሉ ተገገር ሲሆን ያ ክቡር ደም የድነታችን መሠረት እንደሆነ ለዘለዓለም ግንዛቤ ያስገኛል። ደሙ በእግዚአብሔር ዘንድ በሰማይ ኃይሉን መግለጥ ያለበት በታች በምድር ያለውን ኃጢአት ለመክደን ብቻ እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን። በደሙ ተዋጀው ሁሉ ድነቱን ሙሉ በሙሉ በደሙ እንዳገኘ ለዘለዓለም ለደሙ ምሥጋናና ክብር ምስክር ይሆናል።



ድነታችንን ሙሉ በሙሉ በደሙ እንዳገኘን ግልጽ መረዳት ካለን በመርጨት ደም እና በሰማያዊ ደስታ መካከል ያለውን እውነተኛ እና ተገቢ ግንኙነት በተሻለ ሁኔታ መረዳት እንችላለን። አማኙ በምድር እያለ ከደሙ ጋር የሚኖረው እውነተኛ የቅርብ ግንኙነት ገና በምድር እያለ እንኳ ሰማያዊውን ደስታና ክብር መካፈል እንዲችል ያደርገዋል። በደሙ በኩል በሰማይ ታላቅ ደስታ የሚሆንበት ምክንያቱ፡-

*• በመጀመሪያ ወደ በሰማያዊ ስፍራ መልሶ ያስገባን ደሙ ስለሆነ • ሁለተኛ ለሰማያዊ ደስታ ብቁ ስላደረገን እና • በመጨረሻም የሰማያዊ ዝማሬን ልምምድ ስለሰጠን ነው።*

## ደሙ በመንግሥተ ሰማይ ትክክለኛ ስፍራ ይሰጣል

"እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ?" የሚለው ጥያቄ የምንባቡ መሪ ሐሳብ እንደሆነ ልብ ልንል ያስፈልጋል። ከሽማግሌዎች አንዱ እነዚህ ታላቅ ውለታ የተደረገላቸው በዙፋኑና በበጉ ፊት የቆሙት በእጆቻቸውም የዘንባባ ዝንጣፊዎች የያዙት እነማን ናቸው? በማለት ትኩረትን የሚስብ ጥያቄ ይጠይቃል በመቀጠልም አቋማቸውንና አለባበሳቸውን በመግለጥ "ከወዴት መጡ?" የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል ቀጥሎም "ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው" የሚል መልስ ሲሰጥ "እነማን ናቸው?" ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ልብሳቸውን በበጉ ደም አጥበው ያነጹ ናቸው የሚል መልስ እናያለን።

ቀልብን ከሚስበው ልዩ መለያቸው አንዱ ልብሳቸውን በበጉ ደም አጥበው ማንፃታቸው ሲሆን ይህ ሁኔታ ብቻውን የክብርን ስፍራ እንዲይዙ አደረጋቸው። የሚቀጥለውን ቃል ካስተዋልን ግልጽ ማስረጃ ይሆንልናል ቃሉም "ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ ሌሊትና ቀን በመቅደሱ ያመልኩታል በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል" ይላል "ስለዚህ" የሚለው አያያዥ ቃል የሚገልጸው ሰዎቹ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ያሉት በደሙ ምክንያት እንደሆነ ነው። ከፍ ያለውን የክብር ስፍራ እንዲይዙ ካደረጋቸው ከበጉ ደም ጋር በአንድነት ተሣሥረዋል። ደሙ ወደ ሰማያት እንዲገቡ አዳርጓቸዋልና።

ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግባት መብት የሚለውን ከተፈረደበት የሰው

ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ጋር እያይዞ መናገር ይቻላል? አዎን ይቻላል። ይህም የሆነው የኢየሱስን የደሙን ዋጋ እና የፈሰሰበትን ዓላማ ትክክለኛ ግንዛቤ ያገኘን እንደሆነ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ወደ መንግሥቱ በክርስቶስ ደም በነፃ ፀጋ እንዴት እንደተቀበለ

የተረዳን እንደሆነ ነው አለበለዚያ ስለኃጢአታችን እና ስለእግዚአብሔር ፀጋ የተሳሳተ አስተሳሰብ ይዘን ይሆናል ይህም ከሆነ አዳኛችን ለእኛ ላዘጋጀው ክቡር የመዋጀት ደስታ የማንበቃ እንሆናለን።

ሰይጣን ከሰማይ እንደተጣለ እና እግዚአብሔርም ሁልግዜ በሕጉ እንደሚሰራ ተመልክተናል ሰይጣን ባይጣል ኖሮ በሕጉ መሠረት ኃጢአተኛ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሌላ መግቢያ ሊያገኝ አይችልም። ነቢዩ ኢሣያስ "ጽዮን በፍርድ ከእርስዋም የሚመለሱ በጽድቅ ይድናሉ" ብሏል (ት.ኢሣ. 1:27)። ሐዋርያው ጳውሎስም "ፀጋ በጽድቅ ምክንያት ነገሠ" ብሏል (ሮሜ 5:21)። እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም የላከበት ዋና ዓላማ ይህ ነው። ፀጋን አሳንሶ መንግሥተ ሰማይ የመግባትን መብት ለመናገር ከመድፈር ይልቅ መግባት የሰጠንን ታላቁን የክብር ፀጋ መመልከት እና ማክበር መልካም ነው። ወደ መንግሥቱ የገባንበት ታላቁ የክብር ፀጋ አንዳንድ ጊዜ በቤተክርስትያን ውስጥ ከሚጠበቀው በታች ወርዶ ይገኛል። ከጥቂት ቀናት በፊት ከሞት በኋላ ወደ መንግሥተ ሰማይ የመሄድ ተስፋ እንዳለው ይናገር ከነበረው አንድ ሰው ጋር ስንነጋገር ተስፋውን በምን መሠረት ላይ እንዳደረገ ጠየቅሁት በምንም ዓይነት ሁኔታ ስለ ሕይወቱ ግድየለሽ እንደማይሆን በራሱም ጽድቅ ላይ ፈጽሞ እንደማይደገፍ እንዲህ ሲል መልስ ሰጠ "ጌታን ለመፈለግና ፈቃዱን ለማድረግ የተቻለኝን ያህል ጥረት አደርጋለሁ" እኔም መልሼ በቅዱሱ እግዚአብሔር የፍርድ ዙፋን ፊት ለመቆም መሠረት ሊሆንህ አይችልም ብዬ ስነግረው ወዲያውኑ ስለ እግዚአብሔር ምህረት አነሣብኝ እኔም መልሼ ከምህረት በላይ የሚያስፈልገው ነገር እንዳለ ይኸውም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግቦት ብቸኛ ዋስትናው የእግዚአብሔር ጽድቅ እንደሆነ ሲሰማ አዲስ ነገር መሰለው ብዙዎቹ በእምነት መጽደቅ የሚለውን ስብከት መስማት ይፈራሉ ነገር ግን በእምነት ካልጸደቁ የዘለዓለምን በረከት መካፈል እንደማይችሉ ግንዛቤ የላቸውም።

ሙሉ መረዳት ሳይኖረው ስለ ክርስቶስ ምስክርነት ከሚሰጥ ይልቅ ነገር ግን የክርስቶስን መከራ እንዲረዳ የእግዚአብሔር መንፈስ ያበራለት ልብ መካከል ሰፊ ልዩነት አለ።

አንድ ኃጢአተኛ ለሞት ቀርቦ በአልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ ብዙ ገፆች ያሉት አንድ ትልቅ መጽሐፍ በገፆቹ ውስጥ የእርሱ በጣም ብዙ ኃጢአቶች መፃፋቸውን ተጠቆመና እንግዲህ ያለው ተስፋ ምን እንደሆነ ተጠየቀ እርሱም በቀኝ እጁ ጣት ወደ ግራ እጁ መዳፍ እያመለከተ በምስማር የተወጋ እጅ እንዳለ አሣየ። ከተወጋው እጅ ውስጥ ደም እንደፈሰሰ



እስቦ በመጽሐፉ ገፆች ላይ የተፃፉት ብዙ ኃጢአቶች በዚያ ደም እንደተደመሰሱ ገለጸ የበጉም ደም የተስፋው መሠረት እንደሆነ አስረግጦ ተናገረ።

አማኝ ኃጢአተኛን የበጉ ደም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባትን ሰጥቶታል "የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" ደሙን በማፍሰስ የኃጢአትን ቅጣት ተሸከመ በእኛ ቦታ ራሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አደረገ በዚህ ምክንያት የኃጢአት ቅጣት ተከፈለ የኢየሱስ ደም ቤዛ ሆኖ ስለፈሰሰ በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት ለኃጢአት ይቅርታ የፈሰሰ ደም ሆኖ ወደ ዙፋኑ ቀረበ። የእግዚአብሔር ጽድቅ ቅጣትንና መታዘዝን በተመለከተ ሕጉ የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት የኃጢአተኛ ዋስትና እንደተረጋገጠለት ያውጃል በክርስቶስ ያመነውን ኃጢአተኛ ጻድቅ ነህ ብሎ እግዚአብሔር ይመሰክርለታል። ክርስቶስ ለእኔ ሁሉን ነገር እንዳደረገልኝ ማረጋገጫው እምነት ነው። የእግዚአብሔር የጽድቅ አዋጅ ከሕጉና ከትክክለኛነቱ የሚያውጀው አዋጅ ሲሆን ለእኔ ደግሞ ድነት የሚል መጠሪያ ያስጠኛል። የእግዚአብሔር ጸጋ ወደ መንግሥቱ እንድገባ አደረገኝ የበጉ ደም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግቢያዬ ማረጋገጫ ነው። በዚያ ደም ከነፃሁ ሞትን በሙሉ መተማመን ልገናኘው እችላለሁ ወደ ሰማይ መግባት ተሰጥቶኛልና።

ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ፈቃድና ተስፋ የቀረላችሁ ሁሉ፡- "በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ስፍራ የሚያገኙ እነማን ናቸው?" ለሚለው ጥያቄ የተሰጠውን መልስ በጥንቃቄ ስሙ "ልብሳቸውን አጥበው በበጉ ደም አነጹ" ማጠብ የሚከናወነው በሰማይ አይደለም በሞትም ውስጥ አይደለም ነገር ግን በምድር በሕይወታችን ዘመን ነው ራሣችሁን በመንግሥተ ሰማይ ተስፋ አታታልሉ በዚያ ክቡር ደም ካልነጻችሁ በእውነት ካልነጻችሁ ከቶ ወደ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም። ውድ ክርስቲያን ሆይ! ክርስቶስ ራሱ በገዛ ደሙ እንዳነጻህ ሳትገነዘብ ሞትን አትገናኘው።

## ደሙ ለመንግሥተ ሰማይ ብቃትን ይሰጣል

ለሰዎች በማንኛውም ነገር ላይ መብት ቢሰጣቸውና በእርሱ የመደሰት ብቃት ካላገኙ ምንም ትርጉም የለውም። ምንም እንኳ ስጦታው ውድ ቢሆንም በስጦታው ለመደሰት የሚደረገው ውስጣዊ ዝግጅት አናሣ ከሆነ ስጦታው ዋጋ የለውም ሰዎች ሳይዘጋጁ ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት ቢሰጣቸው ተገቢው ደስታ አይሰማቸውም። በአንጻሩም ከእግዚአብሔር ፍጹም ሥራ ጋር ይጋጫሉ።

የኢየሱስ ክርስቶስ የደሙ ኃይል ለኃጢአተኛ የሰማያትን በር ብቻ አልከፈተም ነገር ግን ወደ ሰማያት የሚገባበትን መለኮታዊ ሥራ ሰርቶለታል የሰማይ በረከት ወደ እርሱ እንዲቀርብም አድርጎለታል እንዲሁም ለእያንዳንዱ በረከት ብቃትን ሰጥቶታል። ለሰማይ በረከት ምን ሕግ አለው ? ብቃትን ለማግኘትስ ምን ዝግጅት ያስፈልገዋል? ለሚሉት ለነዚህ ጥያቄዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባችን ውስጥ ምላሽ ይሰጣል። **"እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፣ ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያደርባቸዋል። ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፣ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሙም፣ ፀሐይም ትኩሳትም ሁሉ አይወርድባቸውም በዙፋኑም መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናል፣ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።"**

(ራዕይ 7:15-17)

ከእግዚአብሔር እና ከበጉ ጋር ኅብረት ማድረግ እና መቅረብ ሰማያዊ በረከትን ይሰጣል። በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት መሆን፣ ፊቱን ማየት፣ በመቅደሱ ቀንና ሌሊት እርሱን ማገልገል፣ በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ከለላ ስር መሆን፣ በበጉ ጥበቃና እንክብካቤ ሥር የመሆን የመንግሥተ ሰማይ በረከቶች መሠረታቸው ከእግዚአብሔር እና ከበጉ ይልቅ በሌሎች ነገሮች ቢሆኑ ኖሮ ምን ያህል ትንሽ በሆኑ ነበር። እግዚአብሔርን ማየት ወደ እርሱ መቅረብ በእርሱ መታወቅ፣ መወደድና በእርሱ ጥበቃ ውስጥ ከመሆን የበለጠ በረከት የለም።

## የፈቃድና የአእምሮ ውስጣዊ ስምምነት

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አንድ ከመሆን ውጭ ለእግዚአብሔር መንግሥት መብቃትን የሚገልጽ ሐሳብ አይገኝም። ሁለቱም ሳይስማሙ እንዴት አብረው መሄድ ይችላሉ? እግዚአብሔር ብቻውን ቅዱስ ስለሆነ ኃጢአተኛውም ከኃጢአቱ መንጻትና መቀደስ አለበት አለበለዚያ የእግዚአብሔር መንግሥት ደስታ የሚጠይቀውን ባለማሟላት ሙሉ በሙሉ ብቃት የሌለው ሆኖ ወደ ውጭ ይቀራል። "ያለ ቅድስና ማንም ሰው እግዚአብሔርን ማየት አይችልም" የሰው ተፈጥሮ በጠቅላላ መታደስ አለበት ከዚያም በኋላ ሐሳቡ፣ ምኞቱ፣ ፈቃዱ እና ድርጊቱ በጠቅላላ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይሆናል። መታዘዝ ስንል ሕግን ለመጠበቅ የሚደረገውን ከንቱ ሙከራ ማለታችን አይደለም። ማንም ሰው በተፈጥሮ ማንነቱ ተነሣስቶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ አይችልም። ቅድስና የሰው ባህሪይ መሆን አለበት።



ቀደም ሲል የተመለከትናቸው ታላላቅ በረከቶች የበጉ ደም ያስገኛቸው ናቸው። "የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል" እርቅና የኃጢአት ይቅርታ በመንፈስ ቅዱስ ሲፈጸሙ በሕያው እምነት ደግሞ ጽናትን ያገኛሉ። ደሙ የኃጢአት ምኞትንና ፍላጐትን በመግደል በአስደናቂ መለኮታዊ የማንጻት ኃይሉ ይሰራል። የኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ኃይል በደሙ ውስጥ ይሰራል ከእርሱ ጋር ለኃጢአት ሞተናል በደሙ በኩል ባለን የእምነት ግንኙነት የኢየሱስ የሕይወቱ ኃይል ወደ ውስጣዊ ተፈጥሮአችን በኃይል ዘልቆ ይገባል ደሙ የኃጢአትን ኃይል ይሰብራል ከኃጢአትም ሁሉ ያነጻል።

ደሙ ማንጻት ብቻ ሳይሆን ይቀድሳልም መንጻት የድነት አንዱ ክፍል እንደሆነ ተመልክተናል ይህም የኃጢአት መወገድ ማለት ነው። ደሙ ከዚህም የበለጠ ነገር ያደርጋል የእግዚአብሔር ርስት እንድንሆን አደረገን ኢየሱስ ደሙን ሲያፈስስ በውስጣችንም ያደረገው ይህንኑ ነው እኛ ደግሞ በእውነት የተቀደስን እንሆን ዘንድ ደሙን በማፍሰስ ራሱን ስለእኛ ቀደሰ በዚያ ቅዱስ ደም ስንደሰት እና ራሳችንን ስንሰጥ ለእግዚአብሔር ፈቃድና ክብር ሙሉ በሙሉ ስንማረክ በጌታ ኢየሱስ ውስጥ የተገለጠው የመስዋዕትነትና በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ የመኖር ኃይል በእኛም ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል።

ራሳችንን ባዶ እና ምርኮኛ እንድናደርግ ደሙ ቀደሰን ስለዚህ እግዚአብሔር እኛን ርስቱ በማድረግ ውስጣችንን ይሞላል። እውነተኛ ቅድስና በእግዚአብሔር መያዝና መሞላት ነው። ይህ ተግባር የሚከናወነው በበጉ ደም ነው እኛም በማይነገር ሐሴት እግዚአብሔርን በሰማይ ለመገናኘት በዚህ በምድር እንዘጋጃለን።

## ወደ እግዚአብሔር በመቅረብና ከእርሱም ጋር ህብረት በማድረግ መደሰት

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ዓይነት ፈቃድ የሚኖረው ወይም ለእግዚአብሔር መንግሥት ተስማሚ መሆን የሚመጣው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ከማድረግ ፍላጎትና ደስታ ነው። በዚህ ውስጥ ደግሞ ደሙ በምድር እያለን ለሰማይ እውነተኛ ዝግጅት እንድናደርግ ኃይል ይሰጠናል። ደሙ እንዴት ወደ እግዚአብሔር እንዳቀረበን እና ወደ ክህነት አገልግሎት እንደሚመራን ተመልክተናል የእግዚአብሔር መገኛ ወደ ሆነው ወደ ቅድስት ለመግባት መኖሪያችንንም በዚያ ለማድረግ በደሙ ነፃነት አግኝተናል። ደሙ በሚረጭበት ጊዜ የጸጋው ዙፋን በዚያ ይኖራል የሚለውን ታላቅ ሐሳብ ከደሙ ጋር አያይዞታል ልባችን ከደሙ

ሙሉ የሥራ ኃይል ሥር ሲቀመጥ የእግዚአብሔር መኖሪያ ይሆናል ያ ልብ ድነቱንም ይለማመዳል ደሙ ከእግዚአብሔር እና ከበጉ ከኢየሱስ ጋር የህብረት ልምምዱን እውን አደረገልን "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ" ያለውን ቃል ረስተን ይሆን? የደሙ ኃይል ሙሉ በረከት ከከበረው ፍሬ ጋር ያለው ከክርስቶስ ጋር በፍጹም አንድነት በመኖር ውስጥ ነው። ሥራውን ከሠሪው እና ደሙን ከክርስቶስ የሚለየው የእኛ አለማመን ብቻ ነው በደሙ ያነፃን ያቀረበን እና እንድንጠጣው ያደረገን ክርስቶስ ራሱ ነው በሰማይ ከአብና ከወልድ ጋር ሙሉ ኅብረት ማድረግ የምንችለው በደሙ በኩል ብቻ ነው።

የተዋጀህ ክርስቲያን ወገን ለሰማይ መንግሥት እንድትዘጋጅ የሚያስፈልግህ ነገር ምን እንደሆነና በዚህ ምድር ኑሮህ ሰማያዊ አስተሳሰብ እንዲኖርህ ሊያደርግህ የሚያስችለውን ነገር በማስተዋል እንድትመለከት አሳስብሃለሁ። በላይ በሰማያዊ ሥፍራ በጸጋው ዙፋን ላይ ሁልግዜ የሚኖረው እና ኃይሉን በልብህ ውስጥ መግለጥ የሚችለውን ደሙን ተመልክተህ ከዚያም በኋላ ከእግዚአብሔር እና ከበጉ ጋር ያልተቋረጠ ኅብረት ይኖርሃል ሰማያዊውንም ክብር በሕይወትህ መለማመድ ትጀምራለህ። ልምምዱ ወደ ነፍስህ ውስጥ ጠልቆ ይግባ የሰማይ በረከት የሆነው ደሙ ገና በምድር እያለህ አንድ ግዜ ተሰጥቶሃል ክቡር ደሙ በሰማይና በምድር ሕይወትን ይሰጥሃል።

## ደሙ ለመንግሥተ ሰማይ ዝማሬ ርዕስ ይሰጣል

እስከ አሁን ስንነጋገር የነበረው ከሽማግሌዎቹ አንዱ ስለ ተዋጁት የገለጸውን ሐሳብ ወስደን ነው። ይህ ልምምድ እና ምስክርነት ምን ያህል ይዘልቃል? ምስክርነቱንና ልምምዱን በተመለከተ ከተዋጁት ከራሣቸው አንደበት የሰማነው ነገር አለ? አዎን ራሣቸው ምስክርነት ሰጥተዋል። ዝማሬያቸው በተጠቀሰበት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በታላቅ ድምጽ "በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው" የሚል ዝማሬ ከአንደበታቸው ተደምጧል። ጌታ ኢየሱስ በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ ነበር ስለሆነም ለተዋጁት የአምልኮ ምክንያት ሆነላቸው።

ይህ እውነት የተዋጁት በዘመሩት በአዲሱ ዝማሬ ውስጥ የበለጠ ግልጽ ሆኖ ታይቷል ይኸውም "መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፣ ታርደሃልና፣ በደምህ ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን



ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፣ በምድርም ላይ ይነግሣሉ" ይላል (ራዕይ 5፡9-10)።

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ በጉ የክብር ስፍራ በሰማይ ያየውንና የሰማውን ለየት ባለ አገላለጽ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ይናገራል። በመጀመሪያ ጌታ ኢየሱስ በደሙ ያደረገውን ሲገልጽ "ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ ለእርሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን አሜን" በማለት ይገልፃል (ራዕይ 1፡5-6)

የበጉ ደም የዳኑትን ያለ ማቋረጥ የምሥጋና እና የደስታ ዝማሬአቸውን እንዲያቀርቡ በታላቅ ኃይሉ ያነቃቸዋል ምክንያቱም በመስቀል ላይ የመስዋዕትነት ሞቱ ራሱን ለእነርሱ ስለሰጣቸውና የራሱ ስላደረጋቸው ነው። ደሙ ኢየሱስ ላደረገውና እንዲያደርግ ላንቀሳቀሰው ፍቅር ዘለዓለማዊ ማህተም ነው። በተጨማሪም ደግሞ የማያቋርጥ ሰማያዊ የደስታ ምንጭ ሆኖ ይፈስሳል።

"ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን" የሚለውን አገላለጽ ልብ ብለን ካስተዋልነው በተሻለ ሁኔታ ልንገነዘበው እንችላለን። ስለ ክርስቶስ ደም ካለን የመገንዘብ ዓላማ ሊገታን የሚችል ምንም ምክንያት ሊኖር አይገባም የደሙ ከሆኑት የከበሩ ነገሮች እጅግ በጣም የከበረው ምልክትነቱ፣ መተኪያ የሌለው መሆኑና የፍቅር መግለጫነቱ ነው። እያንዳንዱ የደሙ ተግባራዊ ልምምድ ነፍስ በአስደናቂው የፍቅር ኃይል ልምምድ ውስጥ እንድታልፍ ያደርጋታል። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የደሙን ሙሉ ኃይል መለማመድ ራሱን ስለ እኛ እና ለእኛ በዘለዓለም ፍቅር ከሰጠበት መገለጥ አይለይም።

"ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን" የሚለው ይህ ፍቅር በእውነት ከመረዳታችን በላይ ነው። ኢየሱስ ለእኛ እንዳይሆን ያላደረገው ምን አለ? ራሱን ለእኛ ሰጠ፣ ስለ እኛ ኃጢአት እርግማን ሆነ፣ እንዲህ አይነቱን ቋንቋ መረዳት የሚችል ማነው? እግዚአብሔር ዘመንፈሱ በኩል ለእኛ ካልገለጠው በቀር ይህን የመሰለ ታላቅ ነገር ማሰብ የሚችል ማነው? ኢየሱስ በእውነት ራሱን ለእኛ የሰጠው ማድረግ የሚገባው ነገር ሆኖ በእርሱ ላይ ስለተጣለበት አይደለም ነገር ግን ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንድንኖር ይናፍቅ ከነበረው ጥልቅ ፍቅር የተነሣ ነው።

ስለዚህ ነገር ልባችን በጥቂቱ በመነካቱ መለኮታዊ መደነቅን ሳያስከትል አይቀርም ሆኖም እግዚአብሔር ይመስገን ይህ እውነት የሚሰማን ጊዜ መጥቷል በማያቋርጥ ፍቅር ወደ እግዚአብሔር ቀርበን ሰማያዊውን ሕይወት ተካፋዮች ስንሆን በዚያ ፍቅር እንሞላለን እንረካለንም በዚህ ምድር ሳለን በደሙ በኩል የተሻለ ግንዘቤና ፍጹም የመታመን ተስፋ ስላለን እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል በልባችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር አፍስሶታል፡፡ በዚህ ምድር ልባችን በበጉ ፍቅር አፋችንም በእምነት ምስጋና እንዳይሞላ ሊከለክለን የሚችል ነገር የለም፡፡ እያንዳንዱ የደሙ ኃይል ልምምድ እያደገ ሄዶ የክርስቶስ ፍቅር ልምምድ ይሆናል፡፡ "በደሙ ላይ አለመጠን ማክረር ተገቢ አይደለም አለበለዚያ ወደ ዘመናዊነት አመለካከት ተለውጦ ለሰዎች ትርጉም የማይሰጥ ይሆናል" የሚል አስተሳሰብ አለ እኔ ግን በዚህ ሐሳብ እንደማልስማማ መግለጽ እፈልጋለሁ እኔ ደም የሚለውን ቃል የተቀበልኩት ከሐዋርያው ዮሐንስ ሳይሆን ከክርስቶስ ከራሱ ነው፡፡ ቃሉ በእግዚአብሔር መንፈስ የተመረጠ እንደሆነ ከልቤ አምናለሁ ደሙን ሕያው ያደረገውና የዘለዓለምን ሕይወት ኃይል ተሞልቶ የደሙ ዝማሬ ወደ እኛ እንዲመጣ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ደሙ ከመረዳታችን በላይ የሆነ በረከትን ይዞ ወደ እኛ መጣ በአስተሳሰባችን ላይ የሚፈጠረር የተዛባ የደሙ አመለካከት ስንኩል የሆነ የሰው አተረጓጐም ውጤት ነው "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት" የሚለውን ማወቅና መለማመድ የፈለገ ማንም ቢኖር ቃሉ ከሰማይ እንደመጣ በእምነት ይቀበለዋል፡፡ ሐሴትና የዘለዓለም ሕይወት ኃይል በውስጡ እንዳለበት ቃሉን በተለየ ሁኔታ ይረዳዋል፡፡ "ደሙ" እና "የበጉ ደም" የሚሉት ቃሎች ቅድስትን የእግዚአብሔር የክብር ስፍራ እና አዲሱ ዝማሬ በታላቅ ሐሴት ለዘለዓለም የሚስተጋባበት አድርገውታል፡፡

ሰማያዊ ሐሴት በበጉ ደም በኩል በምድር ባሉት ባልተከፋፈለ ልብ ውስጥ ኃይሉን ይገልጣል፡፡ በላይ በሰማይ ደግሞ በአእላፋት መካከል በዙፋኑ ዙሪያ የክብርን ሥፍራ ይሰጣቸዋል፡፡ በመቤገርት ከእኔ ጋር ተካፋይ የሆናችሁ ወገኖቼ በሰማይ ያሉ በኩራት ስለ ደሙ ምን እና እንዴት እያሉ እንደሚዘምሩ የተረዳን ይመስለኛል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ያቀደልን እነዚህ መልካም ነገሮች በሕይወታችን ፍሬያማ እንዲሆኑ በታማኝነት እንጸልይ፡፡ እውነተኛ ሰማያዊ ሕይወት ለመኖር በሙሉ የደሙ ኃይል ውስጥ መኖር አስፈላጊ ነው ደሙ ወደ ሰማይ መግባትን ሰጠን፡፡



የማስታረቅ ደም በነፍስ ውስጥ በመሥራት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ላሉት ሙሉ መረዳትን ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ደም ወደ ቅድስት ውስጥ አመጣን ወደ እግዚአብሔርም አቀረበን ለመንግሥተ ሰማይም የምንበቃ አደረገን፡፡

የሚቀድሰው ደም ከክፉ ምኞትና ኃይል አዳነን በብርሃን ህብረት ለቅዱሱ የእግዚአብሔር ሕይወት ጠበቀን ደሙ ሰማያዊ የምሥጋና ዝማሬን ሰጠን፡፡ የወደደንና ራሱን ለእኛ የሰጠን የበጉ ደም ለእኛ ብቻ ያደረገልንን ነገር አይናገርም በዋናነት ሁሉንም ነገር እንዳደረገ ይናገራል፡፡ በከፍተኛ ደረጃ በደሙ ውስጥ የእርሱን ሕይወት ተካፋይነትን አገኘን፡፡ በእምነትና ራሱን በመስጠት ደሙ ያደረገለት በሙላት መለማመድ የፈለገ ብቻ በሰማይ ወዳለው የምሥጋና ዝማሬና ፍቅር የሚወስደውን መግቢያ ያገኛል፡፡

በመቤገርት ከእኔ ጋር ተካፋይ የሆናችሁ የሰማይ አጋሮቼ ይህ ሕይወት ተረት አይደለም፡፡ ለእናንተና ለእኔ የተዘጋጀ እውነት ነው ደሙ በመስቀሉ ላይ ብቻ ሳይሆን በዙፋኑም ላይ ታላቅ ክብራችን ነው ሕያው ወደ ሆነው ወደ በጉ ደም ምንጭ ውስጥ በጣም ጠልቀን እንግባ፡፡ የበጉ ደም እንዲሰራ ልባችንን አስፍተን እንክፈትለት ታላቁ ዘለዓለማዊ ካህን ያለ ማቋረጥ በደሙ እንደሚያነፃን ከልባችን እንመን ከዚህ በፊት ያልተለማመድነውን የደሙን ኃይል እንድንለማመድ በሚቃጠል ፍላጎት እንጸልይ ለእግዚአብሔር ካህናት በመሆን በደምህ ዋጀኸን እያሉ ከሚዘምሩት ታላቅ ሠራዊት ጋር በሚበልጥ የሐሴት ዝማሬ እንቀላቀል፡፡

በምድራዊ ሕይወታችን ይህንን ዝማሬ ያለማቋረጥ መዘመር አለብን እንዲህ እያልን "ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገን"

"ለእርሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን" አሜን!

አ! ግሩም ኃይል ነው አ! ግሩም ኃይል ነው

ጌታዬ ሆይ በደምህ ውስጥ ያለው አ! ግሩም ኃይል ነው

**ተ ፈ ፀ መ**

በእንግሊዘኛው "The power of the Blood of Jesus" በመባል የሚታወቀው ይህ መጽሐፍ አንድሪው ሙሬይ ከፃፏቸው መሠረታዊ መጽሐፎች የሚመደብ ነው። የክርስቶስ መስቀል ላይ የፈሰሰ ደሙ በመዋጀት ሥራ እንዲሁም ቅዱሳን በቅድስና ድል በመንሣት ለማመላለስ ያለውን ትልቅ ጉልበት የሚያሳይና በጠቅላላው በእግዚአብሔር አሠራር ላይ የክርስቶስ ደም ያለውን ትልቅ ሥፍራ ያሣያል።

መጽሐፉ የሚያጠነጥንበት ርዕሰ ጉዳይ ዘመን የማይሽረው ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው እና ማንኛውም አማኝ ሊገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ነው። በአሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያን መሠረቷን እንዳትዘነጋ እና ባለፉት አስርት ዓመታት እና ከዚያ በላይ የእግዚብሔርን መንግሥት የተቀላቀሉ አማኞች የክርስትና ሕይወታቸው በማይሻር እውነት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንዲመሠርቱ ለማድረግ ጥቅሙ እጅግ ብዙ ነው ከዚህ የተነሣ ይህ መጽሐፍ መመረጡ ትክክል ነው ማለት እችላለሁ።

መጋቢ ዮናታል ተኪኤ

"ክሩቅ በአክብሮት የምናውቀውን ወትሮ የሐሳባችንና የሰብከታችን ርዕሰ ጉዳይ ያላደረግነውን የክርስቶስ ደሙ ኃይል እንድናስተውል የተብራራ ማስገንዘቢያ ቀርቦልናል። በዚህ መጽሐፍ ከክርስቶስ ደም ጋር ተያይዘው የተነሱት ምንባቦች በጥሩ ሁኔታ የተተነተኑ እንደሆኑ ተመልክቻለሁ የዘለዓለም አለኝታና ድፍረት ያገኘንበትን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በማስተዋልና በአድናቆት እንድናይ የሚጋብዘን ይህ መጽሐፍ ልባችንን ለምሥጋናና ለጥንቃቄ ያንቃልን"

ንጉሤ ቡልቻ

"መጽሐፉ ለምድራችን ወቅታዊና አስፈላጊ ነው። የክርስቶስ የደሙ ኃይል መጽሐፍ ይዘቱ አጥንት ወይም የጽድቅ ቃል ቢሆንም በመንፈሳዊ ሕይወት ምስጢር ለመመላለስና የዘለዓለምን ሕይወት ለመውረስ ሊነበብ የሚገባው መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ እንዴት በክርስቶስ ደም መንፃትና መዋጀት ፤መቀደስ ጌታን ማገልገል፤ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ መኖርን በመጨረሻም ድል ማድረግ እንደሚቻል በዝርዝር ያትታል። "እውነት በብረት መቀነት ይቋጠራል በነፍስ ገበናም ይያዛል" እንዳሉት የዘመኑ አማኞች ሁላችን የዚህን መጽሐፍ እውነት በማስተዋል አንብበን በመያዝ እንኑርበት በጥቂት ሳይሆን በብዙ በግልብ ደረጃ ሳይሆን በጥልቀት እንጠቀማለን።"

መጋቢ ተኩ ከበደ